ይልቅ አጭር ጊዜ ብቻ ትቆያለች። ከዚያም ትመለስና በቤቱ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ትላለች። ሙሴ ዴ ማይሴ የያዛቸው የቤቱ ክፍሎች፣ የክብረ በዓል ክፍል ማለትም የንጉሡ ሥዕል ያለበትና ጥቂት የሚዋሰኑ ክፍሎች፣ ብዙ ጊዜ ባዶ የሚሆኑት በሁለተኛው ፎቅ ላይ ለጉብኚ ባለስልጣናት የሚሆኑ አፖርታማዎች ናቸው። ማዳም ዴ ማይሴ በበኩልዋ ከክፍሏ እምብዛም አትወጣም። የተቀረው የቤቱ ክፍል ለምሣሌ የመፀዳጃ ክፍሎች፣ የመተላለፊያ ክፍሎች፣ የእሊስ መኝታ ክፍል፣ የመልበሻ ክፍሎች፣ የምግብ ማዘጋጃ ክፍሎች፣ ጓዳዎች፣ የልብስ ማጠቢያ ክፍሎች ሁሉ፣ ለሁለቱ ጓደኞች መገናኘት ምቹ ቦታዎችን ሰጧቸው። የተለያዩት አካባቢዎች ግብረ አበርነታቸውን በውበት አደሱላቸው። ጥንቃቄአቸውንም የሚያጎን አደረጉላቸው። ሁለቱም ሁሌም ጥንቃቄ ቢያደርጉም በዚያ ሰፊ ቤት ውስጥ ለመወያየት አንድ ሺህ እድል ሰጣቸው።



# 12

ያልተጠበቀውን ውይይት ከንጉሡ ነገስቱ ጋር ባደረጉ በሚቀጥለው ማለዳ፣ ጆን ባፕቲስትና ሜትር ዣሪሚ ሁለት መድሃኒቶችን በማዘጋጀት ራሳቸውን በሥራ ወጥረው ነበር። ከመድሃኒቶቹ አንዱ፣ ለንጉሡ የሚሄድላቸው ሲሆን ሁለተኛው ካህናቱ እንዲመረምሩት ይላክላቸዋል።

በዚያኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ፣ በየአመቱ የዝክር ድግስ በሚደረግበትና በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ወደሚሠበሰብበት ከከተማው ወጣ ብሎ ወደሚገኝ ትልቅ ቤተክርስቲያን፣ ዲሚጥሮስ ይዟቸው ሄዱ። ፀሐይ ደማቅ ብርሃኗን ታበራለች። በያንዳንዳቸው አዕምሮ ውስጥ የነበረው የመጨረሻው ነገር የስቃይ ቅጣቱ ነበር። ዐይኖቻቸው ሊያዩ እስከሚችሉበት ርቀት ድረስ ሲመለከቱ፣ ነጭ የለበሱ ሴቶችና ህፃናት፣ ጥቋቁር ዣንጥላዎቻቸውን ዘርግተው፣ በትናንሽ አህያዎች ላይ ሆነው ይሰግራሉ። ሽማግሌ ወንዶች፣ ረዣዥም የእረኛ ዘንጐቻቸውን እየተመረኰዙ ይጓዛሉ። ደማቅ ቀለማት ያሏቸውን ካባዎች የደረቡ ብዙ ካህናትና መነኰሣት፣ መስቀሎቻቸውን በሰልፍ ሰድረው አለፉ። ከፍተኛ ባለስልጣኖችን ከፀሐይዋ ቃጠሎ ለማዳን ዙሪያ ክፈፋቸው ላይ የሚቅጨለጨሉ የብር ደወሎች ያሉባቸው ትላልቅ፣ ቀያይና ጥቋቁር ጃንጥላዎች፣ በወጣት ባሪያዎቻቸው ተዘርግቶ ተይዞላቸዋል። ሁሉም ሰው ወደ አንድ የጥድ ዛፎች ጫካ ያመራል። የነዚህ ዛፎች የታችኞቹ ቅርንጫፎቻቸው ወደ መሬት እየተጠማዘዙ ስለወረዱ ሕፃናት እየተንጠለጠሉባቸው ዥዋዥዌ ይጫወታሉ። ቤተክርስቲያኑ እምብዛም አይታይም። ስምንት ማዕዘን የሆነው ክብ የሣር ክዳን ጣሪያው፣ ተስተካክለው በተቆረጡና ከቤተክርስቲያኑ ግድግዳ ስምንት ጫማ ያህል ርቀው በበቀሉ ትላልቅ የጥድ ዛፎች ግንድ ላይ አርፏል። በነዚህ የዛፍ ግንዶችና በቤተክርስቲያኑ መካከል የጊንዲላ ወለሎችን በመጨመር ይህ ተፈጥሮአዊ ምሰሶ ወደ ክብ ሰገነትነት ተለውጧል።

ዲሚጥሮስ ጫማዎቹን ሲያወልቅ፣ መንገደኞችም በተመሣሣይ ፈፀሙ። የመጀመሪያውን የቤተክርስቲያኑን ክልል ጥሰው ለማለፍ ከቻሉ በኋላ፣ የተለያዩ የእድሜ ዘመናት ያላቸውን የፃድቃንና ሰማዕታት ሥነ ሥዕሎች ተመለከቱ። አንዳንዶቹ የባዘንታይን የአሣሣል ጥበብ ተፅዕኖ ያለባቸው ሲመስሉ፣ ብዙዎቹ ግን፣ በተለይ የአቢሲኒያውያን አሻራና

ዘዴ ያሰባቸው ናቸው። የስዕሉቹ አይኖች ሙሉ በሙሉ ከሚቆጣጠሯቸው ፊቶቻቸው ነፃ ሆነው የራሣቸው ሕይወት ያላቸው ይመስላሉ። የፃድቃኑና የሰማዕታቱ አካላት የተሣሉት በብሩህ ቀለም ነው። የቅድስናና የተአምራት መለያ የሆኑ የተከበሩ ምልክቶች ለፀሎት እንደሚያገለግለው የሞተ ቋንቋ፣ በብሩህ ቀለማት ተገልፀዋል። ይሁን እንጅ ማምሳያዎቹ የተወሰዱት ከአገራዊ ሞዴል ነው። ስለዚህም ከበድ ያለውና የበላይነት የሚታይበት የክርስቶስና የናቱ ምስሎች፣ የተራ ሴትና የሕፃን መልክ ያላቸው ናቸው።

ወደዋናው ከተማ ከተመለሱ በኋላ፣ ዲሚጥሮስ፣ ቤተመንግስቱን እንዲጎበኙ ወሠዳቸው። ከንጉሡ ጋር ወደተገናኙበት የክብር ቦታ ሲሄዱ ያረፉበትን ግቢ አሳያቸው። ወጣቱ ሰው በሰጠው ምልክት የተነሣ፣ የንጉሱ አራት አንበሶች ወደተኙበት ጉጆ እንዲያልፉ ዘበኞቹ ፈቀዱላቸው። ከእንስሳቱ አንዱ ወንድ፣ ሦስቱ ግን ሴቶች ሲሆኑ፣ አንዷ በጣም ወጣት ስለሆነች በወፍራም የብረት አጥር ውስጥ ታስራለች። ዲሚጥሮስ፣ እንስሳቱ የተከተቱበትን አንዳች የሰቃይ ቅጣትና የመስዋዕት ታሪክ ሲነግራቸው እንዳቀደ በማሰብ፣ ፖንሴ ለአፍታ ያህል ተጨንቀ። ይሁን እንጅ አውሬዎቹ፣ የንጉሡ የግላቸውና የግላቸው ብቻ መሆናቸውን፣ ሁልጊዜ ማለዳም አንድ ባሪያ እርሳቸው ባሉበት፣ ሥጋ ወደ ጉጆአቸው እየወረወረላቸው እንደሚመግቧቸው፣ ምንም አይነት ነገር ዕረፍታቸውን እንዲረብሽባቸው እንደማይፈቀድ ነገራቸው። ይህን ሲሰሙ መንገደኞቹ እፎይታ ተሰማቸው።

በመጨረሻም፣ ዲሚጥሮስ፣ በከተማዋ ውስጥ በሚገኙ መሣፍንቶች ቤቶች ብዙ የመታያ የእራት ግብዣ ጥሪዎችን ከሰዓት በኋላ አመጣላቸው። ለዚያን ዕለት አንዱን ብቻ ተቀበሉ። አስተናጋጃቸውም ለክብራቸው ሲባል የሚገመተውን ሁሉ አቅርበዋል። ጣፋጭ ምግቦችን፣ በቂ የጠጅ መጠጥ፣ እንዲሁም አነስተኛ ቡድን የሆኑ የሙዚቃ ተጫዋቾችንና ዘፋኞችን አቅርበዋል። በዚያን እለት ከሰዓት በኋላ፣ ብዙ ማስታወሻዎችን የፃፈው ፖንሴ፣ የአገሩን ባህል አይቶ ለመከተብ ቻለ። ካስተዋለው ውስጥ ወንዶች በባህሉ ምግብ ወደአፋቸው ለማድረግ ብዙም እንደማይደፍሩና በአኳያው ግን የሴት ጓደኛቸው አንድ፣ አንድ፣ ጉርሻ የሚሆን እያዘጋጁ እንደሚያጉርሷቸው፣ አቢሲኒውያን ሹካና ማንኪያ እንደማይጠቀሙና በጣቶቻቸው እንደሚያጉርሷቸው አስተዋሉ። ፖንሴ የተቀመጠው፣ በሰል ያለ እድሜ ካላት ረጋ ያለች ግዙፍ ሴት ወይዘሮ ቀጥሉ ነበር። የወይዘሮዋ ወፍራም ቅርፅ፣ የሚፈስስ በሚመስለው በጥልፍ ያጌጠ የጥጥ ቀሚስ ውስጥ ተሰይቶ ይታወቃል። አንዲት ወጣት ባሪያ፣ ስፌውን



እንጀራና ወጡን ከጠረጴዛው ላይ ስታስቀምጥና አጠገቡ የተቀመጠችው ሴት በረዣዥሞቹና የጠርቅ ቀለበት ባጠለቀችባቸው ጣቶችዋ፣ ግማሹን በወጭት ውስጥ ስትፈተፍተው ከቀናነት በመነጨ ስጋት ተመለከታት። ከዚህ በኋላ ሴትየዋ በሚያቃጥል በርበሬ በተሠራው ከቀይ መረቅ ውስጥ ካስዋኘችው በኋላ ሁሉንም ጠቅልላ ጆን ባፕቲስትን አጉረሰችው። በዚህ ጊዜ ወዲያውኑ ከገጠመው የሚያቃጥል ስሜት በስተቀር፣ መቃወም እርባና አልነበረውም። ሁለተኛውን ጉርሻ ዓይኖቹ በዕንባ ተሞልተው ተቀበለ። ሜትር ዠረሚም በስተቀኙ ካለች ለግላጋ ወጣት ሴት እጅ ተመሣሣይ መስተንግዶ ተደረገለት። ሌሎች ወንዶች እንዲህ ያለ አይን ያወጣ ተግባር ሲፈፅም አንዳችም የመደናገጥ ስሜት አልታየባቸውም። ይልቁንስ ፖንሴና ጓደኛው ይህን አስገዳጅ ጉርሻ ለማስቆምና እንደልባቸው ለመናገር ሲጥሩ፣ ሰዎቹ በበኩላቸው ደግሞ ከበድ ባለ ሁኔታ የጉርሻውን ተገቢነት ያረጋግጡ ነበር።

ሁለቱ ሰዎች እስኪጠግቡ ድረስ በልተዋል በሚል አጉራሾቻቸው ስለወሰኑ ይሁን፣ ወይም ደግሞ ባለፈው ተሞክሮ ላይ በመመስረት ይሁን ወይም ሴቶች የሚጠይቁት ዋጋ ይጠድቅብናል ብለው ይሁን ብቻ የስቃዩ ጉዳይ ቀጠለ። ፈረንሣውያኑ በጠጅ ጉርፍ ውስጥ ዋኙ። ውሰጣቸውም ነደደ። ሙሉ በሙሉ ጋሉ። በቤቱ ውስጥ ያሉት ሰዎች ቀስ በቀስ መውጣት ጀመሩ። ጥቂቶች በጨረቃዋ ብርሃን ውስጥ ቡና ለመጠጣት ወደ በረንዳው ወጡ። የፖንሴ ኮስታራ አጃቢ እንዲከተላት ጠቀሰችው። ሜትር ዠረሚም እንዲሁ በሌላ አቅጣጫ ከራሱ አጃቢ ጋር ጠፋ።

ዓይኖቻቸው በእንባ ስለበዙ፣ ከንፈሮቻቸውም በጠንካራ ቅመሞች ስለነደዱ፣ ፊቶቻቸው ላይ ውሃ በመርጨት ለማቀዝቀዝ እንዲችሉ ወደ መታጠበያ ክፍል የሚመሯቸው መስሏቸው ነበር። ከዚህ ይልቅ ስጋጃ ተነጥፎባቸው፣ ትራሶች ተደርድረውባቸው ባሉ ጨለማ ክፍሎች ውስጥ ራሳቸውን አገኙ። አስተናጋጆቻቸው በፀጥታ ልብሶቻቸውን በማውለቅ የነዚህን መንገደኞች የምግብ ፍላጐት ሃላፊነት እንደወሰዱ ሁሉ ሌላውንም ፍላጐታቸውን ፈፀሙላቸው። አጭር የእምቢታ መቋቋም ካደረጉ በኋላ፣ የባለስልጣን አስተያየትን የመቀበል ያህል የማኪያቤሊን ብልህ ዘዴ መቀበል እንዳለባቸው አመኑ። ሊያስወግዱት የማይቻልን ነገር በትጋት ማከናወን ተገቢ ነው። እውነታው ሲገለጥላቸው፣ ለተጀመረው ሥራ ድጋፋቸውን ሰጡ። በምድረበዳው ውስጥ ባሳለፏቸው ረዥም ቀናት፣ የወሲብ ግን ችነትን ፈፅመው

ረስተው ነበርና እንዲህ ባልተገመተ ሁኔታ ሲያገኙት ቢደነቁም አልተቆጎበትም። ጥቂት ቆይቶ ወደ እንግዳ ክፍሉ ሲመለሱ ሌሎች እንግዶች ፈንጠርጠር ብለዋል።

ዲሚጥሮስ፣ ሁለቱን ፈረንሳውያን ወደቤታቸው አጅቦ ሊወስዳቸው ጠየቃቸው። የአስተናጋጆቻቸው ባሎች፣ ከነዚሁ ፈንጠርጠር ብለው ከተቀመጡት መካከል ሣይሆኑ እንደማይቀሩ ባያጠራጥርም፣ ደስ ያላቸው የሚመስሉትን ሰዎች ፖንሴና ሜትር ዠረሚ እጅ ነሱ። ቀጥለውም ታዛዥነታቸውን በከፍተኛ ክብር የተቀበሉትን ሴቶች እጅ ነሱ።

ሁለቱ ሰዎች ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ይበልጥ ግራ ተጋብተው ተኙ። ከጆን ባፕቲስት አዕምሮ ውስጥ አልጠፋ ያለችውን አሲስን ሲያስብ ይህ የስጋ ፈቃድ እርሷን በስልት እንዲጣት መሰለው። ካጋጠመው ልዩ ሁኔታ ጋር ስሜቱ ተደበላልቆበት የወጣቷ ትዝታ ተቀሰቅሶበት፣ ሌሊቱን በውብ የደስታ ስሜት እያለማት አሣለፈው።

በማግስቱ ዘግይተው ከእንቅልፋቸው ተነስተው ወደ ቅመማ ቅመም ገበያ ለጉብኝት ሄዱ። በዚያም፣ ባርካ ውስጥ ላስተናገዳቸው ሙስሊም ምስጋና ይግባውና፣ እርሱ ያሣያቸውን ናሙናዎችና ብዛት ያላቸው እንደልብ የማይገኙ ሌሎች ዕፅዋት ለዕይታ ተደረድረው ተመለከቱ። ከነጋዴዎች ጋር ተነጋገሩ። እንዲያውም፣ ሥራቸው እነዚህን ድንቅ መዓዛና የመድሃኒትነት ጠባይ ያላቸውን ዕፅዋት ከሩቅና ከማይደረስባቸው ቦታዎች እየሰበሰቡ የሚያመጡ ሁለት ሰዎችን አገኙ። ስለተለያዩ ፍሬዎችና ቅጠላ ቅጠሎች አጠቃቀም ሲጠይቋቸው፣ በዚህች አገር ላይ በሚገባ የተጠናው የመድሃኒት ቅመማ ጉዳይ በመርዞች ላይ እንደሆነ ፖንሴና ሜትር ዠረሚ በድንጋጤ አረጋገጡ። በአውሮፖ ደህና አድርገው የሚያውቋት፣ ከጥንት ጀምሮ ትክክለኛና በተግባር የተፈተኑትን የሞት ውጤት የሚያስከትሉትን ሲሆን፣ የነዚህ ዕፅዋት ደካማ ዝርያዎቻቸው የሆኑ መድሃኒቶች ግን በግምት እንደቀሩ፣ ብዙ እንደሚያወዛግቡና እንዲያውም አንዳንዶች ጠቀሜታው ዝቅተኛ የሆነ ሣይንስ የሚሉት እንደሆነም ተገነዘቡ።

- የዚያን ዕለት፣ ለዕራት ወደ ሌላ ቤት ሄዱ። የባለፈው ዕለት ተሞክሯቸውን ስለሚያውቁ ምግባቸውን ራሣቸው መጥነው እንደሚጕርሱ ሙጭጭ ብለው፣ ከመጠጡም ትንሽ ጠጡ። የምግብ ፍላጐታቸውን ሁኔታ ካወቀች በኋላ ጣልቃ መግባቱ እንደማይረባ አስተናጋጇ ተረዳች። ሁለቱ ሰዎች ሲበቃቸው አቆሙ። ከምግቡ በኋላ ቡና ያፈላችላቸውን



ባርያ ልጃገረድ ተጠግተው በአቢሲኒያውያን ስነፅሁፍ ላይ ጕረቤቶቻቸውን በጥያቄዎች አዋከቧቸው። እንደማዘናጊያ ሆኖ ወደ እንስቶች ብዙም እንዳያስቡ ያደረጋቸው ከነርሱ ጭራሹኑ ያልገመቱት ፣ነገር ግን አቢሲኒያውያን ለስነግጥም ታላቅ ፍቅር እንዳላቸው አወቁ።

አጫጭሮቹና እንዲሠሟቸው ተብለው የሚነገሩትን ግጥሞች ወደ ኢጣሊያንኛ ለመተርጐም ዲሚጥሮስ ፈተና ሆነበት። የነዚህ ግጥሞች ውበት ኢትዮጵያውያን ሰምና ወርቅ ብለው በሚያነፃፅሩት መካከል መሆኑን ዲሚጥሮስ አብራራላቸው። ሰም፣ የወርቁ እንቁ የሚፈሰስበት ቅርፅ ማውጫው ነገር ነው። የቅርፁ ማውጫ መልክ ተራ ቢሆንም ውስጡ መሠረት አለው። ይህ ቅርፅ ማወጫ ሲሰበር፣ በውስጡ ያለው ሃብት ይወጣል። በግጥሞቹ ቃላት በመጀመሪያ ላይ ለዛ ቢስ አሳሳች ሲመስሉ፣ በሙሌ የአትኩሮት አጨዋወት ውጫዊው ትርጕማቸው ይጠፋና ሌላ ውስጣዊ ድንቅና ብልህ ትርጕማቸው ይገለጣል። የዲሚጥሮስ ትርጉም፣ ይህን ትርጓሜ የመለወጥ ሂደት፣ ሊገልፀው አልቻለም። ጆን ባፕቲስትና ጓደኛው እንግዶቻቸው ግጥሞቹን እንደገና በመጀመሪያ በሰም ቅርፃቸው ሲናገሩ፣ የመሰልቸትና የመተከዝ መመሳሰል ተመለከቱባቸው። ከዚያም ብዙም ግልፅ የማይሆን የቅላፄና የትርጉም ልዩነት ያከሉበታል። ይህን ጊዜ የወርቁን ሃረግ ተናገረ ማለት ነው። ያን ጊዜ ደግሞ ፊታቸው በአድናቆትና በጣም በሚገርም ደስታ ያበራል።

ሁሉም ሰው ተደስቶ ወደ ቤቱ ሄደ። ጆን ባፕቲስትና ጓደኛው ወደቤታቸው ሲሄዱ፣ ከልብ በመወያየታቸው ለሌሎች ሁሉ የግጥምን ደስታ በመመኘት እንኳን ደስ ያለን ሲሉ ለራሣቸው ተመኙ። ይህ ሁኔታ ቀደም ብለው እንዲሰቀቁና አዕምሮአቸውንም ነፃ እንዲያደርጉ ረዳቸው። ወደ መኝታ ከማምራታቸው በፊት፣ ከንጉሥ ነገስቱ ጋር እንዴት እንደሚሆኑ የመጨረሻ ውይይት አደረጉ። ጆን ባፕቲስት፣ ስለነገሮች ላይ ላዩን ብቻ እንዲመለከቱና የንጉሡን የህመም ምልክቶች ብቻ እንዲነጋገሩባቸው ለጓደኛው ሃሣብ አቀረበ። ሆኖም ግን፣ ለእውነት ቁርጠኛ ፍቅር ያለው ሜትር ዠረሚ፣ ጓደኛው ይበልጥ ሃቀኛ እንዲሆንና ንጉሡ ሕመማቸው በጣም ከባድ መሆኑን እንዲገነዘቡት እንዲያደርጋቸው የሚል ሃሣብ ሠነዘረ። ሰም ወይም ወርቅ ሁልጊዜም ወደ አንድ ነገር ይመለሳል። ቀጣዩ ተግባራቸው ላይ ከውሳኔ ሳይደርሱ እንቅልፍ ወሠዳቸው።

ንጋት ላይ እንደገመቱት ዲሚጥሮስ ቀስቅሷቸው፣ ንጉሰ ነገስቱን በግንባቸው ውስጥ ሊያዩዋቸው ሄዱ።

ንጉሡን በተሸበረ ስሜት ውስጥ ሆነው አገኟቸው። ወዲያው እንደገቡ ሞቅ ባለ ፈገግታ፣ እያሉ እንዲህ አሏቸው።

«አድናችሁኛል»

ጆን ባፕቲስትና ሜትር ዠረሚ ደንዝዘው ቀሩ።

«ማሳከኩ ትቶኛል። ሊገድለኝ የሚጀምረኝ ህመም ጠፍቷል። ትልቁ ቁስል ተቀርፎ ሊወድቅ የሚያገኙት ቦታዎች መድረቅ ጀምረዋል። የራሴን እምነት ባላተኩርበት፣የናንተንም ተአምር ፈጥሯል ማለት እችላለሁ። ተመልከቱ።»

ቀበቶአቸው እንደታሠረ እያለ፣ ክንዳቸውን ተራ በተራ ከእጅጌአቸው ለማውጣት ረዥሙን ቀሚሳቸውን እንደሸሚዝ ሊያወልቁት ቃጣቸው።

ፖንሴ ቁስሉን መረመረ።

«በጣም የተሻለ ሁኔታ ላይ ነው» ሲል አመነ።

« በጣም ስሜትህን የነካው አይመስለኝም» አሉ ንጉሡ « ይገባኛል፣ ጠንቃቃ ነህ። ውጤቱ ጥቂት ሊቆይ የሚችል መሆኑን እርግጠኛ ለመሆን ትፈልጋለህ። ትክክል ነህ፣ ነገር ግን ልንገርህ፣ እፎይታው ጊዜያዊ እንኳ ቢሆን ላንተ ፍፁም ውለታ አለብኝ፣ ከብዙ የማይቻል ስቃይ በኋላ የሰዓታት ሰላም ሰጥተኸኛል።»

«ግርማዊ ሆይ» አለ ፖንሴ «አሁን የምናየው የሚያበረታታን ነው። አሁን በተደረገልዎ ሕክምና ሕመምዎ ምላሽ በማግኘቱ ለማመን በቂ ምክንያት አለን። በሚቀጥሉት ቀናትም በጣም የመሻሻል ለውጦች እናያለን። ነገር ግን . . . »

እዚህ ላይ በጣም አስቃቂ በሆነ ቃልዕ ላይ እንደሚሰማራ ወታደር፣ ፖንሴ ወደ ዠረሚ ተመለከተ።



« . . . ሊያውቋቸው የሚገቡ አንዳንድ ነገሮች አሉ» ሲል ቀጠለ።

«እሰማሃለሁ»

«በሚያሰቃይዎ ህመም ላይ የነበረዎ ቅሬታ ቀንሶ ይሆናል። ጉዳቱ ለረዥም ጊዜም ቢሆን ሊቀንስ ይችል ይሆናል እንጂ ፍፁም አይድንም። ህመሙ እንደና ሊመለስ ይችላል። እርስዎም ከህመሙ ጋር መኖር መቻሉን ሊቀበሉ ይገባል። ያለጥርጥር ግን . . . »

እፍታ ጊዜ በፀጥታ እንዲያልፍ አደረገ። ንጉሡ አይናቸውን ሣያርገበግቡ ፍጥጥ ብለው ተመለከቱ። ጆን ባፕቲስት የራሱን አረፍተ ነገር የመጨረሻውን ሲናገር ራሱን ሰማና ራሱ ተገረመ።

« . . . በዚሁ ጠንቅ ሊሞቱ»

ዲሚጥሮስ እነዚህ ቃላት ከተረጐማቸው በኋላ፣ ንጉሡ መልስ እንዲሰጡ ተመለከታቸው። መልሱ ወዲያውኑ አልተሠጠም። ንጉሡ ተነስተው ቆሙና ወደ ክፍሉ ማዕዘን በመራመድ በጭለማው ውስጥ ከተሠወሩ በኋላ ተመልሰው ወደነርሱ መጡ።

«የምትነግረኝን ባልወደውም፣ ቋንቋህ ያስደስተኛል። ንግግሩ የአስመሣዮችና የሸንጋዮች አይደለም። እኔ ለማዳመጥ መቻሌን በማሰብህም ትክክል ነህ።»

ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለው የጧፉን ነበልባል ተመለከቱ። እንደገና የጆን ባፕቲስት ዓይኖች ውስጥ ትኩር ብለው አዩ።

«ከዚህ ሕመም ጋር ለምን ያህል ጊዜ ልኖር እችላለሁ?»

«አላውቅም» አለ ፖንሴ

«እውነት አይደለም» አሉ ንጉሡ፣ ጐላ ባለ የቁጣና የባለስልጣን የድምፅ ቅላፄ

ጆን ባፕቲስት ግራ ተጋባ።

«በዚህ ዓይነት በሽታ ተለክፎ የሚሠቃይ ሰው ከሁለት ዓመት በላይ በህይወት መኖሩን የማውቀው ማስረጃ የለኝም።»

ንጉሡ፣ ዐረፍተ ነገሩ በትክክል መነገሩን ሰሙ። ቀና ብለው ፀጥታውን ሰበሩት።

«ለኔ በግሌ ከሆነ ሞት ምንም አይደለም። ነገ ልሞት እችላለሁ። ለዚህ ዝግጁ ነኝ»

የንግግራቸውን ሞገስ ቀዝቀዝ ለማድረግ ተመልሰው ተቀመጡ።

«ነገር ግን» ሲሉ ቀጠሉ «የማከናውነው ጉዳይ አለኝ። ትልቁ ልጄ»ሲሉ ቀጠሉ «ገና አስራ አምስት አመቱ ነው። አሁንም ገና ለጋና በቀላሉ ሊጠመዘዝ የሚችል ነው። እኔ ባልነበርኩባቸው ረዥም ጊዜያት ከካህናቱና ከቤተመንግስቱ ስላገኘው ትምህርት ይጨንቀኛል። ዙፋኑን ለርሱ እንዲፀናለት ማድረግ ችዬ ህይወቴ ቢያልፍ ደስ ይለኛል። ይህ ካልሆነ ሦስት የነገስታት ትውልድ አንዳችም ሳይፈይድ ይቀራል።»

የቀለጠው ሰም ቁልቁል ሲፈስስ፣ ሚያዎን ትክ ብለው ተመለከቱት

«ሁለት ዓመት?» አሉ

ብድግ ብለው በገቡበት በር አጠገብ ወዳለ ወንበር ሄዱ። በወንበሩ ላይ በአራት ማዕዘን ቅርፅ የታጠፈ ነጭ የአንገት ልብስ አለ። የአንገት ልብሱን ትከሻቸው ላይ ወርወር አደረጉና ራሳቸውን ጠበቅ አድርገው ጠቀለሉበት።

«አያቴ ዙፋኑን ሲወርሱ» ሲሉ ቀጠሉ «ይህች አገር ሙሉ በሙሉ በሥርዓተ አልበኝነት ውስጥ ነበረች። ጠላቶቻችን ፍፁም አወደሟት፣ ሎሌዎቻችን ነፃነቶቻቸውን መልሰው አገኙ። ካህናቱም በንጉሡ ላይ ፍላጐታቸውን ጫኑባቸው። በአገር ቤት ህዝቡ በርሃብ ያልቅ ነበር።»

ዞር አሉና ወደነርሱ ተራመዱ

«የራሳቸውን ሙታኖች የበሉ ገበሬዎች ነበሩ»

ፖንሴ አይኖቹን ሰበራቸው። ሜትር ዠረሚ በጨለማው ላይ አፈጠጠ።

«የዚህች አገር ሁኔታ ይህን ይመስል ነበር። ሁሉም ነገር ገና መሠራት ይኖርበታል። ንጉሣዊ ሥልጣን በሚገባ መረጋገጥ ይገባዋል። ጠላቶቻችን ወደኋላ መባረር ይኖርባቸዋል። መኳንንቶቹ እጅ መስጠትን ነው ያመጡልን፣ ካህናቱ የእንቅስቃሴው ተቆጣጣሪዎች ሆኑ። ቅድመ አያቴ ፋሲለደስ፣ ሂደቱን በድምቀት ጀምሮ ይህች በዙሪያችን የምትገኘውን የጐንደርን ከተማ ቆረቆረ። ለዘመናት ቤተመንግስቱን ይዛ የኖረችውን አክሱምን ካወደማት ሙስና በተለየ መልኩ፣ ጐንደርን አዲሲቱ ዋና ከተማ አደረጋት። ከዚያ በኋላ የመጣው የርሱ ልጅ፣ የኔ አባት ነው። አባቴም ለአገሩ እንደ አያቴ ታማኝ፣ ታላቅና ቁርጠኛ ነበር። የአባቴን አልጋ ስወርስ፣ ረዥም



ዘመን ለመንገስ፣ የታሪካችንን ቅርስ ጠብቄ ለማቆየትና እንዲያፈራም ለማድረግ ጥሩ እድል ነበረኝ። ለህዝቡ የግብር መጠን ቀንሻለሁ። አገሪቱን ወደተበጣጠቀችና ተለያይቶ ወደሚኖር ቦታ የለወጧትን የቀማኞችንና የዘራፊዎችን የኬላ ቀረጥ አስወግጃለሁ። ከሁሉም የበለጠ የሕግ የበላይነትን ተግባራዊ አድርጌአለሁ። ሕጉ ጥብቅ ነው። ይሁን እንጅ በህግ ፊት ሁላችንም እኩል መሆናችንን እያንዳንዳችን የምናውቀው የአባቶቻችን ሕግ መሆኑ አያጠራጥርም።»

ቀስ በቀስ ንጋት ደረሠ። ሀምራዊ የደመና ቀለም በመስኮቱ ውስጥ ሰንጥቆ ሲገባ ከበላዩ ጨለማ ሌሊት፣ ከስሩ ደግሞ ግራጫ ፈሳሽ ይታያል።

«ይህን ሁሉ ብቻችንን ማከናወናችንን ታውቃለህ። ብቻችንን። ከጐረቤቶቻችን እርዳታ መጠበቁን የተውነው ከረዥም ጊዜ በፊት ነው። እነርሱ ይጠሉናል። ከዚህም ሌላ ከርቀት ሆነው ወዳጆቻችንና ወንድሞቻችን አድርገን ከምንቆጥራቸው የባህር ማዶ ካቶሊኮች ራሳችንን መጠበቅ ይኖርብናል። ከአንድ ክፍለ ዘመን በፊት ቱርኮች ይህችን አገር ሲወሩ፣ በጊዜው ንግሥ የነበረው ንጉስ፣ የፖርቱጋሎችን እርዳታ መጥራት ፈልጐ ነበር። የታላቁ የቫስኮ ልጅ ክርስቶፈር ዳጋማ ሕይወቱን ሳይቀር አሣልፎ ሰጥቶናል። ያዳኑን ግን ከአደጋው በኋላ ጀስዊቶቻቸውን ሊልኩልን ብለው ነው። ካህናቱ እንደመጡ ማን መሆናቸውን እንኳ ያወቀ አልነበረም። አያቶቻችን እጆቻቸውን ዘርግተው ተቀበሏቸው። በክርስቶስ ወንድሞቻችን አይደሉ? ጳጳሱን እንድንታዘዛቸውና ከካቶሊኮች ጋር እንደገና እንድንቀላቀል ሲጠይቁን ተቃውሞ አላደረግንም። እስቲ አስበው። ከሌላው አለም ተገልለን በመቅረታችን እጅግ ተጐድተናል። የዳግም ቅልቅሉ ሃሣብ አያስደስትም? ይሁን እንጅ፣ የነርሱ የወንጌል ትርጉም ከኛ ትርጓሜ የሚበልጥበትን መንፈሣዊ የመከራከሪያ ነጥብ አቅርበው እንዲያረጋግጡ ጠየቅናቸው። ይህ በርግጥ ተገቢና ትሁት ጥያቄ ነበር። የኛ ካህናት ንትርኩ ውስጥ ሃሣብ ሰፊ ሆነው ገቡ። ሆኖም ግን በንባብና በጥናት ያገኙትን ታላቅ ዕውቀት አመጡት። በራሣቸው በጣም እርግጠኞች የነበሩት ጀስዊቶች ለጥያቄዎቻችን መልሶቹን እንደማያውቁ መናዘዝ ነበረባቸው። ወደሮም ተዋርደው ተመለሱ።

«ጳጳሱ በጣም የተማሩና ይሉኝታ የለሽ የሆኑ ሌሎች ቀሣውስትን ላኩ። እኛ አሁንም፣ እንደወንድሞቻችን ተቀበልናቸው። የነርሱ ተግባር ግን የጠላት ዓይነት ሆነ። በዚያ ጊዜ ትልቁ ደካሞታችን ንጉሡ ነበሩ። ምስኪኑ ሰው በቀላሉ ሃሣባቸውን ተቀበሏቸው። በጀስዊቶች

ኘርውዣዊ ውስጥ ሆነው ብዙ መጥፎ ውሳኔዎችን ፈፀሙ። በመጨረሻም ባላቸው ሙሉ ሥልጣን ሁሉም በጅምላና አገሪቱም ወደ ካቶሊክነት እንዲለወጡ አዘዙ። በጣም ዘግይቶም ቢሆን፣ ከወሰን ድንበራችን ባሻገር ካሉት ሌላ፣ ሌሎች ክፋዎች መኖራቸውን አወቅን። እነርሱም ወዳጆቻችን መስለው የማንፈልገውን እንድንቀበል ያደረጉን ናቸው። ዝርዝሩን ለሌላ ጊዜ አቆይሃለሁ። ነገር ግን የፈረንሣውያኑ ካህናት የጠንቅ መዘዞች፣ አዕምሯችንን አሸንፈው፣እንድንታዘዛቸው ሊያደርጉን የሚያበቃቸው አዲስ እምነት በግድ ሊጭኑብን የሚያስችላቸው፣ በመሃከላችን አለመግባባትና ጠብ ፈጥረን ሽባ እንድንሆን በመፈለግ፣በሽፍጥ ሊገዙን የሚያግዟቸው ለቁጥር የሚያታክቱ ማስረጃዎች ነበሩ። አገራችን እጅግ የከፋ የርስ በርስ ጦርነት ያየችው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው። የከፋ ውጥረት በነበረበት ጊዜ እንኳ ተጠብቆ መኖር የቻለው የንጉሠ ነገስቱ ሥልጣን እንክትክት አለ። ይህ ሁሉ የሆነው ንጉሡ በቅዕበታዊ ድክመታቸው የነዚህን እንግዶች እምነት ለመቀበል በመሞከራቸው ነው። ያን ጊዜ ሊከራከሯቸው ባይችሉም በቀሳውስቱ ዙሪያ ጥገኝነት ፈለጉ። ጠላቶቻችን በውስጣችን የተቀሰቀሰውን ግርግር ለራሣቸው ጠቀሜታ አዋሉት። ይህንን የተከተለው ሶስት ትውልድ፣ ሊፍቀውና ሊያስተካክለው የጣረው የገለፅኩልህን ትርምስ ነው።

እየተረጋጉ ደበልጥ ለስለስ ብለው ቀጠሉ።

«አየህ ነገሮች ሁሉ ይህን በመሰለ ደረጃ ላይ ናቸው። እኔም ጊዜ የፈለግሁት ለዚሁ ነው።»

በዚህ ጊዜ ነግቶባቸው ነበር። ንጉሡ ወደ ፖንሴ ተጠግተው እጃቸውን በትከሻው ላይ አሳረፉ። እጃቸው ክችች ያለ ደካማና ክብደት ያልነበረው ነበር።

«አንተን የመሣለ ሰው ስመለከት ከምዕራብ የሚመጣልንን ሁሉ ላለመቀበል የምናደርገው ጥረት ትልቅ ሃፍረት ሆኖ ይሠማኛል። ጎረቤቶቻችን ድንገተኛ ወረራቸውን ከምድረበዳው ከመጀመራቸው በፊት የናንተና የኛ ሥልጣኔ አንድ ነበር። በአያቶቼ ቤተመንግስት ግሪክኛ ይነገር ነበር። አሁንም ቢሆን በራችንን እነዚህ ወንድሞች ለሚባሉት እንዳንከፍትላቸው፣ እንዳንሰበር ስጋት አለን። ሁላችንም ደህና አድርገን እንደምናውቀው፣ አሁንም ሃይማኖታችንን ሊያስለውጡን እየሠሩ ናቸው። የሚያደርጉት ነገር የሚያጠፋን መሆኑን አልተረዱም»

እጃቸውን አነሱና ወደበሩ መራመድ ቀጠሉ።



«አመሰግንሀለሁ» አሉ በደስታ። «ህይወቴ አሁን ተሰፋ አለው። ማከናወን የሚገባኝን አውቃለሁ። ይህን ለመፈፀም ምን ያህል ጊዜ እንደቀረኝም አውቄአለሁ።»

ንጉሡ ወጥተው ሄዱ። ጉብኝዎቻቸው አዝነውና ተክዘው በዝምታ ቀሩ። የቀን ብርሃን እያየለ ወደ ክፍሉ መዝለቁ የረበሸው ዲሚጥሮስ፣ ወደቤታቸው አጅቧቸው ተመለሠ። ልብሶቻቸውን ሲቀይሩ፣ ወጣቱን ከሁለት ሰዓት በኋላ ለማግኘት ተስማምተው ብቻቸው እንዲተዋቸው ጠየቀ።

በሩ እንደተዘጋ ሜትር ዣሪሚ ዘልሎ ጆን ባፕቲስት ላይ ተከመረበት።

«አብደሃል እንዴ? ምን ለክፈህ? ተስፋቸውን እያለመለምክ፣ ረዥም የህመም ዘመን እንዲኖራቸው የሚያደርግ መድሃኒት እንደምታዘጋጅላቸው ተስማምተን ነበር። ታዲያ ባደረግኸው ነገር የምታዝንበት ምን ተገኘ? ሕመሙ እየበረታ ስለመሄዱ ምን ግምት ተፈጠረብህ?

«አውቃለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት። ጭንቅላቱን በሁለት እጆቹ መሃል ቀብሮ «ሰውዬውን ስመለከታቸው . . . ራሴን ለመዋሸት አልቻልኩም።»

«ውሸት አንድ ነገር ነው። ነገር ግን እውነቱን ሁሉ ለምን ትነግራቸዋለህ?»

«ሁሉንም ነገር እንድዘረግፈው ያደረገኝ በሰውዬው ውስጥ ያለ አንዳች አስገዳጅ ሃይል ነው።»

«በርሣቸው ውስጥ ሣይሆን ባንተ ውስጥ ነው» አለ ዣሪሚ «ሳንድ ንጉስ እጣ ፈንታውን መንገር! ምን ዓይነት እብደት ነው። ወዳጄ፣ ራስህን ፈጣሪ ነው ያደረግኸው። ነገሩ በጣም ቀላል ነው። ይህ ሁሉ ሌላ ሳይሆን ትምክህት ነው። እያበጠ የመጣ ትልቅ ትምህክት»

«አይመስለኝም» አለ ፖንሴ ዝቅ ባለ ድምፅ። «እኔ የማስበው ተቃራኒውን ነበር። ሣነጋግራቸው ንጉሥ ሆነውብኝ አይደለም። ልክ ለ . . . ወንድም እንደምናገረው ነው።»

«ወንድምህን ነዋ ስሜቱን የወጋኸው»

ንግግሩን ሣይጨርስ በሩ ላይ ሦስት ጊዜ ማንኳኳት ተሰማ። ፕሮቴስታንቱ ሊከፍት ሄደ። ሁለት የጥበቃ መኮንኖች ሊይዟቸው መጡ።

# 13

ዘበኞች የተቆጡ ይመስላሉ። የሚናገሩትም የራሣቸውን ቋንቋ ብቻ ነው። ፖንሴና ሜትር ዠረሚን ሌሊት በተጠቀሙት የምስጢር በር በኩል ሣይሆን፣ የቤተመንግስቱን ግድግዳ ሙሉ በሙሉ ዞረው በዋናው የክብር በር በኩል ወሰዷቸው።

ጠባቡን የእንግዳ መቀበያ ክፍል አቋርጠው መጀመሪያ ከራስና ከቀሣውስቱ ጥያቄዎች የተኘጉደጉዱላቸው የእንግዳ መቀበያ አዳራሽ ውስጥ ገቡ። በቦታው ላይ እነዚያው ባለስልጣናት ነበሩ። በመካከላቸው ባለው የድንጋይ ወለል ላይ በአንሶላ የተሸፈኑ ሶስት ሰዎች ተጋድመዋል። አንድ ካህን ሲናገሩ፣ ከንጉሡ ጋር ይፋዊ የሆነውን የመጀመሪያ ንግግር ሲያደርጉ፣ በአረብኛ ሲያስተረጉም የነበረው ቱርጁማን ወደፊት ቀረበ።

«በእጃችሁ የተዘጋጀ መድሃኒት ሰጣችሁን። ይህም ለንጉሡ የሚጠቅም እንደሆነ ታስቦ ነው። ባሮች ቀመሱት። እናም ሁሉም ሞቱ» አሉ

ጆን ባፕቲስት በእጅጉ እፎይ አለ። የባሰ መጥፎ ይገጥመኛል ብሎ ፈርቶ ነበር። «ይፋ» የተባለው መድሃኒት ከውሃ፣ ከዱቄትና እንዲያቀልመው ሲባል ከቀይ ስር ጭማቂ ተዋህዶ በዲሚጥሮስ ፊት የተዘጋጀ ነበር።

«ለክቡራኑ እንዲህ በል» አለው ጆን ባፕቲስት። «ያዘጋጀነው መድሃኒት በጣም ቀላል ነው። ናሙናችንን ከመላካችን በፊትም እኩል መጠን ያለውን ለንጉሠ ነገስቱ አገልጋይ ለጌታ ዲሚጥሮስ ሰጥተነው ነበር።»

የዲሚጥሮስ ስም ሲጠቀስ፣ ቱርጁማኑ ገና ማስተርጎም ሣይጀምር በአዳራሹ ውስጥ ጉርምርምታ ጀመረ። ወጣቱ ግሪካዊ እንዲመጣ እንደተላከበት፣ ሁለቱ መድሃኒት ቀማሚዎች ተረዱ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ አንዲት ትንሽ ሣጥን ይዞ እያሳበው ደረሰ። በዚያች ሣጥን ውስጥ ለቀሣውስቱ የተሰጠው ነገር ግማሹ ነበረበት።

ወጣቱ ረዘም ያለ ንግግር አደረገ። ምንም እንኳ ፈረንሣውያኑ ምን እንደሚል ባይረዱትም፣ የቅላፄውን ሞቅ ማለት ለራሳቸው እንደሚስማማቸው ተረጎሙት።



እንቅስቃሴውን ከቃላቱ ጋር እያስማማ፣ ዲሚጥሮስ ሳጥኗን ከፈታት። ከተዘጋጀው ውስጥ የላቀጠች ፍሬ ጠልፎ አወጣና በይፋ እየበላ አሣያቸው። ከዚያም በዙሪያው ላሉት ሁሉ አደላቸው። ቀሣውስቱ የማስመሰል ጥላቻ አሣዩና ከአጭር ውይይት በኋላ ስብሰባው ተበተነ። ወዲያውኑ አዳራሹ ባዶ ሆኖ በሩ ተዘጋ። ጫጫታ ያለበት ወሬ ግን ይሰማ ነበር።

ግጭቱ መቋጨቱን ዲሚጥሮስ በፈገግታ ገለፀ

«እነዚህን ሦስት ያልታደሉ ሰዎች በመመረዛቸው፣ ንጉሡ የሞት ቅጣት ይፈርዱባቸዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ» አለ ጆን ባፕቲስት

ጥቂት ወታደሮች በፀጥታ ወደ አዳራሹ ገብተው፣ የአስከሬኖቹን ቁርጭምጨሚቶች ይዘው ጐተቷቸው።

«አንድ ሰው የሚፈረድበት፣ ሰው ሲገድል ብቻ ነው። ባሮች ደግሞ ሰዎች አይደሉም» አለ ዲሚጥሮስ ኮስተር ብሎ።

ከዚህ በኋላ ሁለቱ ሃኪሞችና መንገድ መሪያቸው ክፍሉን ለቀቀው ወጡ። የሌሎችን መከራ መቀበል፣ በተለይም መሳው ህብረተሰብ ያፀደቀው ከሆነ ለመልመድ በጣም ቀላል ነው። በነዚህ ሰለባዎች ላይ የተፈፀመውን የፖለቲካ ሤራ ወዲያውኑ ረስተው በድርጊቱ ጅልነት ብቻ ሣቁ።

የዚህ አይነቱ ተግባር፣ ንጉሡ በምን ዓይነት ብዙ አደጋዎች መሃል ሥልጣናቸውን እንደሚጠቀሙበት እንዲገነዘቡ ረዳቸው። ንጉሠ ነገስቱ የሚተማመኑባቸውም እንደ ዲሚጥሮስና ሃጅ አሊ የመሰሉ ከውጭ አገር በመጡ ሰዎች ላይ ብቻ ነበር። ከነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ በወታደራዊ ወረራ ወይም ዘመቻ ጊዜ የተማረኩና የታሠሩ ናቸው። ቱርካውያን አፍነው የሚወስዷቸውን ወጣት ክርስቲያኖች በማስለም፣ የሱልጣኑ ጠባቂ ወታደራዊ ጓድ እንደሚያደርጓቸው ዓይነት፣ ንጉሡም ወጣት ሙስሊሞችን ክርስትና በማንሣት አገልጋያቸው ሊያደርጓቸው፣ እነርሱ ፍፁም ታማኝነታቸውን ያረጋግጡላቸዋል። ከአገራቸው ውጭ ለሚደረጉት ምስጢራዊ ተልዕኮዎች እንደ ሃጅ አሊ ያሉትን ከፍተኛ ውለታ ያላቸውን ሰዎች ወይም አርመናውያንና የአቶማን ከሊፋ ዜጋ የሆኑ የምስራቅ ሜዲተራኒያን ክርስቲያኖችን ይጠቀማሉ።

ፖንሴና ጓደኛው፣ ጐንደር በኖሩበት ጊዜ የንጉሡን ምስጢራዊ ጠባቂ፣ የርሱንም ጥላ ከለላ መለየት ቻሉ። ከዲሚጥሮስ በተጨማሪ በጣም ጠንቃቃና ማንነታቸው ተለይቶ የማይታወቁ ምስክሮች፣በሚጓዙባቸው ጉዳናዎች፣ ምግብ በሚበሉባቸው ቤቶች ፣ እፅዋት በሚሰበስቡባቸው የባላገር አካባቢዎች ሁሉ ከጐናቸው ይኖራሉ። የማያስቀይመውን የገበሬዎች፣ የወሮበሎችን ወይም የነጋዴዎችን ሁኔታ በማየት ንጉሡ በፈረንሣውያን ላይ ያላቸውን ሃያልነት ይቀበላሉ።

እነዚህ ተጓዦች በዋናው ከተማ ውስጥ የሰነበቱባቸው ሣምንታት፣ የየዕለቱን ሕይወት ትዕይንት የአይን ምስክር ሆነው እንዲያረጋግጡ ዕድሉን ሰጥቷቸዋል። የአገሬውን እንግዳ ባህል ተመልክተዋል። ምንም እንኳ በዚህኛው መስመር ቁጥብ መሆናቸው መጥፎ ስም ቢያስጣቸውም፣ ጥቂት የሲጋ ፈቃድ ግንኙነትንም አድርገዋል። ከዚህም ባሻገር ብዙ ቤተክርስቲያናትን ጐብኝተዋል። አገራዊውን ባህላዊ የስዕል ቅብ ተመልክተዋል፤ በመጀመሪያ ላይ አልጥማቸው ያላቸውን የአገሪቱን ሙዚቃ አድንቀዋል። በተለይም ሙዚቃው በውዝዋዜ ታጅቦ ትዕይንትና ድጋፍ ሲኖረው ውበቱን በተሻለ መረዳት ችለዋል።

ብዙ ነገሮች ከምን እንደተሠሩ፣ ከእንጨት ይሁን ከመዳብ ወይም ከቀርከሃ ፈጥነው ለማወቅ ቻሉ። የእጅ ስራዎቻቸው ዓይነት፣ መስያየትና መብዛት፣ በንጉሠ ነገስቱ ግዛት ውስጥ ብዙ የተለያዩ ባህሎች አብረው መኖራቸውን ያንፀባርቁላቸዋል። ፖንሴ፣የማስታወሻ ደብተሩን በሙንጭርጭር ፅሁፍ ሞላው። ለዘዴኛው ዲሚጥሮስ ምስጋና ይግባውና ሌላም ገዛ። አቢሲኒያውያን ወረቀት ስለማያውቁ የሚፅፉት በብራና ላይ ነው።

ጥርጣሬ ላለመቀስቀስ፣ እንደመጀመሪያው ቶሎ ቶሎ ባይሆንም ንጉሡን ማየታቸውን ቀጠሉ። የሕመማቸውን ሣይሆን የምልክቱን ቀስ በቀስ መክሰምና መለወጥ መዘገብ ቻሉ። ንጉሡ ስለህመማቸው መብርታት ወይም መሻል ፈፅሞ ደግመው አልጠየቋቸውም። በሌላ በኩል ለቁጥር የሚያታክቱ ስለ ባህል፣ ስለሳይንስና ስለምዕራባውያን አገሮች ፖለቲካ ይጠይቋቸው ነበር።

ንጉሡ እንደገና ለወታደራዊ ዘመቻ እንደሚንቀሣቀሱ ዲሚጥሮስ የሚያረዳቸው ዕለት ደረሰ። የሲናር ንጉስ፣ በድንበር አካባቢ የተፈጠረውን አነስተኛ ግጭት ሰበብ በማድረግ



በአቢሲኒያ ላይ ጦርነት አውጇል። ጐንደር ከመሰንበት ይልቅ ንጉሡን ተከትሎ መሄዱ አደጋው አነስተኛ እንደሚሆን ወጣቱ ግሪካዊ ነገራቸው። የንጉሡን ድጋፍ ለማግኘት በአደገኛ ሁኔታና በብልጣብልጥ አካሄድ የመድረሳቸው ጭምጭምታ በሚናፈስባቸው በሁለቱ ባዕዳን ላይ፣ የቤተመንግስቱ ባለስልጣናት በሚያገኙት ተነፃፃሪ ነፃነት ሌላ ሴራ ለመጠንሰስና ለመፈልፈል ዕድል ይኖራቸው ይሆናል። የፈረንሣውያን ሐኪሞችን ባለስልጣናቱ በይፋ ያስተላለፉላቸውን መመሪያ በመጣስ በአደገኛ ሁኔታ ወደ ንጉሡ ቀርበዋል። ያዘጋጁላቸውንም መድሀኒት የወሰዱና የዳኑ በማስመሰል በመግለፅ፣ ሕመማቸው እንደተሻላቸውና በመጨረሻም ንጉሡ መዳናቸውን ሁሉም እንዲያውቁት በማድረግ አስወሩ። ንጉሡም ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ብዙ ስጦታዎች ለሁለቱ ባዕዳን ሸለሟቸው። ከዚህም ባሻገር፣ በከተማዋ ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች ሕሙማንም ገንዘብ ያገኙ ነበር። በጊዜ ብዛት ጆን ባፕቲስትና ሸሪኩ ጓደኛው ከሁሉም ዓይነት ደረጃ ከሚመጡ ሰዎች ጋር እንዲገናኙ ጥሪ ይጐርፍላቸው ጀመር። ይልቁንም ንግስቲቱ የሚማረሩበትን ህመማቸውን እንዲያክሙ በይፋ በመጠራታቸውና በተሣካ ሁኔታ በመፈፀማቸው ካህናቱ በርግጥ ተቆጥተዋል።

ንጉሁን በወታደራዊ ዘመቻቸው ላይ የማጀቡ ጥያቄ ሲመጣ፣ እውነቱ መገለፅ ያለበት ጊዜ መድረሱን ጆን ባፕቲስት ወሰነ። አቢሲኒያ ውስጥ መቆየቱ ምንም ያህል ደስታ ይስጠው እንጂ፣ የጉዞው እውነተኛ ምክንያትና እርሱም በይሁንታ ለመቀበል የተገደደበትን አይዘነጋውም። አንድ የአቢሲኒያን ኤምባሲ ይዞ መመለስ ይኖርበታል።

ኤምባሲ ይዞ የመመለስ እድሉ ደግሞ የተረጋገጠ አይደለም። ንጉሡ፣ ጀስዊቶችንና ምዕራባውያን ሃይሎችን ያላመኑበትን ምክንያት ፈረንሣውያኑ ተገንዝበዋል። ንጉሠ ነገስቱም አገራቸው በሯን የምትከፍትበት ጊዜ ገና መሆኑን ነግረዋቸዋል።

የኤምባሲ ሃሣብ ጉዳይ የፖለቲካ መሰናክል ቢሆንም፣ ሌላ የግል የሆነ ችግርም አለ። እስከ አሁን ድረስ ፈረንሣውያኑ፣ ንጉሠ ነገስቱ ዘንድ ለመድረስ የነበራቸውን የረዥም ጊዜ ዕቅድ ጥቅም ብቻ ነው ያገኙትና አሁን ግን የዚህን ዕቅድ ጉዳትም ማሸተት ጀምረዋል። የንጉሁን አመኔታና ወዳጅነት ለማግኘት ያደረጉት ጥረት፣ እነርሱ ከመጀመሪያውኑ ተስፋ ካደረጉት ይልቅ በጣም ተሳክቶላቸዋል። ከሁሉም የበላይ የሆኑት ንጉሠ ነገስት ወድደዋቸዋል። ከነርሱ ጋር በመተማመንና በፍቅር ተሣስረዋል። ለዚህ ደግሞ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የማያጨቃጭቅ ማረጋገጫ ሰጥተዋል። እነርሱ ያከናወኑት ጨዋታ ግን አደጋ

አልነበረውም ማለት አይደለም። ከንጉሡ ነገስቱ ጋር የፈጠሩት ወዳጅነት፣ ንጉሡ፣ እነርሱ ለኤምባሲ ያላቸውን ጉጉት እንዲቀበሉ ያደርጋቸው ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ ሊሆን የሚችለው ከነርሱ በፊት ሌሎች ብዙ ተጓዦች ላይ እንደተፈፀመው ክርሣቸው እንዳይለዩ እድሜአቸውን ሙሉ አስረው ሊያስቀሯቸው መቻላቸው ነው። ጆን ባፕቲስት በሚቀጥለው ውይይት ጊዜ ለንጉሡ ነገስቱ ሊነግራቸው ወሰነ። ቀኑን ሙሉ ካይሮን፣ ካይሮ የሚገኘውን ቤቱንና ማዳሞዜል ዴ ማይሌን ሲያስብ ዋለ። የራሱን ሃሣብ እየመላለሰ በማባባስ፣ የመመለስ ናፍቆቱ በጣም ስለአየለበት፣ ሌላው ቀርቶ ሃሣቡን የማይለውጥ ተቃዋሚንም ቢሆን ለማሣመን በውስጡ ሃይል ተሰማው።

ንጉሡ ሁልጊዜም ጉልላት ባለው የቤተመንግስቱ ክፍል ውስጥ አይቀበሏቸውም። ብዙ ጊዜ ዲሚጥሮስ ይመጣና ንጉሡ ነገስቱ በአንድ ደን ዳርቻ ነብርና አንበሣ ለማሣደድ ቀን ቀን በሚያርፉበት የአደን ድንኳናቸው ድረስ ይወስዳቸዋል።

አሁን አሁን በተለመዱ ጉዳዮች ላይ ማውራት ጀምረዋል። ይሁን እንጅ፣ ንጉሡ የክብራቸውን ደረጃና ተፈጥሮአዊ ግርማ ሞገሣቸውን ፈፅሞ ዝቅ አላደረጉላቸውም። በዚያን ዕለት ማታ ለክብራቸው ከባለስልጠኖቻቸው ጋር የእራት ግብዣ አደረጉላቸው። ሰስቱም ሰዎች በእንጀራው ላይ ወደ ፈሠሠው ወጥ እጃቸውን እየሰደዱ ያጠቅሣሉ። ዲሚጥሮስ፣ ዜጐችን ለሚገዛው ህግ ተገዥ ነው። ስለቀጣዩ ዘመቻና ስለንጉሡ መሄድ ተወያዩ። ምግቡ ካበቃ በኋላ አንድ ወታደር በጣሣ ውሃና ገበቴ አቅርቦ ጣቶቻቸውን ታጠቡበት።

«ግርማዊ ሆይ» አለ ጆን ባፕቲስት ብቻቸውን ሲሆኑ «አሁን ስለገዛዎ ተነጋገርን። ነገር ግን ስለኛ ደግሞ እንድናገር ይፍቀዱልኝ»

ቃላቱ አሻሚ ናቸው። የንጉሡ ነገስቱ ዓይኖች ሲያርፉበት፣ በተመሣሣይ አቅጣጫ ስለመንዛቸው ፖንሴ እንዳልተናገረ ገባው።

«ግርማዊነትዎ ጠርተውን መጥተናል። እኛም በአቅማችን ልክ መስራት የሚገባንን ፈፅመናል። ከመጀመሪያው ጀምሮ ሃጅ ዓሊን ከሃሣባችን ውጭ አድርገነው ነበር። አሁን ግን ወደመጣንበት አገር የመመለሻ ጊዜአችን ነው።»



አንድ አገልጋይ በትናንሽ ስኒዎች ቡና አመጣ። ንጉሡ ለእንግዶቻቸው በራሣቸው እጅ አቀረቡ። አቢሲኒያውያን «ጤና አዳም» ከሚሉት ውብ መዐዛ ካለው ተክል ላይ ጥቂት ቅጠሎችን እየበጠሱ ወደ ቡናቸው ውስጥ እየጨመሩ ለመናገር ጊዜ ወሠዱ።

«በጣም የሚገርም ነው። እዚህ ኗሪ የምትሆኑበትን ሁኔታ ዛሬ ማታ ላዋያችሁ ነበር። ለዘመናት ያለን እስገዳጅ ሕግ በጣም ጥብቅ ነው። እንግዶች ሁል ጊዜም እንኳን ደህና መጣችሁ ቢባሉም፣ አገራችን ውስጥ መቆየት ይኖርባቸዋል። ችግሩን ታውቁታላችሁ። ከዚህ ስነስርዓታችን ለቀን በወጣን ጊዜ ሁሉ ሲከተለን የነበረውን አሣዛኝ ጉዳይም ሳይቀር ታውቁታላችሁ። እኔም ሕጉን ለመጠበቅ አስባለሁ።»

ፖንሴ ወደ ጓደኛው ዞር ብሎ፣ ቀጥሎ ምን ሊገጥም እንደሚችል እያሰበ ሲመለከት፣ በፕሮቴስታንቱ አይኖች ውስጥ አላምንም የሚል ስሜት አነበበ።

«በቁጥጥር ስር ላደርጋችሁ ሃሣቡ የለኝም። ወይም ደግሞ በጣም ሊያስቸግራችሁ የሚችለውንና እኔም የምረዳውን ተገልሎ የመኖር ሕይወት ኑሩ አልልም። ስለዚህ ሃሣቤ በይፋ ሹመት ለጥቻችሁ፣ ቤተመንግስቱም እንዲያፀድቀው አድርጌ፣ እኔ የምገምተውን የናንተን ከፍ ያለ ዋጋ ልከፍል የሚችል ዳረጐት እየተሰጣችሁ እንድትኖሩ ነው።» ሲሉ ንጉሡ ተናገሩ።

«ግርማዊ ሆይ» አለ ፖንሴ፣ ደስ በሚል ወዳጃዊ ቁርጠኛ አነጋገር፣ «በበኩሌ አዝናለሁ። ልንቀበልም አንችልም። ከመጀመሪያ ጀምሮ ወደ ካይሮ መመለስ እንዳለብን ነግረንዎታል።

«እውነት ነው» አሉ ንጉሡ ነገስቱ «ይህንንስ ነግራችሁኛል። የካይሮ ፓሻም በአወዳሽ ደብዳቤው ውስጥ ይህንኑ ገልጿል። ያ አንድ ነገር ነው። የገለፅከላችሁን ሥነስርዓት ለመጣስ ምናልባት ይህ አንድና ብቸኛው ሁኔታ ይሆናል። የካይሮውን ፓሻ እንደ ጠላቴ ነው የምቆጥረው። በሌላ በኩል እኛ ስራ አብረናቸው ከምንሰራቸውም ጋር ጠላት ነው። እኔ በአባይ ላይ ባለኝ ሃይል ምክንያት ይፈራኛል። እኔ ደግሞ እነርሱን የምፈልግበት ጉዳይ አለኝ። እዚህ ያሉት ጳጳስ ሲሞቱ፣ አዲስ ፓትርያርክ እንዲላክልን ይፈቅዳል። በባህላችን የኛን ቋንቋ የማይናገር፣ እዚህ ከመምጣቱ በፊት ግብፅ ውስጥ ከሚገኘው ገዳሙ ወጥቶ የማያውቅ መነኩሴ፣ እዚህ እኔ ፊት እየተንቀጠቀጠ በመቆም የቤተክርስቲያናችን የበላይ መሆን

ከመቸውም ጊዜ በበለጠ አሁን በጣም ጠቃሚ ነው። ስለዚህ ለግብፅ ፓሻ በገባሁለት ቃል መሠረት እንድትሄዱ ልፈቅድላችሁ እችላለሁ።»

« ለግርማዊነትዎ እጅግ ትልቅ ውለታ አለብን።»

«እኔም አንድ ተመሣሣይ ጥያቄ እንዳቀርብላችሁ ፍቀዱልኝ» አሉ ንጉሡ

ፖንሴ ጭንቀላቱን ዝቅ አደረገ። የበላይ ገዥው ፍላጐታቸውን በሃይል ለመጫን ባይፈልጉም አግባብተው ሊያቆዩዋቸው የመሞከር ጥረታቸውን ግን አልተዉትም።

«ምንም አይነት ፍቅር ሊነፍጋችሁ ከማይችለው ከአንድ ክርስቲያናዊ ልዑል ይልቅ ይህን አንዳችም ምስጋና ምን ጊዜም አሣይቷችሁ ለማያውቀው ለዚህ ቱርካዊ ለማገልገል ለምን መረጣችሁ?»

«ግርማዊ ሆይ የምንመለሰው ለካይሮው ፓሻ ስንል አይደለም» አለ ፖንሴ።

«ታዲያ ለምንድነው?»

ወጣቱ ሃኪም ወዲያውኑ አሰበ። እንግዲህ ተቃርበናል። ቡናውን ፉት አለና ቀጠለ።

«እንደሚያውቁት ሜትር ዠረሚና እኔ ሸሪኮች ነን። እሱ እኔን ይከተለኛል። እርግጡን ግን ወደቤት መሄድ የምፈልገው እኔ ነኝ።

«እንግዲያው ደህና፣ እኔም ጥያቄውን ያቀረብኩት ላንተ ለጆን ባፕቲስት ነው» አሉ ንጉሁ

«ይኸውልዎ ግርማዊ ሆይ፣ ከአንዲት ወጣት ሴት ጋር ፍቅር ይዞኛል» አለ ፖንሴ።

ንጉሡ ሣቁ። እንዲህ ሲስቁ ሲያዩ የመጀመሪያቸው ነበር። ድምፅ አውጥተው በጣም ሲስቁ፣ ጭንቅላታቸውን ወደ ኋላ ጣል አድርገው ነው። ጭውውቱ እንደገና እንዲቀጥል ዲሚጥሮስ በአክብሮት ጠበቀ።

«ደህና» አሉ ከሁሉም የበላይ የሆኑት ንጉስ። «በኔ ቤተመንግስት ውስጥ ሙሉ በሙሉ በወርቅ በተሸፈነ መኖሪያ ቤት ለመኖር እጅግ እንደምትደሰት አስባለሁ። እንደሠማሁት ካይሮ



በጣም ይሞቃል። ሴቶች ደግሞ የኛን ያየር ጠባይ ይመርጣሉ። ሚስትህ ጐንደር መጥታ አብራህ እንድትኖር አድርግ»

«ሚስቴ አይደለችም።» አለ ጆን ባፕቲስት

«እዚሁ ልታገባት ትችላለህ»

«እውነቱን ለመናገር፣ ግርማዊ ሆይ . . . እዚህ ደረጃም ላይ ገና አልደረስንም።»

ንጉሡ፣ ያን አስደናቂ አሣሣቃቸውን እንደገና ሣቁ።

«ታዲያ ምን ደረጃ ላይ ነው የደረስከው?»

«ግርማዊ ሆይ፣ ይህች ወጣት የማህበረሰብ ደረጃዋ ከኔ እጅግ ከፍ ያለ ነው። አባቷ፣ በመንግስታችን ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ አላቸው፣ እኔና እርስዋ እንፋቀራለን»

ይህን እንደተናገረ ምናልባት ዕድሉን ሊሞክር እንዳሰበ መሰሎት ጆን ባፕቲስት ለአጭር ጊዜ መጥፎ ስሜት ተሠማው። በአፍቃሪ ላይ በሚነገር አጉል እምነት የተነካ፣ በዚህ በተለየ ነጥብ ላይ ስለ ዕጣ ፈንታ ከሌላው ሁሉ ነገር በበለጠ ፈራ።

«አሁንም ቢሆን ቤተሰቦችዋን ማሳመን መቻል ይኖርብኛል። ይህ ደግሞ ቀላል የሚሆን አይደለም።»

«እንግዲያው በአንድ ታላቅ ንጉስ አጠገብ እንደምትኖርና አንተም ከከፍተኛ መኮንኖቼ አንዱ እንደምትሆን ንገራቸው።»

«አቤት! ግርማዊ ሆይ፣ እርስዎ ሰዎችን በተሻለ ያውቋቸዋል። ሰዎች አርቀው አያዩም። ምንም ነገር ይሁን በቀጥታ በአይናቸው ስር ካልሆነ የለም የሚሉ ናቸው። ለግርማዊነትዎ የማገልገል ሹመት፣ የብዙ ማዕረጐች ክብረት እንዳለውና የታላላቅ ቤተሰቦቻችንን ልጆች በኩራት እንደሚሞላቸው በሚገባና ሙሉ በሙሉ አውቃለሁ። ነገር ግን ያፈቀርኳትን ልጅ አባት ለማሣመን ይህ በቂ አይሆንም»

ዲሚጥሮስ ተርጐሞ እስኪጨርስ ለጥቂት ጊዜ አቋረጠ:: ከዚያም ድምፁን ከፍ አድርጐና እያንዳንዱ ሃሣብ በአምሮው ውስጥ እንዳመጣለት አስቦ እንዲነግረው ጭንቅላቱን ግራና ቀኝ በማወዛወዝ ቀጠለ::

«ግርማዊነትዎ እኔን ለመርዳት የሚቻለውን ሁሉ እያደረገልኝ መሆኑ ይታየኛል:: ለዚህም ባለውለታ ነኝ:: እንደ እውነቱ ሌላም ነገር አለ . . .»

«ምንድን ነው? ተናገረው»

«ብናገረው ድፍረት ይሆንብኛል:: ምክንያቱም አስተሣሰቡቼ እርስዎ አጥብቀው ከሚይዙት የፀና እምነትዎ ጋር በተቃራኒው የሚሄድ ነው»

«ቀጥል! ተናገር:: የምከለክልህ ከሆነ፣ ቢያንስ ከሁለት አንዳችን፣ መሞከር ሲገባን ያላደረግነው ኸለን ብለን እንፀፀታለን::»

«እንግዲያው እንዲህ ነው» አለ ጆን ባፕቲስት በመጨረሻ:: ልክ አንድ ሠው ጭንቱን ከትከሻው ላይ አንቃንቆ እንደሚጥለው አይነት ቃላቱ በጥድፊያ ይወጡ ጀመር:: «የፍቅረኛዬ አባት ዲፕሎማት ናቸው:: ለርሣቸው ደረጃ ተመሣሣይ በሆነ ማህበረሰባዊ ቦታ ለመድረስ ብችል በደስታ ይቀበሉኛል:: እኩል መሆኔንም ያረጋግጣሉ:: ወይም የተመሣሣይ አለም አባል መሆኔን ይቀበላሉ:: ይህ ሊሆን የሚችለው ግርማዊነትዎ እኔ በአቢሲኒያ የፈረንሣይ ንጉስ፣ የግርማዊ ሉዊስ አስራ አራተኛ፣ ቋሚ አምባሣደር፣ እንድሆን እርስዎ ሃሣብ ቢያቀርቡ ነው:: ከዚያ በኋላ ወደዚህ ልመለስና የደረጃዬን አንፀባራቂነት ለማፈቅራት ሴት አረጋግጣላታለሁ:: ግርማዊነትዎ በሁፋንም አጠንብ የሚሰጡኝን ደረጃ የፍቅረኛዬ አባት ሊረዱት የሚችሉት ካልሆነ ዝቅ አድርገው ይገምቱታል ብዬ እፈራለሁ»

«ኤምባሲ ነው?» አሉ ንጉሡ

በዚያን ቅፅበት፣ በንጉሣዊ ድንኳን ስር የገባው ድንገተኛ ነፋስ፣ የአሸዋ አውሎ ነፋስ ከወለል ላይ በማስነሣቱ ውይይቱ ቆም አለ::

«አየህ፣ ይህ የኛ ባህል አይደለም» አሉ የሁሉም የበላይ «ለጐረቤቶቻችን መንገር የሚገባን ጉዳይ ካለ በተቻለ መጠን በነጋዴዎች፣ ቅዱሣን ቦታዎችን ለመሣለም በሚጓዙ



ሰዎችና አንዳንዴም በለማኞች ሣይቀር በቀጥታ መልዕክቶቻችንን እንልካለን:: የየመንግስታቸው ይፋ ባለስልጣኖች ተደርገው ሰዎች ሲላኩልን፣ ለምሣሌ በቀድሞ ጊዜ ከፖርቱጋል እንደተላኩት አይነት እብሪታቸው ደማችንን ያፈላውና አገራችንን ለቅቀው ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ እንፈቅድላቸውም ነበር»

«አውቃለሁ» አለ ፖንሴ

ንጉሡ በጠረጴዛቸው ዙሪያ እጃቸውን በሸካራው የድንኳን ጨርቅ ላይ ምንም እንደማያስብ ወይም እንደማያዳምጥ ሰው አሣርፈው ወዲያና ወዲህ አሉ::

«ከዚህም በተጨማሪ፣ እናንተ ጀስዊቶች የምትሏቸው ካህናትና ሌሎችም እንዲሁ አሉ:: የአረቦችን ልብስ እየለበሱ በድንበሮቻችን አካባቢ በማንገዋበብ፣ ወደ አገራችን ለመግባት አመቺ የሚሆናቸውን አነስተኛ ሰበብ ሁሉ አፈፍ ያደርጋሉ:: ሕፃን እያለሁ፣ ልክ እኔ፣ አንተ እንድትመጣልኝ እንደላክሁት፣ አባቴም፣ ከካይሮ ሃኪም እንዲመጣለት ላከ:: ሁለት መነኮሣት መጡ:: ጥቂት ቢጠራጠርም፣ በወዳጃዊ ሁኔታ ተቀብሎ አስተናገዳቸውና ሐኪሙ ማንኛቸው እንደሆነ ጠየቃቸው:: ዶክተሩ ከነሱ ጋር ጉዞ ሊጀምር እንዳልቻለና እነርሱ ግን ቀድመው መምጣታቸውን በጥሞና ተናገሩ::

«እና ምን ሆኑ?» ሲል ጆን ባፕቲስት ጠየቀ

«የፈረንሣይ ካህናት ተመልሰው መምጣታቸውን ህዝቡ ሲሰማ፣ መሠብሠብ ጀመረ:: የኛ ካህናትና መሣፍንት ደግሞ፣ ከዚህ በፊት እንዳጋጠመን መጥፎ ዕድል፣ ንጉሡ ሃይማኖቱን ይለውጥ ይሆናል በሚል ፍርሃት፣ በተገለለ ቦታ አስቀመጡት:: በማንኛውም ሰዓት የርስበርስ ጦርነት ሊፈነዳ የሚያሰጋ ነገር ነበር:: ንጉሡ አባቴ፣ ፈፅሞ አላመነታም:: ሁለቱንም እንግዶች በቁጣ ለወጣው ሕዝብ አሣልፎ ሰጣቸውና በቤተመንግስቱ ፊት ለፊት በድንጋይ ተወግረው ሞቱ:: ይህን ያነሣሁልህ፣ እኛ ባንፈልጋቸውም እንኳ እዚህች አገር ለመግባት ምንም ነገር እንዲያቆማቸው የማይፈልጉ አክራሪዎችን ኤምባሲው ከመነሻው ይዞ ቢመጣ የሚል ስጋት መኖሩን ልገልፅልህ ነው::»

«ትክክል ነው» አለ ጆን ባፕቲስት፣ እንደተከዘ ቆይቶ። ወዲያውኑ የመጣለትን ሃሣብ ለመናገር እንደከጀለ ሆኖ ቀጠለ። «ግርማዊነትዎ በሚገባ የሚያውቁትን፣ ለካህናቱ ያለዎትን ጥላቻ የሚያውቅና እነርሱን ወደዚህች አገር ፈፅሞ ላለማምጣት ቃል የሚገባልዎትን አምባሣደር ይሹሙ። ይህ አሠራር ጉዳዩን ሁሉ ፍፁም በአዲስና ጠንካራ መሠረት ላይ ይጀምረዋል። እኔ እንደማስበው፣ ግርማዊነትዎ በእውነት የሚያስፈራዎ እምብዛም ነው። በተቃራኒው ግን፣ በአገርዎ ያለውን ሁኔታ ከሚያውቁት የፈረንሣይ ንጉስ መልዕክተኛ መቀበል፣ ጉን ለጉንም የጄስዊቶችን የብልጣብልጥ እንቅስቃሴ ማወቅዎና ቀሣውስቱ የሚፈፅሙትን የመጀመሪያ አዲስ የዘመቻ እንቅስቃሴ ምልክት ለሁሉም የበላይ ንጉሳችን ሪፖርት እንዲያደርጉ ይረዳዎታል። ንጉሰ ነገስት ሉዊስ አስራ አራተኛ፣ ከጳጳሱ ጋር ከፍተኛ ግቡቡንት ስላላቸው የሃይማኖታቸው ማህበር ያለውን ከፍተኛ ጉጉት እንዲገታው ሊጠይቋቸው ይችላሉ። ብዙ ነገሮች የሚሆኑት እርስዎና አገርዎ በኛ አገር በሚገባ አለመታወቃችሁ ነው። ፕሮፖጋንዳ በማይምነት ውስጥ ስር ይሰድዳል። ግልፅ በመሆኔ ይቅር ይበሉኝ። ስናገረው ያሳፍረኛል እንጂ፣ ጄስዊቶች፣ ይህች አገር በማይምነትና በጭካኔ የተሞላች የአረማውያን ምሣሌ ነች እያሉ መናገር ችለዋል። ይህ ደግሞ፣ የእምነትን ብርሃን እንዲያስገቡ ለማስቻል ለነርሱ ክብርና ዝና ይሠጣቸውና ባለውለታ ያደርጋቸዋል። እኔ ያለውን እውነተኛ ሁኔታ ለንጉሣችን በትክክል ማስረዳት ብችል እርሣቸው ይረዱኛል። በሁለቱም አቅጣጫ ልረዳዎት እችላለሁ። በጋራ መከባበር ላይ የተመሠረተ ግንኙነት ባላቸው፣ አንዱ በምዕራብ ሌላው በምስራቅ በሚገኙ ሁለት የክርስቲያን ንጉሦች መካከል እንዲኖር ልረዳዎት እችላለሁ። ይህ አካሄድ የንጉሠ ነገስት ግዛትዎን ሰላም በማናጋት ስልጣንና ዘለዓለማዊውን ነፍስ ለመንጠቅ የሚጥሩትን የሰርጎገቦችን ምንጭ ከመነሻው ይገድበዋል።»

ቀስ በቀስ እያደገና እየጋለ፣ ሌሎችን ሲያሄስ የቆየበት ረዥምና ቁጣ የተሞላበት ንግግሩ ሲያበቃ፣ ድንገተኛ የሆነ መደነቅና የመውደድ ስሜት ስላሳደረበት፣ ጆን ባፕቲስት ዓይኖቹን በንጉሡ ላይ ተከለ። ንጉሡ መንቀሣቀስ የማይችሉ መስለው ለረዥም ጊዜ ቆዩ። ከዚያም ዘበኛውን ጠሩት። በአንድ እጁ አለንጋ፣ በቀበቶው ላይ ጉራዴ የታጠቀ ረዥምና በጣም ቀጭን ወጣት መጣ።

«ፈጥነህ ሰው ወደ ከተማ ላክ። ሙራድ እዚህ እንዲመጣ አድርግ» አሉት።



# 14

ሰው ምንም ያህል ዋሾ ቢሆን፣ ሌባም ቢሆን፣ ቃሉን የማይጠብቅና ከሃዲም ቢሆን እንኳ፣ እድሜውን በሰላም ለመጨረስና ለተባረከ ረዥም ዘመን የሚበቃው ጠንካራ እምነት ሲኖረው ብቻ ነው። ቅንጣት ታህል እምነት ያለው፣ የዕምነት ፅናቱ ፍፁም የሆነ፣ በሆነ ባልሆነው ጉዳይ ዕምነቱ የማይዛባበት ሰው፣ ከክፉ ነገር ሁሉ ይጠበቃል። ሙራድ እንዲያ ያለ ሰው ነው። ይህ አርመናዊ፣ በካውካሰስ ሕዝቦች ላይ ብቻ የሚታየውን ዓይነት የማይገመት ዕድሜ ኖሯል። የካውካሰስ ሕዝቦች በሂሳብ ጉብዞች ቢሆኑም፣ የዕድሜ ጉዳይ ሲነሣ ስለሚጃጁ ይምታታባቸውና ፤ የታላላቆቻቸውን ዘመን እንኳ መናገር ያቅታቸዋል። የሙራድ ረዥም እድሜ በሁለት ክፍሎች ብቻ ሊከፈል ይችላል። የመጀመሪያው የልጅነት ጊዜው ነው። በሻን ሐይቅ አጠገብ በምትገኝ መንደር ውስጥ የሕፃንነት ዘመኑን ያሣለፈው ሙራድ፣ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ከነጋዴ አባቱ ጋር ነው። ከአስራ አምስት አመቱ ጀምሮ፣ ባልተቋረጠና ባልተናጋ አራት የአቢሲኒያ ነገስታት ዘመን አገልግሏል። የኢትዮጵያን የቅርብ ጊዜ ታሪክ በሙሉ በዓይኑ ያየ ሰው ነው። የጄስዊቶችን ተልዕኮ፣ ከአገር መባረራቸውን፣ ከዚያም የተከተለውን የስርዓት አልበኝነት ጊዜ፣ የፋሲለደስ ወደስልጣን ዳግም መመለስና መንግስት መቆጣጠር፣ የልጅ ልጁ እያሱ ያከናወናቸውን ሁሉ አይቷል። ቋንቋዎችን በማወቁ፣ በዲፕሎማሲ ጥበቡ፣ ሰዎችን ፈጥኖ በመፈረጅ ችሎታው፣ በተለይም ወደህንድና ባሲ ወደሚገኘው የደች ተጠሪ፣ የነገስታቱ ተመራጭ የመንግስት መልዕክተኛ እንዲሆን አድርጎታል። ለረዥም ጊዜ በቆየው ዝናው ሳቢያ፣ አሁን በቅርቡ ከተመለሰበት ተልዕኮ ባታቢያውያን ስለአድናቆታቸው የሰጡትን ብዙ የነሐስ ደወል ይዞ መጥቷል።

ጆን ባፕቲስት፣ ጎንደር ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ሙራድን ብዙ ጊዜ አግኝቶታል። በመጀመሪያ እንደተገናኙ ሙራድን ዕድሜው መከላከያ ያልሆነለትን ሕመም አከሞለታል። ነገር ግን በዕድሜው ምክንያት እንኳ ሲደክም ባልቻለው የፍትወት ብርታቱ ይህ ሕመም እርሱ እንዳለው «ለሃያ አራተኛ ጊዜ» ይዞታል። የፖንሴ ሕክምና ውጤታማ ነበር። ሽማግሌው፣ ሃያ አምስተኛውን የመለከፍ ዕጣ ለመቀበል፣ ከዕለታት አንድ ምሽት ላይ አንዲት ያለተዳረች ውብ ድንግል ወጣት ሴት አስከትሎ ሲንቀሳቀስ ድንገተኛ በሆነ የአንጎል ውስጥ ደም መፍሰስ ግማሽ ሰውነቱን በድን አደረገበት። ጆን ባፕቲስት ሳደረገለት እንክብካቤና ጥንቃቄ ምስጋና ይግባውና የተጎዳው ጎኑ ቀስ በቀስ ወደ ሕይወት ተመለሰለት። ሆኖም ግን፣ አንዱ እጁ አሁንም

ሲሰንፍበት ከንፈሮቹም የወደቁ ናቸው። አዕምሮው ግን ጉዳት አላገኘውም። ንጉሡ የራሣቸውን አስተያየት ሁልጊዜም ያለአድልዎ በማድነቅ በሚመለከተው ሰው ሃሣብ ላይ መጨመራቸው ወጣቱን ሃኪም ፖንሴን እፎይ አሰኘው።

ሽማግሌው ከአንድ ሰዓት ቆይታ በኋላ ደረሠ። ሲያዩት እንቅልፉን ሳይጨርስ አስቀድሞ እንደተነሣ ሰው ቅር መሠኘትና የመበሳጨት መልክ ይታይበታል። ሙራድ ትንሽ እንደሚተኛና ለዚያውም ጥሩ እንቅልፍ እንደማይወስደው፣ አለመደሰቱን የሚያሣየው መቃጣትም ለማስመሰል እንደሆነ ጆን ባፕቲስት አውቋል። ይህ ገፅታው፣ ገና ምክክር በሚደረግበት ጉዳይ ላይ የሽማግሌውን ዕርካታ የሚደብቅለት ዘዴ ነው። ሽማግሌው፣ አታላይ ነጋዴ ስለሆነ፣ ይህ የቅሬታና የብስጭት መልክ ለድካሙ፣ ለጥረቱና ለሚከፍለው መስዋዕትነት የሚጠይቀውን ዋጋና የሚጠብቀውን ማካካሻ ከፍ ያደርግለታል።

ሙራድ እንደመጣ፣ ንጉሡ፣ የጆን ባፕቲስትን የኤምባሲ ስራ ሙሉ በሙሉና በቀላሉ እንዲገነዘበው አደረጉ። በርግጥ የፍቅርን ጉዳይ አላነሱም። ይህን አስቸኳይ ጉዳይ ለመቀበልና ለመፈፀም ያለውን ዝግጁነትም ጠየቁት።

ሽማግሌው፣ በክፊል የንጉሡ ነገስቱ የአደን እቃ በሆነውና አንፀባራቂ ሱል ከተለበጠ ወንበር ላይ ተቀምጦ አዳመጠ። አቀማመጡ በጉን ሆኖ፣ ክርኑ ላይ ተደግፎ፣ አይኖቹን በከፊል ጨፍኖ ነበር። በዚህ ጊዜ ከታችኛው ቅንድቡ በስተጀርባ ባሉት የነጡ አይኖቹ አጮልቆ ሲመለከት፣ በራሱና በንጉሡ መካከል ልዩ ንቃት ኖሯቸው፣ ወደ ኋላና ወደፊት እንዲንከባለሉ እያደረገ መሆኑን ጆን ባፕቲስት ተሰማው። ወጣቱ ሰው ግን፣ ንጉሡ እየገለፁት ያሉት ጉዳይ አንዳችም ማስመሠል የሌለበት እጅግ ከፍተኛና ጠቃሚ ጉዳያቸው መሆኑን ለመግለፅ ተቁነጠነጠ። የንጉሡ ንግግር ቀዝቀዝ እያለ ሲመጣ፣ ሙራድ በተቆራረጠ የሕመም ስሜት ድምፅ ተናገረ።

«ግርማዊ ሆይ! ይህ ድንቅ ሃሣብ ነው። ነገር ግን ሄሮዱቱስ እንደተናገረው የማሰንቆ መምቻ እንደተጠቃሚው ነው። ሲያስፈልግ የሙዚቃ መሣሪያ ይሆናል። አለበለዚያ የጦር መሣሪያ ይሆናል። በተመሣሣይ መልክ ይህ እጅግ ታላቅ የሆነ አዲስና አስቸጋሪ እቅድዎ በአተገባበሩ ላይ ተመስርቶ በጭራሽ የተለየ ውጤት ያስገኝ ይሆናል።»

ይህ የሙራድ የተለመደ የአነጋገር ስልት ነው። አንድ ጦረኛ ሊመታው የሚፈልገውን ሰው፣ ከጋሻው በስተጀርባ ራሱን ደብቆ እንደሚቀርብ ሁሉ፣ ሙራድም እውነት ይሁን የፈጠራ



የግሪክ ፈላስፎችን ምሣሌ እንደሸፋን ሳይጠቅስ የራሱን አስተያየት ጨርሶ ሰጥቶ አያውቅም። ንጉሱ ቀሪውን ለመስማት ጠበቁ።

«በመጀመሪያ» አለ ሙራድ፣ ፍፁም በደከመ አኳኋን፣ «ግርማዊነትዎ በፅሁፍ አንዳችም ነገር ማስፈር የለብዎትም። በምዕራባውያን ዋና ከተማና በዚህ መካከል ያለው መንገድ ረዥም ነው። ደብዳቤዎ ባልሆነ ሰው እጅ ወድቆ ያለአግባብ ሊጠቀሙበት የሚችሉበት ዕድልም በጣም ሰፊ ነው። ሌላው ቀርቶ እዚሁ አገር ውስጥ፣ እርስዎ ከፈረንሣይ ንጉስ ጋር ኤምባሲ መጠየቅዎን ቀሣውስቱ ቢያውቁ፣ ሊፈጥሩ የሚችሉት ትልቅ ችግር ይኖራል። ወይም ደግሞ በጉዞው ላይ ደብዳቤው ቢጠፋና በማይገባው ሰው እጅ ቢወድቅ፣ ቱርኮች በርስዎ ሃሣብ ላይ መጠንቀቅ ይጀምራሉ። ሰር ፖንሴም፣ ርስዎ ፈላጭ ቆራጭ የሆኑበት ፍጡርዎ ተደርጉ ይገለፃል። በመጨረሻም መታሰብ ያለበት የፈረንሣይ ቤተመንግስት አለ። ጀስዊቶችን፣ ብልጣብልጥ ክርክራቸውን፣ አንድን ሰው እውነት ያልሆነውን ነገር እውነት ነው ብሎ እንዲቀበል የማድረግ ችሎታቸውን፣ ቅንነት የጐደለውንና ሽፍጥ የተሞላውን አስተሣሰባቸውንም እርስዎም ያውቃሉ። በርስዎ ግምት ፍፁም ጉዳት የሌትም የምትባል አንዲት ቃል፣ በነርሱ ተጠምዝዛ የነርሱን መገኘት የምትጠይቅ ሊያደርጓት ይችላሉ። ወይም ደግሞ ለርም የታማኝነት መግለጫ ያደርጓታል። ወይም ማንኛውንም እነርሱ የሚፈልጉትን ያደርጉታል። በአጭሩ አንዳችም ነገር በፅሁፍ አያስቀምጡ»

«እንግዲያው እንዴት መቀጠል እችላለሁ?» ሲሉ ይህን ሁሉ ቆመው ሲሰሙ የነበሩት ንጉሱ እጃቸውን ወገባቸው ላይ ወደኋላ አሣርፈው ጠየቁ።

«አባትዎና አያትዎ እንዳደረጉት፣ እርስዎ ራስዎም ብዙ ጊዜ ሲያደርጉ እንደነበረው»

«ሰር ፖንሴን እጅበ የሚሄድልኝ መልዕክተኛ» አሉ የሁሉም የበላይ «አንተ ያልከውን ዘዴ ለመከተል ፈልጌአለሁ። ግን ማን ይሁን? አንተው ሙራድ?»

«ግርማዊነትዎ ይህን የሚጠይቁኝ ለደጉነቱ ቢሆንም፣ ይህ ለእኔ ታላቅ ክብር ስለሆነ አመሰግንዎታለሁ። ግን እንደሚያውቁት ሞት በከፊል መትቶኛል። ትዕግስት ስለነበረኝ ሞትን አጉንብሼ አሣለፍኩትና አመለጥኩት። ሆኖም ግን በድጋሚ የሚመታኝ ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን አስባለሁ። ይህም ለመጨረሻ ጊዜ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ።»

«እንግዲያው ማን ይሁን?» ሲሉ ንጉሡ ጠየቁ። «ሃጂ አሊ ንቃቱንና ጠንቃቃነቱ በመሃመዳውያን መካከል ነው። እንዲህ ያለውን ተልዕኮ መወጣት አይችልም»

ከተገቢው በላይ የገንዘብ ዋጋ ከሚጠይቀው ከሀጅ አሊ ጋር ተመልሶ እንደማይገዝ ሲያውቅ፣ ፖንሴ እፎይታ አገኘ። ዞር ብሎ ሜትር ዣርሚን ተመለከተው። ከድንኳኑ በስተኋላ በፀጥታ ከተቀመጠበት ሆኖ አጠገቡ እንዲመጣ ጆን ባፕቲስት ጠራው።

«ማይሌ ወጣት አቢሲኒያውያን መሣፍንቶችን እንደሚፈልግ ረሣህ እንዴ?» አለ ፕሮቴስታንቱ ዝቅ ባለ ድምፅ።

«ለዚህ የሚሆን ቅንጣት ዕድል እንኳ የለም። ቢሆንም እጠይቃለሁ።»

ጆን ባፕቲስት ወደ ንጉሡ አጠገብ ተመለሰ

«ከጨዋ ቤተሰብ የሆኑ ብዙ ወጣት ኢትዮጵያውያን ቢካተቱ ግርማዊነትዎ ምን ይላሉ። እነዚህ ወጣቶች ከጉዞው ብዙ ነገር ሊጠቀሙ፣ ፈረንሣይ ወስጥ ሊማሩ፣ ቋንቋችንንም እንዲሁ ተምረው የርስዎንም ቋንቋ ለኛ ምሁራን ሊያስተምሩ ይችላሉ።»

«አብደሃል እንዴ» አሉ እያሱ «በጐረቤቶቻችን ሣይገደል ይህችን አገር ለቅቆ መሄድ የሚችል አቢሲኒያዊ ክርስቲያን የለም። ደግሞም ጉዳዩ በምስጢር የሚያዝ መሆኑን አትርሣ»

እርሱም ልሞክር ብሎ ያቀረበው ጥያቄ ነበርና ይህን ክርክር ፖንሴ በቅፅበት ተቀበለው።

እንደገና በዝምታ ሃሣብ ውስጥ ለጥቂት ጊዜ ቆዩ።

«ዲሚጥሮስ?» አሉ ንጉሡ በፍጥነት፣ አስተርጓሚያቸውን ተመልክተው

«የለም፣ የለም፣ እርሱ እዚህ እጅግ ጠቃሚ ሰው ነው» ሲል ሙራድ ተቃወመ።

መልሱን ትንሽ በትንሽ በፍጥነት ቢለቅቀውም የድካም መንፈስ እንዳለበት ይታወቃል። ሽማግሌው ሰውዬ ዕፖ አድርጐ ሊያቀርበው የፈለገው ሰው እንዳለውና፣ ንጉሰ ነገስቱንም ቀስ በቀስ ወደዚያው ሊያመላክታቸው እንዳሰበ ጆን ባፕቲስት ተረዳ።

የሁለት ወይም የሦስት ሰዎች ስም እንዲጠቀስ፣ ሙራድ ጊዜ ሰጠ። ይሁንና የተጠሩት ሁሉ ወዲያውኑ ተሰረዙ። በመጨረሻም ሆን ተብሎ ፀጥ ከተባለ በኋላ፣ አርመናዊው እንደማፈር ብሎ ጉሮሮውን አጠራ።

«መቼም ሁል ጊዜም የእህታችን ልጅ አለ . . .?

«ምን አይነት የእህት ልጅ ነው የምትለው? እህትህ ብዙ ልጆች እንዳሏት አውቃለሁ። ሁሉም ሴቶች ይመስሉኛል»

«ወንድ ልጅም አላት። እንደኔው ስሙ ሙራድ ነው። ይህ ብዙም እንደማይስማማ ይገባኛል። ምንም እንኳ አርባ አመት ቢሆነውም እርስዎን ደስ ካለዎት፣ ሙራድ ወጣቱ ብለን እንጠራዋለን። ያደገው አሌፖ ውስጥ ነው። ግርማዊነትዎ ምናልባት ያውቁ እንደሆን፣ ዋርሣዬ



በዚያ አገር ለጥቂት ጊዜ ሲነግድ ነበር። የርሱ ሚስት፣ የእኔ እህት፣ ከአስራ አምስት አመት በፊት ወደዚህ ተመለሰች። ከባሏ ጋር በጭራሽ ልትስማማ ስላልቻለች ነው። በባህላችን መሠረት አባትዬው ልጁን ከራሱ ጋር አቆየው። ወይ ጉድ! ልጁ ካለው ድንቅ ችሎታ ሌላ ስለመናገር ፈልጌ አይደለም። ግርማዊነትዎ ሃሣቡን የሚቀበሉኝ ከሆነ ልጁ ምግብ አዘጋጅ ሆነ።»

«እና ታላቁን ንጉስ እንዲጠይቅ የምትልከው ይህን ሙራድ ነው?»

«ግርማዊነትዎም በሚገባ እንደሚያውቀው፣ ተመራጭ መልዕክተኞች ትሁቶች ናቸው። ምክንያቱም ማንም ሳያስተውላቸው ያልፋሉ። በርግጥ በጣም የሚያስፈልገው ፈጣን አሣቢ መሆንን ነው። ዋርሣዬ ደግሞ በምንም መልኩ ዘገምተኛ አይደለም። እንደሚታወቀው ዓይነት ተራ ምግብ አዘጋጅ አይደለም። ለአንድ ታላቅ ክርስቲያን ነጋዴም አገልግሏል። ጥቂት ቋንቋዎችን ተምሯል። ከነዚህ መካከል የፈረንሣይኛን መሠረተዊ ነገሮች ማወቁን አምናለሁ። ባለፈው ዓመት ተመልሶ ሲመጣ በጣም ተሻሽሎ ስላገኘሁት ደንቆኝ ነበር። ግርማዊነትዎ ራስዎ እርሱን የማየት ዕድል ስለሚኖርዎ እኔ ብዙ ባልናገር ይሻላል። ከሁለት ቀናት በፊት ጣና ሃይቅ ላይ አሣ ሊያጠምድ ሄዷል። አሣ ማጥመድን በጣም የሚወደው ሲሆን አበሣሠሉንም በሚገባ ያውቅበታል . . . እልክበትና ነገ ይገኛው እመጣለሁ።»

«በጣም ጥሩ» አሉ እያሱ ያለጉጉት፣ «እቀበለዋለሁ።»

ሽማግሌው መልዕክተኛ ትርፍ የሚያገኝበት መስሎት ስለገመተው፣ የራሱ ቤተሰብ አባል የሆነ ሰው በዚህ ተልዕኮ ላይ እንዲመደብ መፈለጉን ንጉሡ ተረድተዋል። ይህ ደግሞ ደንብ ነው። የንጉሡ አማካሪዎችም ትርፍ የሚያስገኝላቸው ካልሆነ በስተቀር ምንም አልፈየዱም። ይህንንም በደንብ ያውቃሉ። ከዚህም ባሻገር የራሣቸውን ፍላጐት ሲከታተሉ በንጉሡ ፍላጐት ላይ ሚዛናዊነት የሌለው ተግባር ለመፈፀም ወደኋላ የማይሉ ናቸው። እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ልክ እንደጀልባ ነው። የጀልባዋን አገልግሎት የተዋዋለው ሰው ጥቅም ሲያመዝን፣ ጀልባዋ ወደርሱ በኩል ታዘነብላለች። ጀልባዋን የሚያንቀሣቅሳት ሰው ጥቅም ሲያመዝን ደግሞ፣ ወደ ሌላው አቅጣጫ ተጋድላለች። ስለዚህ እንዳትሰምጥ በሁሉም አቅጣጫ ሚዛኗ እኩል መጠበቅ አለበት።

«መልዕክተኛ የማግኘት ችግር አሁኑኑ መፍትሔ የምንሻለት ጉዳይ ነው። ነገር ግን ይህ መልዕክተኛ ይዞት በሚሄደው መልዕክት ላይ ግርማዊነትዎ ወስኗልን?»

«በርግጥ» አሉ ንጉሡ፣ እንደገና በራስ መተማመን እየታየባቸው። በዚህ ርዕስ ላይ የሽማግሌውን ይሁንታ እንጅ ምክሩን አይፈልጉም። «ለንጉሡ ሰላምታዬን ያደርስላቸዋል። ይህ ሰላምታ አንድ ዜጋ ወይም ሎሌ የሚልከው ዓይነት ሳይሆን፣ አንድ ንጉስ እንደማዕረጉ

ለሌላ ንጉስ የሚልከው ቡራኬና ምስጋና ይሆናል። እኩያ ለእኩያ የሚልከው ዓይነት ይሆናል። ስለኒህ ስለሱዊስ ያወቅሁት ሃያል መሆናቸውን ነው። አልጋቸውና ዙፋናቸው በሰላም ተጠብቆ፣ ግዛታቸው በሰዎች ላይ እንዲስፋፋ እመኝላቸዋለሁ። በተጨማሪም፣ እድሜአቸው በሽምግልናው ውስጥ ቢሆንም መልካም ጤንነትንም እመኝላቸዋለሁ። ፍቅርና ደስታንም እመኝላቸዋለሁ። እነዚህን ምኞቶች መልዕክተኛው ሲገልፃቸው የእኩልነት ደረጃችንን በግልፅ ማሳወቅ ይኖርበታል። መልዕክተኛው፣ የንጉስ ሰለሞንና የንግስት ሣባ ልጅ፣ የምኒልክ ተወላጅ፣ የነገስታት ንጉስ፣ የላይኛው ኢትዮጵያና የታላላቅ ንጉሦች ንጉስ፣ የታላላቅ አገሮችና ግዛቶች፣ የሸዋ ንጉስ፣ የከፋ ንጉስ፣ የጋፋት ንጉስ ፣የእንጐት ንጉስ ወዘተ. . . መልዕክተኛ መሆኑን ይናገራል። መልዕክተኛው ከዚህ ከመልቀቁ በፊት እነዚህን ሁሉ አንድም እንኳ ሳይስት፣ ክብራቸውንና ማዕረጋቸውን ማወቁን እኔው ራሴ እነግረዋለሁ። ከዚህ በኋላ ሰላማችንን የሚያደፈርሱ ካህናት ከእንግዲህ በኋላ ከሮም እንዲመጡብን እንደማንፈልግ ለንጉስ ሉዊስ ይናገራል። በዚሁ ጊዜ እኛ ለነዚህ ካህናት በመርህ ደረጃ ምንም ዓይነት ጥላቻ እንደሌለን፣ እንዲያውም በቅድሚያ እጆቻችንን ዘርግተን በደስታ እንደተቀበልናቸውና እነርሱ ግን መስተንግዶችንንና እምነታችንን እንዳዋረዱብን፣ ንጉሡ እንዲያውቁ አድርጐ ይናገራል። በርሣቸው በኩል የእጅ ባለሙያተኞችንና ሠራተኞችን እንዲልኩልን፤ ምክንያቱም የርሳቸው አገር ባለእጆች በጣም ጥሩ ጥበበኞች ስለሆኑ፣ ሠዓሊው ብራንካሊዩን በቀድሞው ጊዜ ዘወድ በመድፋት ላይ ለነበረው ንጉስ ክብር ሲል ቤተክርስቲያኖቻችንን እንዳስጌጠልን ሁሉ፣ ዋና ከተማችንን ያስጌጡልናል። በመጨረሻም ታማኝ ዜጋቸው የሆነውን የፖንሴን ልጅ፣ ሰር ጆን ባፕቲስትን በመንግስቴ ውስጥ የርሳቸው አምባሣደር አድርገው ቢያስቀምጡልኝ በአገሬ ውስጥ ያለውን ሥልጣኔንና እድገት ለርሣቸው ሊያሣውቅ፣ በርሣቸውም አገር ያለውን እንዲሁ ለኔ በየጊዜው ሊያሣውቀኝ እንደሚችል ይናገራል። መልዕክቴ ይኸው ነው። ይህ የአቤቱታ አቀራረብ ሳይሆን አንድ የሁሉም የበላይ የሆነ እኩያውና ወንድሙ ለሆነ የበላይ የሚልከው ሰላምታ ነው። በዚህ ውስጥ አንድም የሃይማኖት ጉዳይ አይጠቀስም። ምክንያቱም ማንም እንደሚያውቀው ሁለታችንም በክርስቶስ እናምናለን። ይህ እውነታ ደግሞ ሊያስተባብረን እንጂ ሊከፋፍለን አይገባም። ከዚህም በላይ ከነዚህ መንፈሣዊ ፀቦች የምናተርፈው እሰመኖሩ ብቻ ሳይሆን ይህ ጉዳይ የነገስታት ጉዳይ እንዳልሆነ እምናለሁ።

«እና ምን ገፀ በረከት ይልኩላቸዋል?» ሲል ሙራድ ጠየቀ

«ገፀ በረከት? በዚህ ሁኔታ ውስጥ ጠቀሜታ አላቸው?»



«ግርማዊ ሆይ፣ እንደ እኩያ አነጋግራቸዋለሁ ብለው በአንደበትዎ የነገሩን እርስዎ ነዎት። አንድ ታላቅ መስፍን፣ በራሱ ግዛት ውስጥ ላለ ሌላ መስፍን ሰላምታ ሲልክ ምን ያደርጋል? ታላቅነቱንና ክብሩን የሚያሣዩለት ስጦታዎችን በማድረግ እርሱ ግን ምንም እንደማይሻ ያሣየዋል።»

«ትክክል ነህ ሙራድ» አሉ ንጉሡ። «ለኛ አለም ልዑላን የምንሰጣቸውን ዓይነት ገፀበረከቶች አዘጋጁ። ፖንሴ በጣም በትንሹ በምናውቀው በምዕራቡ ዓለም ይበልጥና በተለይ የሚወደደው ምን እንደሆነ ንገረን፣ ይህ ያንተ ሥራ ነው»

እነዚህን ተናግረው፣ ንጉሡ እንግዶቻቸውን አሰናበቱ። ሙራድ በእጅጉ ሊያተርፍበት የሚችለውን ስምምነት በተሣካ መልኩ ስለፈፀመው፣ የተፈጠረበትን የደስታ ስሜት ለመደበቅ ሲል እያቃሰተ ወደ አልጋው ተመለሰ።

ከሁለት ቀናት በኋላ ሙራድና ወጣቱ ሙራድ መጡ። አጐቱ ብቻ ባለበት፣ ከንጉሡ ጋር በምስጢር ተገናኙ። ከዚህ በኋላ ራሱን ከፖንሴና ከሜትር ዡረሚ ጋር አስተዋወቀ። ሰውዬው፣ ግዙፍ በርጫም ሲሆን፣ ጉንጮቹ በተሰየ መልክ ፍም ስለሚመስሉ፣በሃይል በጥፊ የተመታና ምልክቱ ሣይጠፋ የቀየበት ይመስላል። የኩርዶችን ወይም የፋርሳውያንን የአለባበስ ዘዴ ተከትሎ ለብሷል። ረዥሙ እጀ ጠባቡ ቁርጭምጭሚቱ ላይ ሲደርስ በጣም እየጠበበ የመጣውን ባጊ ሱሪውን ሸፍኖበታል። ሰፋት ያለው የጨርቅ ቀበቶ ወገቡ ላይ ጠምጥሟል። በተላጨው ራሱ ላይ ቢጫ የሃር ጥምጣም አድርጓል። እነዚህ ሁሉ ጨርቆች ግን የዘይት ጠብታዎች ነጠብጣብ አለባቸው። ይህ ማለት፣ ሰውዬው ንፅህና የሌለው ነው ማለት አይደለም። ነገር ግን በጣም ከመንገብገቡ የተነሣ፣ ልብሱን እንኳ እስኪለውጥ ስለአላስቻለው ምግቡን መንጭቆ እየተስገበገበ ሲውጥ፣ ዘይት በልብሱ ላይ ስለተንጠባጠበበት ነው። ሙራድና ወጣቱ ሙራድ በአለባበሱ ላይ የወሰዱት ጥንቃቄ፣ ምግብ በጭራሽ የተረፋቸው አያስመስላቸውም። ምንም ነገር ለማክናወን ሌላው ቀርቶ መሃረቡን ዘርግቶ እንኳ ከንፈሮቹን ለመጥረግ አልሞከረም።

የአለባበሱ እንክን፣ አሉታዊ ስሜትን ይናገራል። ይሁን እንጅ ማራኪ ፊት አለው። ከረዥም ዘመን በፊት የነበረው የልጅነት የደስደስ ፊቱ፣ በወፍራሙ ፊቱ ውስጥ ተጠብቆ የቆየ ይመስላል። የፊት መሸብሸብም በፋፋው ሥጋው ላይ ምንም መስመር አልሠራም። ጢሙን እንዲያድግ ቢተወውም በሰርጓዳ ጉንጮቹ ላይ ሁለት የመጠባበቂያ ፂሞች መስለው ይታያሉ። ፈረንሣውያኑ ከመጀመሪያውኑ በዚህ ሰው ላይ አንድ የሚጠቅም ነገር አዩበት። አሁን

በሚታየው ዓይነት ሙራድ ወጣቱ፣ የትም ቦታ ቢሆን ትኩረት ሳይስብ ሊሄድ ይችላል፡ የሚናገረው በትክክል ፈረንሳይኛ ሳይሆን በምስራቅ ሜዲትራኒያን የሚገኙ ነጋዴዎች የሚጠቀሙበትን መሰል የሰሽ ቅይጥ ቋንቋ ነው። ሌላ የተሻለ አምባሣደር በርግጥ ማሰ[illegible] ይቻላል። ይሁን እንጅ ይህኛው ጥሩ የጉዞ ጓደኛ፣ ምስጢር ጠባቂና ጥሩ ምግብ አብሣይ ሊሆ[illegible] ይችላል።

ጆን ባፕቲስት ከሁሉም በላይ የሚያሣስበው ጉዳይ በማንኛውም መልኩ ፈጥኖ መልቀቁ ነው። በመንገዳቸው ላይ ዋናዎቹን መሰናክሎች ሁሉ አልፈዋቸዋል። በመመለስ ላይ የሚኖረው ችግር እምብዛም አላሳሰበውም። ይህን ጊዜ ካይሮ በሆነኩ ብሎ አሊስን ባለማቋረጥ ያስባታል። አዕምሮው ውሃ በማያሳልፈው ጓዳው እርሷን ብቻ በማሰብ ተወጥሯል። በጉዞው ጊዜ በጣም ርቀት ላይ በመሆኑ ተስፋ ሳለመቁረጥ በመወሰን፣ ስለርሷ አብዝቶ ላለማሰብ ተጠንቅቆ ነበር። አሁን ግን መልኳና ቁመናዋ በአዕምሮው ውስጥ በግልፅ ይታዩት ጀመር። ዳግመኛም በቅርቡ እንደሚያያትና ታላቁን የኤምባሲ ዜና ሲያበስራት ታየው። ጆን ባፕቲስት ይህን ሁሉ የሚያልመው ለመመለስ ጓዙው እየተዘጋጀ ሣለ ነው። ችግሮች፣ እርግጠኛ ያለመሆን ሁኔታዎችና አንድ ሺህ አንድ የሚሆኑ ብዙ ሥራዎችና ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች፣ እርሱ በትዕግስት እንደሚጠብቃት ሁሉ እርሷም መመለሱን በናፍቆት እንደምትጠባበቅ ለአፍታ እንኳ አይጠራጠርም። በፍቅር መጀመሪያ ላይ ምንም ነገር እርምጃውን ቢያዘገየው ይመግበዋል። ምንም ነገር በተቃውሞ ቢነሣበት ወኔና ብርታት ይሰጠዋል። እነዚህን ሁለት ፍቅረኛሞች ለጥቂት ቀናት ከተገናኙ በኋላ እንዲለያዩ ካደረጋቸው አስገዳጅ ሁኔታ ሌላ ተቃራኒ ነገር ማሰብ ይከብዳል። ተፃራሪ የሚመስለው የሁለቱን ስሜት እንዲህ እንዲጠነክር ለማድረግና ጥርጣሬን አሽቀንጥሮ ለመጣል፣ ሌላ ነገር ይህን ያህል አይሠራም ነበር።

ወደ ቤት የመመለስ ሃሣብ አጥብቆ ስሜታቸውን ያነሣሣው ጆን ባፕቲስትና ሜትር ዠሪሚ፣ ንጉስ ነገስቱ ለዘመቻ ሊወጡ በተዘጋጁበት ጊዜ እነርሱም ዝግጅታቸውን አጠናቅቀው ቅፍለታቸውን ሰብስበው አደራጁ። ከነርሱና ከወጣቱ ሙራድ ሌላ አስር አቢሲኒያውያን ባሮች ነበሩ። ንጉሡ፣ ለወጣቱ ሙራድ ብዙ ዓይነት ዕቃዎችንና ትጥቆችን ሰጥተውት ነበር። ከነዚህም መካከል የክብረ በዓል ልብሶች ሲገኙባቸው፣ በአጠቃላይ ሁለት ሻንጣ ሙሉ ሰጥተውታል። አስሩ ጥቋቁር ሰዎች ግማሽ ሰውነታቸውን እርቃናቸውን የነበሩ፣ፀጉራቸውን በዛጐል ሹሩባ የተሠሩ፣ ሁሉም በጦርነት የተያዙ፣ ስድስት ወንዶችና አራት ሴቶች ነበሩ።



ወጣቱ ሙራድ፣ የተልዕኮው ዝርዝር የሌለበት፣ በአጐቱ ተዘጋጅቶ በንጉሠ ነገስቱ የተፈረመና ብዙ የመንግስት ማህተሞች ያረፉበት፣ ተለይቶ የተገለፀ ተቀባይ ያልታወቀበት፣ በአጭሩ አርመናዊው የንጉሡ የመንግስት መልዕክተኛ መሆኑን የሚገልፅ አጥር ምጥን ያለ ደብዳቤ ይዟል። ለፈረንሣዩ ንጉስ የሚያቀርበውን መልዕክት ግን በጥንቃቄ ከልቡ አጥንቷል። ባሮቹ በጉዞው ላይ መንገደኞቹን ያገለግላሉ። በጉዞው መጨረሻ ላይ፣ ሉዊስ ለሚባለው ለንጉስ ሉዊስ አስራ አራተኛ ልጅ በስጦታ ይቀርባሉ። ሌሎች ስጦታዎችም እንዲሁ ነበሩ። ከነዚህም መካከል አምስት ፈረሶችና በከባድ ሰንሰለት እንዲቆራኙ የተደረጉ ሁለት ኮርማ ዝሆኖችም ነበሩ። ሦስት ሣጥን ሙሉ የጥርኝ ዝባድ፣ ትንባሆና የወርቅ አፈር ከስጦታዎች መካከል ነበሩ።

ፈረንሣውያኑ ሐኪሞች በበኩላቸው፣በቆይታቸው ጊዜ የሰበሰቧቸውን ወርቅ፣ የከበሩ ድንጋዮች፣ ቆዳ፣ የገዘፈን ጥርስ እና ሌሎችም ታካሚዎቻቸው፣ ከነዚህም መካከል የንጉሠ ነገስቱ የልፍኝ አስከልካይ በክፍያ መልክ እንዲቀበሏቸው የለመኗቸውን፣ ዕቃዎች የሚጭኑባቸው ሁለት ፈረሶች ያስፈልጓቸው ነበር። በቆይታቸው ወቅት የሰበሰቧቸውን የደረቁ ዕፅዋት፣ ሥራስሮችና ፍሬዎች ሰፊና በጣም ቀላል በሆነ ስልቻ ውስጥ አድርገው የሚጭኑበት አንድ አህያ ነበራቸው። ለንጉሡ የሚያገለግል ብዙ ብልቃጥ መድሃኒት፣ ከነሕክምና መመሪያው ለዲሚጥሮስ አስቀመጡለት። ምንም እንኳን ንጉሠ ነገስቱ ለጊዜው የዳኑ ቢሆኑም ሕመሙ ግን ተመልሶ መምጣቱ አያጠራጥርም።

በቆይታቸው ወቅት በከተማዋ ከሚኖሩ ብዙ ሰዎች ጋር ተዋውቀው ስለነበር፣ ተሠነባብተው እስኪነሱ ሦስት ቀናት ፈጀባቸው። ጆን ባፕቲስት፣ ሃሣቡ ሁሉ በሚወዳት ልጅ ላይ ስለነበረ ከተዋሸማቸው ሴቶች የቀረቡለትን ስጦታዎች በተቻለ የትህትና መጠን ሣይቀበል ቀረ። በተለይም በመጨረሻው ምሽት ይህን ዓይነቱ ስጦታ በጣም ብዙ ነበር። ስለዚህም ሜትር ዠሪሚ ሁለቱንም ወክሎ ሲሰራ ነበር።

መድረሱ አይቀርምና የመጨረሻው ዕለት ደረሰ። የበጋው ወቅት እየተገባደደ ስለነበር የደመና ቁልል በምሽት ሰማይ ላይ ያንዣብባል። ተጓዦቹ፣ ከንጉሡ ጋር መጀመሪያ በተገናኙ ብት የቤተመንግስቱ አናት ዘብ ክፍል ውስጥ ለመጨረሻ ጊዜ ሊወያዩ ተገናኙ። ንጉሡ፣ እንደ ወንድሞቻቸው አቅፈዋቸው ሳሙ። ሁልጊዜም እግዚአብሔር እንዲጠብቃቸውና በፍጥነት መልሶ እንዲያመጣቸው እንደሚለምኑትም ነገሯቸው።

«እንካችሁ» አሉ ለእያንዳንዳቸው የእጅ መዳፍ የሚያክልና የይሁዳ አንበሣ ምስል መሀሉ ላይ የታተመበት የወርቅ ሜዳሊያ እየሰጧቸው። «እንደማታምኑበት አውቃለሁ። ነገር ግን በነዚህ ውስጥ ከቁሣዊ ሃብትነታቸው ይበልጥ ጥቂት ነገሮች አሉባቸው»

ንጉሡ የወርቁን ሰንሰለት በጆን ባፕቲስት አንገት ላይ በራሣቸው እጅ ካጠለቁለት በኋላ አቀፉት። በተመሣሣይ መልክ ለሜትር ዠረሚም አደረጉና ወዲያውኑ ተለዩዋቸው።

የዚያኑ ዕለት በርቀት በህዝባዊ ስብሰባ ላይ እንደገና ንጉሡን አዩዋቸው። እንደቀሣውስቱና መሣፍንቱን ከሆነ፣ ተጓዦቹ ንጉሡን በግል ማየት አይፈቀድላቸውም። ይሁን እንጅ ውስጡ ምስጢርነቱን ሁሉም ያውቃሉ።

ሁለቱም ፈረንሣውያን ዙፋኑ ወደተዘጋጀበት የቤተመንግስት ግቢ ተወሰዱ። ከንጉሰ ነገስቱ ጥቂት እርምጃዎች ፈቀቅ ብለው አራት አንበሶች በጉጆአቸው ውስጥ ሆነው ያቃስታሉ። እንደሁልጊዜውም፣ ንጉሠ ነገስቱ ንቅንቅ ሳይሉ በአፈ ንጉሣቸው በኩል ይናገራሉ። ፖንሴና ሜትር ዠረሚ በግንባራቸው መሬት ላይ ተደፍተው ሰገዱ። ግንባራቸውን የገጨው በመንገዱ ላይ የተነጠፈው ጉርበጥባጣ ድንጋይ መጀመሪያ ሲመጡ በጣም ቀዝቃዛ ከነበረው ቢለይም ተመሣሣይ ስሜት ነበረው። ልዩነቱ እምብዛም በማይታወቅበት ምድር፣ ከሠማይ በታች ተቀራርቦ የተነጠፈው ጥቁር ድንጋይ፣አፈሩ ወይም ድንጋዩ ከእንግዲህ በኋላ በከፊልም ቢሆን የነርሱ ነው። ከንጉሠ ነገስቱ ዘንድ የቀረቡበት ጊዜ ትንሽ ረዘም ሲል፣ ቀሣውስቱም፣ ተጓገሮቹ ረዘም ላለ ጊዜ እንደሰገዱ ቢቆዩ ጥሩ እንደሚሆን አሰቡ። ሲነሱ ግን ሁለቱም ሰዎች እያንዳንዳቸው መሬቱን በስሱም ቢሆን እንዳወረዙት ይህም በእንባቸው እንደሆን አስተዋሉ።

ሠላሣ ፈረሰኛ ወታደሮች ከከተማው ጀምሮ የአምስት ቀን ጉዞ እስከወሰደባቸው አክሱም ድረስ አጀበዋቸው ተጓዙ። እንደደረሱም፣ ከወጣቱ ሙራድና ከቀሪው ቅፍለት እንዲሁም ዝሆኖች ጋር ተቀላቀሉ። እስከ ንጉሠ ነገስቱ ግዛት ወሰን ድረስ በቁጥር ሰባት ወንዶች ያሉበት ቀላል አጃቢ ኃይል ይዟቸው ሄደ። ከዚያም አክሱምን ለቅቀው ወደ ቀይ ባህር ጠረፍ ተጓዙ።



# 3

# የሹመት ደብዳቤው

# 1

ዲፕሎማሲ ጥበብ ነው፡፡ ጥበብ ሲባልም ርጋታን የሚጠይቅ ጥበብ ነው፡፡ ሁልጊዜም ያልተቋረጠ ክብር የሚጠይቅ ጥበብ ነው፡፡ ለአረማመድ እንኳ ግርማ ሞገስ የሚሻ ጥበብ ነው፡፡ ስለዚህ ከጥረት ጋር፣ ከድካም ጋር፣ ከጥድፊያ ጋር የሚጣጣም አይደለም፡፡ በአጭሩ ወይም በሌላ አባባል ከስራ ጋር የሚስማማ አይደለም፡፡

ሙሴ ዱ ማይሌ፣ አንዳችም የሚሠራው ነገር ባልነበረውና ራሱን ሙሉ በሙሉ ለስራ ማዋል ይችል በነበረበት እንደነዚያ ጊዜያት ሳይሆን፣ እንደአሁኑ አስተዋይ ዲፕሎማት ሆኖ ሥራውን አከናውኖ አያውቅም፡፡ ማንም ሰው፣ ወኔ ኖሮት ስለዚያ ጊዜው ህይወቱ ሊጠይቀው ቢችል በምስጢር ተሸፍኖ፣ በማጣት ሸትቶ ይኖር ከነበረበት ደረጃ ተነስቶ፣ ራሱን የመንግስት ባለሟል ማድረግ የቻለ ሰው መሆኑን ይረዳል፡፡ የመልዕክተኞቹ ቡድን ወደ አቢሲኒያ ከሄደና ከካህናቱ መጥፎ ሴራ በኋላ፣ ቆንሲሉ የተለመደውን የመንግስት አገልግሎቱን ቀጠለ፡፡ ጥቂት ዘግይተው በደረሱት ጋዜጦች ላይ፣ ከሥራ አቻዎቹ አንዳንዶቹ አዲስ የስልጣን ደረጃ እንዳገኙ ያነበበውን ወደጉን በመተው የራሱንም ህጋዊ የጉጉት አቅጣጫ ማመላከት የሚችልበትን ዘዴ መፈለግ ጀመረ፡፡ በመጨረሻም፣ ከርሱ በፊት ተወስኖ በነበረ ትዕዛዝ መሠረት ብዙ የቱርክና የአረብ ሰዎችን ጉበኘ፡፡ ለነዚህ ሰዎች የሚነግራቸው አልነበረውም፣ ከነርሱም ምላሽ ለመስማት ደንታ አልነበረውም፡፡ ውይይቱ፣ ልክ የምስራቃውያን የቀረፃ ጥራት የብዙ ሺህ ተጓዦችን አይኖች እየማረኩ ግን አንዲትም ቅርፃቅርፅ ወይም መልክ ወይም ምልክት እንደማይቸሩ፣ እንዲሁ ያለ አንዳች ፋይዳ ይቋጫሉ፡፡

ይህም በስምምነት የዘለቀ ቆይታ፣ ፖንሴና ሃጅ አሊ ጉዞ ከጀመሩ በኋላ፣ በ1700 ግንቦት ወር መጀመሪያ ላይ ከፉኛ መሰናክል ገጥሞት ነበር፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው በሁለት ሣምንት ለድሜ ውስጥ ነው፡፡ በመጀመሪያ የክቡር ዱ ፖንቻርትሬይን ደብዳቤ የያዘ ፖስታ ከአሌክሣንደርያ ይመጣል፡፡ ቆንሲሉ ሳይረበሽ ለማንበብ ቢሮውን ቆልፎ ተቀመጠ፡፡ ደብዳቤው፣ በመደበኛው የሰላምታ አቀራረብ ጀምሮ ወደ ሌሎች ጥቃቅን ጉዳዮች ይሸጋገራል፡፡ ከዚህ በኋላ ሚኒስትሩ ርዕሱን ኢትዮጵያን ወደ ሚመለከት ጉዳይ ይቀለብሱታል፡፡ ሙሴ ዱ ማይሌ፣ ከደብዳቤው ውስጥ የሚከተሉትን አስደንጋጭ ዐረፍተ ነገሮች ያገኛል፡፡

*ወደ ኢትዮጵያ የጀመርከውን የመንግስት መልዕክተኞች ሥራ በተመለከተ የንጉሡን ሃሣብ የዘገቡልህ መልካሞቹ ጀስዊቶች፣ ምንም እንኳ ተመሣሣዮች ባይሆኑም ከራሣቸው ሃሣቦች ጋር ያምታቱት ይመስለኛል።*

*አቢሲኒያ፣ የቅዱስ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሥርዓት ውስጥ በተመሲጋኞቹ የየሱስ ማህበረሰቦች ጥረት መግባቷን ሲያውቁ፣ ግርማዊነታቸው ደስታቸውን መግለፃቸውን በጆሮዬ የሰማሁት ሐቅ ነው። ነገር ግን፣ ቬርሣይለስ ውስጥ የአቢሲኒያን ንጉስ መቀበል አልፈቀዱም ነበር። ከግርማዊነታቸው ጋር ዛሬ በድጋሚ ተመካከርን። እንዲህ ያለውን ኤምባሲ ለመቀበል ደስተኛ እንዳልሆኑ ላረጋግጥልህ እወዳለሁ። ምክንያቱም፣ ይህ አይነት ተግባር አሁን ያለውን የአውሮፖ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ከመቸውም በበለጠ ጥሩ ግንኙቱን ጠብቆ ማቆየት ሲገባ፣ የአቶማን ሡልጣንን የሚያስቆጣ ሊሆን አይችልም ማለት አይቻልም። ከደብዳቤህ እንደተረዳሁት መልዕክተኞችህ በሰላም ስለመመለሳቸው ልበ ሙሉ አይደለሁም። ነገር ግን፣ እነዚህ መልዕክተኞችህ ወደ ካይሮ የሚመለሱ ከሆነና ከኢትዮጵያው ንጉስ መልዕክተኞች ጋር ታጅበው የመምጣት ዕድል ካላቸው፣ እነዚህን ባለሙሉ ሥልጣን አምባሣደር የሆኑ ሰዎችን ወደ ቬርሣይለስ እንዳይገዙ እዚያው እንድታቆያቸው የራሴን አስተያየት እለግስሃለሁ። ለጥቂት ጊዜ አጠገብህ አቆያቸውና የሚያቀርቡትንም ምስጋና ተቀበል። ከዚያ በኋላ ከብዙ የምስጋና ጭነት ጋር ወደ ጌታቸው መልሰህ ላካቸው። ከዚህ ሌላ አይደረግም።*

እነዚህ አዳዲስ መመሪያዎች አንዳች ክፉ ነገር እንደሚመጣ የሚጠቁሙ ናቸው። ሙሴ ዱ ማይሌ፣ በገበታ ላይ እንኳ ትካዜና ሃሣብ ገብቶት ሲውል በተከታታይ ቀኖች በጉዳዩ ላይ ከሙሴ ማቼ ጋር ሲመካከር ሰነበተ። የዕቃ ማስቀመጫ በሆነችው ትንሽ ክፍል ውስጥ የሚሠራው ፀሐፊ፣ አሁንም፣ አሁንም በመጠራቱ ደስታ እየተሰማው ነው። በሚቀጥለው ሣምንት ደግሞ ሌላ አስደናቂ ሁኔታ ተከሠተ። አንድ አረባዊ ፈረሰኛ በፈጣን ግልቢያ እስከፈረንሣውያን ማሕበረሰብ መኖሪያ ድረስ ሽምጥ እየጋለበ ይመጣል። ያደረገው ቀይ ባርኔጣ በነፋስ ውስጥ እየተውለበለበ፣ ቆንስላው ግቢ ፊት ለፊት ሲደርስ ከፈረሱ ላይ ዱብ ብሎ ወርዶ፣ ለፈረንሣይ ተወካይ ደብዳቤ መያዙን ያስታውቃል። ቆንሲሉ በፖስታው ላይ አጥብቆ በተጠየቀው መሠረት፣ ደብዳቤውን ከመልዕክተኛ እጅ ላይ ራሱ ተቀበለ። ጥቂት ጥያቄዎች ካቀረበለት በኋላ፣ ደብዳቤውን ያመጣው መልዕክተኛ ሦስት ደረጃዎችን አልፎ በአረቢያን የባህር



ወሽመጥ በኩል ከጅዳ የመጣ መሆኑን አወቀ። መልዕክተኛው እንደደረሰ ሊከፈለው ይገባ ነበርና፣ በዋጋው ላይ እንዲከራከር ሙሴ ዱ ማይሌ ሃላፊነቱን ለፀሐፊው ሰጠው።

አዲሱ ደብዳቤ ዲፕሎማቱን ከመጀመሪያው የበለጠ መንፈሱን ረበሸው። በቤቱ ውስጥ ያለው አጠቃላይ እንቅስቃሴም ግራ ተጋባ። ስንፍናን ዱቄት ለማድረግ በሚገባ ተሟሽቶ የሰሰጠነው የቆንሲሉ ጭንቅላት፣ ዛሬ እፍኝ በማትሞላ የመታወክ ፍሬ መንሣጠጥና ማቃሰት ጀመረ። ማዳም ዱ ማይሌ፣ ባሏ እንደገና ጤናውን አደጋ ላይ እየጣለ መስሏት ተጨነቀች።

ከሁሉም ይልቅ የተጨነቀችውና ዜናውን የተራበችው በርግጥም አሊስ ነበረች። በነዚህ ሁሉ ረዥም ወራት ሁሉንም የስሜት ደረጃዎች በማቋረጥ፣ ከተስፋ ወደ መጨነቅ፣ ከዚያም መጥፎ ነገር ይደርሣል በሚል መሰቃየትና በመጨረሻም ገና ያልተከሰተ አስፈሪ ሁኔታ ይኖራል በሚል ተሰቃየች። በአሁኑ ጊዜ እጅግ አደገኛና ወደ ሞት ሊያደርስ ወደሚችል ደረጃ ራሷን እያደረሰችው ነው።

የሁለቱ መልዕክተኞች መድረስ፣ የአሊስ ትዕግስት የማጣት እና የጉጉቷን መጠን እንደአሣት የሚያቃጥል ትኩሣት ለቀቀባት። ሙሴ ዱ ማይሌ ግን አዕምሮውን የያዘውን ምስጢር ጉዳይ ለቤተሰቡ ላለመግለፅ ወስኗል። የመልዕክተኛው ቡድን ወደ አቢሲኒያ ሲንቀሣቀስ እድሮበት በነበረው ከመጠን ያለፈ በራስ መተማመን ሳቢያ፣ በቤቱ ውስጥ ተፈጥሮበት የነበረውን ምስቅልቅል ሁኔታ በሚገባ ያስታውሰዋል። በዙሪያው ያሉት ሰዎች ያቀረቡለትን የመጀመሪያ ጥያቄ ተከትሎ ምስቅልቅል ነገሮች ስላሉ፣ እንደ አይስተር አሣ ዝም፣ ዝግት ብሎ ያጉረመርማል።

በር ስር ተለጥፈው ለማዳመጥ ከፍተኛ ጥረት ከማድረጋቸው በስተቀር፣ አሊስና ፍራንቸይዝ የተሻለ ነገር ማወቅ አልቻሉም። በዚህም ሣቢያ መላምቶችን መደርደር ጀመሩ። አሊስ፣ መንንትና ፍቅር ስላለባት፣ የታሰባትና በርግጥም ያለማጋነን ያጋጠማት፣ በጆን ባፕቲስትና በተልዕኮው ላይ አንዳች አሰቃቂ ነገር ደርሷል የሚል ነው። ፍራንቸይዝ በመጨረሻ ላይ አንድ ሃሣብ እስከታመጣ ድረስ ተስፋ በመቁረጥ ምንም አይነት ዜና ላለመስማት ወስና ነበር።

«ቆንሲሉ ይህን በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሚያከናውኑት ስላልሆነ፣ ያለው ብቸኛ ነገር ምንነቱን መፈተሽ ነው» አለች

«ወደ ቢሮው መግባት? ይህ ፈፅሞ የማይሆን ነገር ነው» አለች አሊስ።

በፍራንቾይዝ ሥር ሆና በመቆየትዋ ወኔ ያሳት ወጣት ሴት መሆን ብትችልም፣ ትዕዛዝ የመጣሱ ሃሣብ ግን በእጅጉ አስፈራት።

«ይህ በጣም አስቸጋሪ አይደለም። በምሽት ወረቀቶቻቸውን ሁሉ ጠረጴዛው ላይ በትነው ነው የሚተውት። በሩም ቢሆን አይቆለፍም። ይህን፣ የመስኮቶችን መጋረጃ የሚለቀቀው ትንሹ ኑቢያዊ ነግሮኛል» አለች ፍራንቾይዝ

«ወደ ቢሮው መድረስ የሚቻለው በእንግዳ መቀበያው በኩል እንደሆነና ጠባቂው ደግሞ እዚያ ውስጥ እንደሚተኛ ረስተሻል ማለት ነው።»

«ታውቂያለሽ» አለች ፍራንቾይዝ በማታለል። «ወደ ቤታቸው መጀመሪያ በመጣሽ ጊዜ ለአባ ጋቦሪ የሰጠናቸው መጠጥ፣ ምናልባት ሙሉ በሙሉ ሊያስተኛቸውም ይሆናል በማለት ሜትር ዡረሚ ፈርቶ ነበር»

«እናስ?»

«እናማ ሌላ ጠርሙስ እኔ ዘንድ አስቀመጠ። ከዚህ ውስጥ ጥቂት ጠብታዎች በማንኛ ውም ፈሣሽ ውስጥ ቢጨመር፣ ምስኪኑ ሰው ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ውስጥ ስለሚገባ፣ አጠገቡ ቆመን እንኳ ድምፃችንን ዝቅ ሣናደርግ ብናወራ ሊያዳምጠን አይችልም። ያንን በቁሱ ላይ መጠቀም አልነበረብንምና አልተጠቀምንም። ይሁንና ጠርሙሱ አሁንም እኔ ዘንድ አለ።»

በማግስቱ ጧት ጠባቂው ዘበኛ የተቀሰቀሰው፣ አንድ ባሣ ውሃ በሸሚዙ ላይ ከተቸለሰበት በኋላ ነበር። ሙሴ ዴ ማይሴ፣ የአገሬው አገልጋዮች ጠጪ በመሆናቸው ከማማረር ሌላ ያለው አልነበረም።

እንደከ ትላንት በስቲያ ማታ በአምስት ሰዓት ድረስ ዘበኛው መተኛቱን እርግጠኛ ስትሆን፣ ፍራንቾይዝ በበሩ አጠገብ ሆና ስትጠብቅ፣ አሊስ ወደ አባቷ ቢሮ እየዳኸች በጠረጴዛው ላይ በተቀመጠው ቀይ የቆዳ ማህደር ላይ የሚኒስትሩን የዴ ፖንቻርትሬይን ደብዳቤ ለይታ አወቀች። የሰም ማህተሞቹና በወረቀቱ ላይ ጉላ ብለው ሲታዩ በውሃ ቀለም የተፃፉት ደብዳቤዎች አያሣስቱም። የወረቀቶቹን ቅደም ተከተል ለማስታወስ እየሞከረች በጥንቃቄ አነሣቻቸው። ለማንበብ እንኳ ስትሞክር፣ ዋናው ጉዳይ የሚገኘው ሌላ ቦታ ነው በሚል ወደጉን አስቀመጠችው። በጣም ርግጠኛ ሆና ሌላ ትንሽ ደብዳቤ ከስሩ አገኘች።



የመጀመሪያው ደብዳቤ ከሌሎቹ ደብዳቤዎች ሁሉ ጉላ ብሎና በግርማ ሲታይ፣ ይህኛው ግን ጉስቁልቁል በማለቱ ተጨማድዶ፣ ጫፉ አወይቦትና በቆሻሻ ጣቶች ምልክት የተበላሸ ነበር። አሊስ በጥንቃቄ አነሣችው። የተላከው ከጂዳ ሲሆን የፅሁፉ አጣጣል የጆን ባፕቲስት ነው። ወረቀቱን ወደ ደረቷ በሃይል አስጠግታ አቀፈችው። ለማንበብ ስትጓጓ ደረቷ ላይ ይዛው አቆየችው። ወረቀቱን ደረቷ ላይ አቅፋ ማቆየትዋ ጆን ባፕቲስትም ይህችኑ ወረቀት እንዲሁ እንዳደረጋት መሰሏት፣ እርሷም በርሱ እጆች ላይ የራስዋን ያስቀመጠች መሰላት። በመጨረሻም ልታነብበው ተበራታች። መጥፎ ሁኔታ ላይ ተከኖ በመቃ ብዕር ስለተፃፈ፣ በደብዳቤው ብዙ ቦታዎች ላይ የቀለም ነጠብጣቦች ቢኖሩበትም አጭርና በሚገባ ሊነበብ የሚችል ጽሁፍ ነው። የፅሁፉ አጣጣል ሽቅብ ወደ ቀኝ ዘመም ያለ ነው።

ክቡር ሆይ

*በአሁኑ ጊዜ ወደ ካይሮ በመመለስ ጉዞ ላይ እገኛለሁ። አባ ብሬቬዳንት፣ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ሳይደርሱ በመሞታቸው ሐዘን ቢሰማኝም፣ ወደ አቢሲኒያ የተደረገው ተልዕኮ ሙሉ በሙሉ የተሣካ ነበር። ከኔ ጋር ከንጉሡ የተላኩ አምባሣደር ይዤ እየመጣሁ ነው። ሰውዬው ለጥቂት ጊዜ ምፅዋ ላይ ቢዘገዩም፣ በአሁኑ ሰዓት ቀይ ባህርን እያቋረጡ ናቸው። ንጉሡ ነገስቱ፣ ለፈረንሣዩ ንጉስ የምናቀርባቸውን ልዩ ልዩ ገፀ በረከቶች ሰጥተውናል። በዚህ መሠረት አስር አቢሲኒያውያን ባሮች፣ ፈረሶች፣ ሁለት የዝሆን ጥርሶችና ሌሎችም ብዙ አሉ። ቡድናችን ተመልሶ ሲሰባሰብና የመጓጓዣ መርከቡን ስናገኝ ወደ ፖርት ሳይድ የምናደርገው ጉዞ ይጠብቀናል። ሁሉም ነገር በሰላም ከተከናወነ፣ በአንድ ወር ውስጥ ካይሮ እንደርሣለን። ለክቡርነትዎ ጤንነት እፀልያለሁ።*

«በአንድ ወር ውስጥ!» አለች አሊስ

በወረቀቱ አናት ላይ ቀኑ የተጫጫረበትን ቦታ ተመልክታ በፍጥነት አሰላችው። ልክ ከሃያ ዘጠኝ ቀናት በፊት የተፃፈ ነው።

የጆን ባፕቲስትን ደብዳቤ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠችና የሚኒስትሩን በላዩ ላይ አኖረች። ልታውቅ የፈለገችውን ስላወቀች ከዚህ የበለጠ ማንበብ አያስፈልጋትም።

# 2

ካምፖቻቸው ካለበት ከፍተኛ ቦታ ላይ ሆነው፣ ጆን ባፕቲስትና ጓደኞቹ መላዋን የስዊስ ከተማ ማየት ይችላሉ። ከተማዋ፣ ጥቂት የኦቶማን ሕንፃዎችና ከቀይ ሸክላ የተሠሩና የሮማውያን የጣሪያ ክዳን ሸክላ የለበሱ ብዛት ያላቸው ባህላዊ ቤቶች በዝቅተኞቹ አረቦች መኖሪያ ሠፈሮች ውስጥ እዚህም፣ እዚያም ተንጠባጥበው የሚታዩባት ናት። በሁለት ረድፍ፣ በረዥም ቦታ ላይ የተተከሉትና ጠርዛቸው የነተበ የሚመስሉት የቴምር ዛፎች አረንጓዴ ቅጠሎች፣ ከባህር ወሽመጡ ውስጥ በሚመጣው ነፋስ ይርገበገባሉ። ሶስት ማዕዘን ቅርፅ ያላቸው የጠረፍ ነጋዴዎች ጀልባዎችም፣ እስከ ምድረበዳው መዳረሻ በሚዘረጉት የስማያዊው ባህር፣ቀጭን ጣት በሚመስለው ውሃ ላይ በረዥም ሰልፍ ይንሳፈፋሉ። መንገደኞቹ የሲናን ባህረገብ ገደል ወደኋላቸው ትተው፣ የግብፅን ለጥ ያለ የጠረፍ ምድር ደርሰዋል።

ስዊዝ ማለት፣ የውሃ ሕልም የሚያበቃባት የሃዘንና የትካዜ ቦታ ናት። በሕንድ ውቅያኖስ ውስጥ ዳብሮ የሚጀምረው ውሃ፣ በቀይ ባህር ረዥም ክንድ ውስጥ እየተንከባለለ ቀጥሎ በዚያው ባለው አሸዋ ውስጥ ሲቋረጥ፣ የሜዲቴራኒያን የማይበገርና የማይነቃነቅ ምድር፣ ለቀይ ባህር ጥሪ ጆሮ ዳባ ልበስ ያለ ይመስላል። ለቁጥር የሚያታክቱ የሲራራ ነጋዴዎች የሰፈር ምልክቶች ወይም ዱካዎቻቸው ሁለቱንም የባህር አካሎች በሚከፍለው የአሸዋ ቀበቶ ሁሉ ላይ መስመራቸው ተዘርግቷል።

ጊዜው የዝናቡ ወቅት ማብቂያ ነበር። የመጨረሻዎቹ ዝናብ ያዘሉ ጥቋቁር ደመናዎች ከባዱንና ቀዝቃዛውን ዝናብ በምድር ላይ ሊያዘንቡ በዝግታ ይሰባሰባሉ። ባሮች፣ የወዳደቁ እንጨቶችን ሰብስበው በሚያነዱበት እሣት አጠገብ ጥቂት የተጎዥ ቡድኖች ተቀምጠው ይመለከታሉ። ጊዜው ፈጥኖ እየመሸ ነው። በሰማይ ውስጥ የሚታዩት ቀለማት ማራኪ ህብር ፈጥረዋል። ጥላው የምድሩን አቀማመጥ አጉልቶ ስላወጣው ንፅፅሩን ያሣምረዋል። ይህ አስደናቂ ነገር እያለ፣ ተጓዦቹ እርስ በርሣቸው ሳይተያዩ የየራሣቸው ምስኪን ሁኔታ ሁሉ ይሰማቸዋል። በዚህ ሰዓት ሁሉም የሚሰማቸውን ዓይነት ስሜት ያልተሰማው፣ ሙራድን ብቻ ነበር። ሙራድ በዚህን ጊዜ ሙሉ በሙሉ የሚያስበው ስለምግባቸው ጥራት ብቻ ነበር።



የሚቀቀለው ምግብ፣ ቀለሙ ቀይሮና አምሮ እንደሆነ በማለት አሁንም አሁንም እየተንተከተከ ያለውን የቆፋውን መግላሊት ያነሣል።

ጐንደርን በኩራት ከለቀቀው ሰልፍ የቀረው ጥቂት ነው። የሙራድ ፈረስ፣ ገና ከተራራው እንደወረዱ በቆላ ዝንብ ተነድፎ ሞተ። ሌላ ፈረስ ለማግኘት አርመናዊው ወደ ንጉሠ ነገስቱ ዘንድ መልዕክት መላክ ነበረበት። አምስት ፈረሶች ወዲያውኑ ተላኩለት። ሆኖም ግን፣ እነዚህም በፍጥነት ሞተው አለቁ። የሁለቱ ፈረንሣውያን ፈረሶች ግን ትንሽ እንኳ ባለመታመማቸው ጥርጣሬ አስከተለ። መዘግየቱ ያስቆጣው ፖንሴ፣ ሜትር ዝረሚን ይዞ ለቆንሲሉ መልዕክት መላክ ወደሚችልበት ወደ ጅዳ በጀልባ ተጓዘ። በመጨረሻም በሣጥኖች የነበሩትን ብዙዎቹን ነገሮች ከሠዋ በኋላ፣ ሙራድ የቀረውን በአህዮችና በሁለት በቅሎዎች ላይ ጫነ። ፖንሴ ግን፣ ሙራድ የቀሩትን ሁሉ ምፅዋ ላይ አትርፎ ሣይሸጥ እንዳልቀረ ጠረጠረ። በጊዜው ዝግጅቱ ይህን ይመስል ነበር። ዝሆኖቹ ረዥም ዕድሜ አላገኙም። አንደኛው ጠረፍ ላይ በነበረው ሙቀት ሳቢያ ሞተ። ጠንካራ የሚመስለው ሌላኛው ዝሆን ግን በአንድ አነስተኛ ጀልባ ላይ ሙሉውን ወሰል ይዞ ተጫነ። ይህን ዝሆን በሰንሰለት አስሮ ጀልባው ላይ ለመጫን አስር ሰዎች አስፈልገው ነበር። ዝሆኑ በጀልባው ላይ ተጭኖ እንዲያ ሲንሳፈፍ ሲመለከተው ሙራድ ኮራ። ከዚህ በኋላ ቀሪዎቹን አጃቢዎቹን አስከትሎ እርሱም በፈንታው ዝሆኑ የተጫነበትን ጀልባ ለማጀብ በትልቅ ጀልባ ላይ ተሣፈረ። በእንስሳቱ አዕምሮ ውስጥ ምን እንደተፈጠረ ምስጢር ሆኖ ይቀራል። ነገር ግን የዝሆኑ ጥጃ ዙሪያውን በውሃ በመከበቡ ፍርሃት ዋጠው። ጆሮዎቹን እያራገበና በሚያስፈራ ሁኔታ ጡሩምባ መሰል ድምፁን እያሠማ፣ የታሠረባቸውን ሁለት ሰንሰለቶች በጥሶ ወሰሉን ረጋግጦ አደቀቀው። የጀልባዋ ነጅ ግን ውጤት ባያመጣም ዝሆኑን ለማረጋጋት ተሯሩጧል። ነገር ግን እርሱም ባለመቻሉ፣ ዝሆኑ የታሰረበት ጀልባ ተገልብጦ የባህሩ ውሀ በላያቸው ላይ ተደፋ። በዚህ አደጋ አምስት የጀልባ ሠራተኞችም ሰጠሙ።

ሙራድ፣ ምንም ዝሆን ሣይዝ ደረሰ። አስቀድሞ መሬት ላይ የሞተውን ዝሆን ጆሮዎች ግን አስቧብት በማስቀረጥ በሚገባ በሚስማር በታሸገ በእንጨት ሳጥን ውስጥ አስቀምጧቸዋል። እነዚህ የሚያማምሩ ትላላቅ ጆሮዎች የአፍሪካ ዝሆኖችን ጆሮዎች ያክላሉ። የንጉሰ ነገስቱን እፁብ ድንቅ ስጦታ ምልክት ለማስቀረት አስቦ ስላከናወነው ሥራ፣ ጆን ባፕቲስት፣ አርመናዊውን አሞገሰው። በዚህ ማስረጃ ለተጠራጣሪዎች ሊያሣዩት የሚችሉት ይኖራቸዋል። የጆን ባፕቲስትን ሙገሣ፣ ሙራድ በትህትና ተቀበለው። ነገር ግን፣ በርሱ አዕምሮ ውስጥ

የዝሆኑን ጆሮዎች አስቀርጦ ያስቀመጠበት ምክንያት ፍፁም የተለየ ነበር። ከዚህ በፊት እንደሰማው የዝሆን ጆሮ በሚገባ ተጠብቆ እንዲደርቅ ቢደረግ ተወዳዳሪ የሌለው ልስላሴ ይወጣዋል።

የባሮችም ሁኔታ የተለየ አልነበረም። ሱቁርካዊው ሱልጣን ምስጋና ይግባውና እርሱ በሳክለት ጠመንጃ ተኳሽ፣ በትንንሽ ደሴቶች ላይ የነገሠው የምፅዋ መስፍን፣ መንገደኞቹ ሣይረበሹ እንዲያልፉ የሚጠይቀውን የንጉሡን መልዕክት ለማክበር ሙሉ በሙሉ ዝግጁ ነበር። ናኢቡ፣ ሃያላኑ ጕረቤቶቹ በርሱ በኩል መልዕክተኞቻቸው እንዲያቋርጡ ሲጠይቁት አጅግ ያመሰግናል። ይሁን እንጂ በንጉሥ ነገስቱ መልዕክት ውስጥ የባሮች ነገር ስላልተጠቀሠ፣ ናኢቡ አራቱን ሴቶች ለራሱ ጥቅም ሲል አስቀራቸው። ከሙራድ ሰዎች አንዱ በዝሆኑ ሣጥን ውስጥ አብሮ ሞተ። አራቱ ግን ጅዳ ደረሱ። የእንስሳቱ ጭነት ቀለል ይልላቸዋል በሚል ለመካው ሸሪፍ ታስቦ የነበረውን ስጦታ፣ አርመናዊው፣ ምፅዋ ላይ ሸጧቸዋል። በምትኩ ግን የቀረበለት የጥርኝ ዝባድና ሁለት ክረጢት የወርቅ አፈር፣ ለሸሪፉ አነስተኛ ካሣ ሆነለት። ከቀሩት አቢሲኒያውያን ባሮች ይበልጥ ፈርጣማ ጡንቻ ባላቸው በሁለቱ ላይ አይኑን የጣለው ሸሪፍ፣ እነዚህ የርሱ ንብረቶች መሆናቸውን አሳወቀ። በዚህ ላይ ፖንሴ ተቃውሞ ሲያነሣ፣ ሸሪፉ አንዱን ብቻ ለመውሰድ ተስማማ። ከዚህ በኋላ የተረፉት ሦስት ብቻ ሆኑ። ከነዚህም ውስጥ አንዱ እግረ ቀልማማ ሲሆን፣ ሁለቱ የአስራ አንድና የአስራ አራት ዓመት ሕፃናት ናቸው። እነዚህ ልጆች በዚያን ዕለት ምሽት በስዊዝ ኮረብታዎች ላይ እራታቸውን በሉ።

ሁለቱ ፈረንሣውያን እስካሁን ያለውን ታሪካዊ ሂደት ሊያሻሽሉት አልቻሉም። ፖንሴ፣ በአረቢያ ውስጥና በቀይ ባህር ጉዞ ላይ ክፉኛ ከመታመሙ በስተቀር ፈረሶቻቸውና ብዙው ጓዛቸው አሁንም ድረስ መኖራቸው ርግጥ ነው። ቀደም ሲል ምፅዋ ውስጥ ሜትር ዠረሚ ታምሞ ነበር። ከአንድ ዓመት ጉዞ በኋላ ሰውነታቸው መንምኖ፣ በትኩሣትም ደክሞ፣ በጀልባ ላይ ከወጡም በኋላ እግሮቻቸው ቆስለው፣ የሚታጠቡበት የጨው ውሃ አሳብጦባቸው፣ አሸዋውም አበቃ ሲባል ይባስ እያበሳጫቸው ነው። ክብራቸውንና ማዕረጋቸውን ሊመልስላቸው የሚችለው ጅዳ ውስጥ ተስፋ አድርገው የገዟቸው አዳዲስ ቦላሌዎች፣ ባለማሰሪያ ኮሌታ ያላቸው ከጥጥ የተሰሩ ሸሚዞችና ቀያይ ለደሪያዎች ናቸው። የገዙትም እንዲህ ነው። ጥቂት የባህር ላይ ወንበዴዎች እነዚህን ልብሶች ከአውሮፖውያን የሽልማት መርከብ ላይ በምርኮ የወሰዷቸው ናቸው። ወንበዴዎቹም ልብሶቹን በመጠኑኛ የወርቅ መጠን ሊለውጧቸው



ይስማሙዋቸዋል። ልብሶቹን ከገዙ በኋላ በጥንቃቄ አጣጥፈው በቆዳ ሻንጣዎቻቸው ውስጥ ይደብቋቸዋል። ከዚህ በኋላ የተነሣው ጥያቄ እነዚህን ልብሶች እንዴት ሊጠቀሟቸው እንደሚችሉ ነው። ከዚህም በተረፈ ፀማቹ ጓድ፣ ካይሮ መግባቱ አይቀርምና እንዴት ሲገሰፅ ነው የሚለው ሌላው ጥያቄ ነበር።

«ከካይሮ የሶስት ቀናት ጉዞ ርቀት ላይ ነን» አለ ጆን ባፕቲስት «ከዚህ በኋላ ከነዚህ ከሁለቱ ጋር አብረን እንጓዛለን። በመጨረሻው ሠፈራችን ላይ፣ ዠረሚ ፈረስህን ለኛ ትተህ በቅሎ በመያዝ ወደ ሰሜን ትሄዳለህ። ከሁለት ቀናት በኋላ በአባይ ዳር ካለችው ቤንና መንደር ትደርስና ከአንድ ቀን በኋላ ከአሌክሳንደሪያ ካይሮ ትገባለህ። ምክንያቱም ሄዷል የተባልከው አሌክሳንደሪያ ስለሆነ ነው።»

ምንም እንኳ ይህ ሰው የጉዞውን መከራ ሁሉ አብሮ የተጋራ ቢሆንም፣ በመልሱ ላይ አንዳችም ክብር ሳያገኝ ነው። ይሁን እንጅ ይህን ትሁት ድርሻ፣ ይህ ልምድ ያለው የጥንት ወታደር በዝምታ መቀበሉን ፖንሴ ያውቃል።

«ሁሉታችንስ፣ አብረን እንቆያለን?» ሲል ሙራድ በመጓጓት ጆን ባፕቲስትን ጠየቀው።

«አዎን፣ ግን ለሁለት ቀናት ብቻ። ከዚያም ዠረሚ የሚለየን ቦታ ላይ ትቆያላችሁ። እኔ ቀድሜ እሄዳለሁ።»

«ምን?» አለ ሙራድ «ብቻዬን በምድረ በዳ መካከል ልቆይ ነው?»

«ብቻህንማ አትሆንም። ባሮቹ አሉልህ» ሲል ሜትር ዠረሚ አጉረመረመ

«ቅር የሚልህ ነገር አለ? ለመሆኑ አይተሃቸዋል?»

«ደህንነቱ በሚያስተማምን የሲራራ ነጋዴ ሰፈር እናርፋለን። እዚያም ለሚጠብቃችሁ ሰው እኔ እከፍላለሁ።» አለ ፖንሴ ኮስተር ብሎ

«እናም አንተ ቀድመህ ትሄዳለህ?» አለ ሙራድ ጠንካራ እምነት ሳይኖረው።

«የናንተን መድረስ አስቀድሜ ወሬው እንዲነዛ አደርጋለሁ። በሚቀጥለው ቀን እኩለ ቀን ላይ፣ በተቻላችሁ መጠን በጨዋነትና በኩራት ትመጣላችሁ። ከባሮቹ አንዱ፣ በዕድሜ ጠና

ያለው፣ የእግሩን ሽባነት ለመደበቅ ቁርጥራጭ ጨርቆችን እንጠመጥምበትና በሌላው በቅሉ ላይ ሆኖ ይከተልሃል። ሁለቱ ህፃናት በአህዮች ላይ ሆነው ከኋላ ይከተላሉ።»

ሙራድ ጭንቅላቱን አነቃነቀ።

«ለመሆኑ ሻጥንህ ውስጥ ስንት ልብሶች አሉህ?» አለ ፖንሴ

«አንድ»

«በመጠባበቂያነት ያዘው። በደፋ የምትታይበት ቦታ ስትደርስ ቀይረው። ወደ ከተማዋ መግቢያ ላይ ስትደርስ ሰላምታ ሊያቀርቡልህ የሚመጡትን ሰዎች እጅግ ረዥም፣ አስቸጋሪና አደገኛ ጉዞ አድርጎ የሚመጣውን ሰው እባካችሁ ተዉት በላቸው።»

ከዚህ በኋላ በጥቂት ተጨማሪ ጉዳዮች ላይ ተወያይተው ከተስማሙ በኋላ፣ ጊዜው ስለመሸ በእሣቱ ዳር በየጃንያዎቻቸው ላይ ተጠቅልለው ተኙ ። ጆን ባፕቲስት፣ ታላቅ ፍንደቃ ተሰማው። መላ አካሉ፣ አንድ ሺህ አንድ የድካምና የሕመም ስሜት ለቀቀበት። ላለፈው አንድ አመት ከስራቸው ሆኖ ያደረባቸውንና በቅርቡ የሚለያቸውን የከዋክብት እይታም አሰበ። በቅርብ ያለችውን ካይሮና የአሊስ ልዩ ስሜት አዕምሮውን ሞላው። ሁሉም ነገር ተስፋ የሚያስቆርጥ ቢሆንም እንኳ አንድ ተንኘ በጉዞ ጅማሮው ላይ ትዕግስት አያጣም። ስለሆነም በጉዞው መሃል ላይ የነበረው ትዝ አለው። ታዲያ አሁን በመመለሻው ሰዓት ላይ መዘግየቱ ለምንድን ነው?። ደቂቃዎች እንዲህ እየተንቀራፈፉ የሚያዘግሙት ለምንድን ነው? በተለይም ሰላም በሚያገኝበትና ሁሉንም በመጨረሻው ላይ በሚያውቅበት ሰዓት ለምንድን ነው ጥቂቶች እንቅፋት የሚሆኑት? ሲል ይጠይቃል።

የመመለሱን ሃሣብ ጆን ባፕቲስት ለረዥም ወራት በውስጡ ሲያሣድገው ቆይቷል። አሊስን፣ ፍቅሯንና እስከ ዘለዓለም የሚጣመሩበትንም ሁኔታ አሰቧል። ነገር ግን የሚወድዳትን ሴት፣ በዓይኖቹ ሥር የሚያኖርበትን፣ ራሱንም ለታላቅ ደረጃ ለማብቃት፣ ድንጋይ በድንጋይ ላይ በመገንባት መላውን ሕንፃ እንዴት እንደሚሰራው በቅፅበት አሰበ። በመካከላቸው ያለው ርቀትና ልዩነት ምንም ያህል የሰፋ ቢሆንም፣ ከተለያዩና ግራ ከሚያጋቡ ደካማ ተስፋዎች የተሠራ የሃሣብ ሕንፃ ቢሆንም፣ ትዝታውን ይጠግንለታል። ጥቂት ረዘም ካሉ ያለፉ ቀናት የተሰበሰቡ ያልተሟሉ የዕይታና የድምፅ መረጃዎችን ይዞ፣ በመሠረቱ አይታው የማታውቀው



ሴት ታፈቅረኛለች ብሎ ማሰቡን፣ በሚገባ የማታውቀው ሴት ትጠብቀኛለች ብሎ በጭፍን የሚወራረድ መሆኑን፣ ይህ ሁሉ ሃሣብ እንዴት በሚከዳ በአሸዋ ላይ የተገነባ ሕንፃ እንደሆነ ተገነዘበ። ይህን እያሰላሰለ ረዥምም ቦታን ለረዥም ጊዜ ተጓዘ። ይህ ታዲያ ከራሱ ፍላጎት ሌላ ሊሆን ይችል ይሆን? ያንን ሌሊት በነዚያ ስለታም የምድረ በዳ ድንጋዮች ላይ ሳይመቸው አረፍ ብሎ፣ ጆን ባፕቲስት፣ አሊስ ታፈቅረው እንደሆነ ብቻ ሳይሆን፣ ከቶውንም እርሷ በዚህ ዓለም ላይ በርግጥ ኖራ ይሆን ሲል ራሱን ጠየቀ።

በመጨረሻም ይህን የመጨረሻ ሠፈር እኩለ ለሊት ላይ ለመልቀቅ ወሰነ። ባለፈው ቀን ሁሉም ነገር እንደታቀደው ተከናውኗል። ሜትር ዠረሚ፣ እንደልማዱ እያጉረመረመ በአሌክሣንደሪያ አቅጣጫ ሄዷል። በጣም እንቅስቃሴ በሚበዛበት የሲራራ ነጋዴዎች ማረፊያ ስለሠፈሩ፣ ሙራድ ተፅናንቷል። በዚህም ላይ ሁለት ሚሊሺያ ወታደሮች ለሊቱን እዚያ ለማሣለፍ ወስነዋል። ሁሉም ሰው ስለደከመው በጊዜ ተኛ። ሙራድም ወዲያውኑ በከፍተኛ ድምፅ ማንኮራፋት ጀመረ። ጆን ባፕትስት በበኩሉ እንቅልፍ እንደማይወስደው አውቋል። በፀጥታ ፈረሱን ጫነው። አህያውንና ሌላውን መሣሪያውን ሁሉ በሚቀጥለው ቀን ወደ ከተማ እንደሚደርሱ ስላወቀ ከቀረው ጓዝ ጋር ተወው። ሲነሳ ግን፣ ንፁህ ሸሚዙን፣ ቦላሌውንና ኮቱን ለብሶ ብቻውን ወጣ። በምዕራብ በኩል ትልቅ ነጭ ጨረቃ መንገዱን እንደ ክረምት ፀሐይ ወገግ አድርጋ፣ በማብራቷ ታሣያለች። ቀኑ የሚያንገበግብ ሙቀት በመሆኑ ከአንዳንድ ኪስ ቦታዎች ላይ ባሉ መንገዶች ሞቃት አየር ይጋረፋል። ብቸኛው ሰው እንደ ብዙ የሃር ኮቶች መውሰብሰብ ብቅ ጥልቅ እያለ ይጋልባል። በምድረ በዳው መሬት ላይ የፈረሱ የኮቴ ምት እንደ ብዙ የልብ ትርታዎች የገደል ማሚቶ ፈጥሮ ይሰማል።

ጆን ባፕቲስት፣ በፕቶሎሚ ቤተመቅደስ ፍርስራሽ ስር ሲያልፍ፣ ዓለም ገና በጨለማው ውስጥ እንደጠለቀች ነች። የጊዜውን ማጠር ማሰላሰል አልፈለገም። ይልቁንም፣ እርሱ በተቃራኒው፣ የእያንዳንዷን ሴኮንድ ዘለዓለማዊነትና ከቤቱ ተለይቶ የቆየበትን ማብቂያ የሌለውን የጊዜ አዝጋሚነት ያስባል። ሰማይና መሬት ሲላቀቁ ካይሮ ደረሰ። ዘበኞቹ ሁሉ ተኝተዋል። በሮችም ዝግ ነበሩ። ውብ ልብስ የለበሰና ምንም መሣሪያ ያልታጠቀውን ፈረንሣዊ ከተመለከቱ በኋላ ምንም ጥያቄ ሳያቀርቡለት እንዲገባ ፈቀዱለት። እንደግራጫ ጥላ ከወዲያና ከወዲህ በመዋከብ ላይ ከሚገኙት ለማኞች በስተቀር፣ ከተማዋ አሁንም በእንቅልፍ

ላይ ነች። ከፀሐይዋ ጋር ቀዝቃዛ የነፋስ ሽውታ አብሮ መጣ። ወፎች በፊጣን በረራቸው ከአናት በላይ ሽው ሽው እያሉ ይዘምራሉ።

ሽማግሌው የፈረንሣውያን ማህበረሰብ ሰፈር ጠባቂ፣ ፖንሴን ገና ሲጋልብ እንዳየው የመስኬቶ ጠመንጃውን ሊተኩሱበት ነበር። ነገር ግን ወዲያውኑ ለየውና የደስታ ፖኸቱን ለቀቀው። ጆን ባፕቲስት ግን ዝም እንዲል ገሰፀው።

በመጨረሻም ወደ ዋናው ጉዳና ሲገባ፣ የቆንሲላው ግቢ ግማሽ መንገድ ያህል ዝቅ ብሎ በነፖ ሜዳ ላይ ባንዲራው ሲውለበለብ ተመለከተ። በረኸርም መንገድ ስግሪያው የተነሣ ፈረሱ አረፋ ደፍቆ፣ ሳይመሩት ይራመዳል። ጋላቢውም፣ መኮርኮሩንና ማጣደፉን በመተው ለኮውን ቀዳማዩ ላይ አሳርፎታል። ጆን ባፕቲስት ቀና ብሎ፣ የአሊስን መስኮት ተመለከተ። መስኮቱ ክፍት ነው። ቢሆንም መጋረጃዎቹ ወርደዋል። በዚህ ሰዓት ከዚህ ንድፉ የተገላቢጦሽ ታትሞ ከሚታየው ሰማያዊ የጥጥ ጨርቅ በስተቀር በርሱና በርስዋ መካከል ሌላ መሰናክል የለም። ሊለያቸው የሚችል ምድረበዳ ወይም ተራራ ወይም የዱር አውሬ የለም። አሁንም ቢሆን፣ ሁለቱን የለያያቸው የፍቅር ጉዳይ በተነሣ ቁጥር፣ የመረዳዳትና የመደጋገፍ ጥያቄ በተወሣ ቁጥር፣ ሰዎች በመሃከላቸው ያበጁት ደካማ፣ ነገር ግን ለጊዜው ጠንካራ ግርዶሽ ብቻ ነው። ጆን ባፕቲስት ከማስተዋሉ በፊት ፈረሱ ቆመ።

በአትክልቱ ስፍራ ውስጥ የሚንቃጨል ድምፅ ተሰማ። ምናልባትም ጠባቂው፣ ይህ እንግዳ ሰው ምን እንደሚፈልግ ለማየት ሲቀርበው ይሆናል። ሆኖም፣ ቅጭልጭልታው ጆን ባፕቲስትን ከቀን ህልሙ አነቃው። ፈረሱን እንዲራመድ አደረገው። በመጀመሪያው መንገድ ተጠምዝዞ የለመደውን ግን የረሣውን ቁልቁለት መንገድ አግኝቶ ወደ ቤቱ ሄደ። ከፈረሱ ላይ ወርዶ፣ በመሿለኪያው ላይ ባለ የቀለበት መቀርቀሪያ ላይ ካሠረው በኋላ ወደ ቤቱ በር አቀና። ቁልፉ እንደተለመደው በተሸረፈው ግድግዳ ውስጥ ባለው ጉድጓድ ተደብቋል። በሩን ከፍቶ ገባ። የታችኛው ቤት ወለል አሁንም ጨለማ ሲሆን፣ በፎቁ ላይ የሚገኘው የርሱ ክፍል ግን ብሩህ ቀን ሆኗል። በክፍሉ ውስጥ አንዳችም የተለወጠ ነገር የለም። በዓለም ውስጥ ወዳለ ሩቅ ቦታ ሄዶ ስለነበር፣ ሌላው ቀርቶ ራሱ ያለፈበትን ዱካ እንኳ አጥቶ ነበር። እንደተረት ተረት ከሚታሰቡና በቀላሉ ከማይደርስባቸው ሰዎችም ጋር ተነጋግሯል። በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ ሊገደልም ነበር። በውሃ ውስጥም ሊሰምጥ ነበር። ረሃብም ሊገድለው ነበር። ልክ እንደህልም፣እውነት በማይመስሉት ተንጠልጣይ የቁሺያ ተክል፣ ሃምራዊው አበባ እያፈካ ነው።



የአጋቬው ዕፅ፣ በህይወት ዘመኑ አንዴ የሚያብበውን አበባውን፣ በረዥሙ ዘንጋማ ሽካራ ግንዱ ላይ ያወዛውዘዋል። አራውካሪያው መቅላት ጀምሯል። የብርቱካን ዛፎች ፍሬ አበጅተዋል። የተክሎቹ አዝጋሚ ታዛዥነት፣በተጨነቀችው ሀይወቱ ውስጥ ያለፈው ሳይቋረጥ፣ ወደ አሁኑ ማለፍ የሚያስችለውን የመተሳሰፊያ መስመር አበጅተዋል።

የተክሎች ተፈጥሮአዊ እድገት፣ የሰውን ልጅ እጆች በማፍቀራቸው ምን ያህል በቁጥጥር ስር እንደሆኑ፣ ምን ያህል እየተመሩ እንደሆነ ጭምር፣ ጆን ባፕቲስት ተመለከተ። ጥቂት ወንበሮች በበረንዳው ላይ እዚያና እዚያ ከመታየታቸው በስተቀር፣ እርሱ እስከሚያስታውሰው ሁሉም ነገሮች ባኖራቸው ሥፍራ ላይ ናቸው። መከራ የማይችለው ስብስብ፣ ብርታቱንና ሥርዓቱን፣ ምርታማነቱንና መጠኑን ጠብቆ ሲያየው ያልተቋረጠና ከመጠን በላይ የሆነ ክትትል እንደተደረገለት አወቀ። በእፅዋቱ መካከል ያለው ሰላምና ርጋታ የተጠበቀው፣ በሚቀናቀኑትና በሚበጣበጡ ተክሎች መካከል ሚዛናቸው ተጠብቆ እንዲቆዩ ያደረገው የተንከባካቢያቸው ብልህነት አለ። ከመጀመሪያ ዕይታው ጀምሮ እንዳልተዋቸው ተረዳ።

ይህንን ካረጋገጠ በኋላ ከባድ ድካም በሰውነቱ ሁሉ አረፈ። ሙሉ ልብሱን እንደለበሰ፣ የፈረስ መኮርኮሪያው ከጫማው ጋር እንደታሰረ፣ ወደተንጠልጣዩ አልጋው ሄዶ ተጋደመ። ጉዞው የፈጠረበት የመንፈስ ጭንቀት፣ ባለማቋረጥ የቆየበት ጥንቃቄና አመቱን ሙሉ የነበረው ሙሉ ንቃት በአንድ ጊዜ ከላዩ ላይ ወረዱ። በድካም ላይ ያነጣው ብርታት፣ በጥቂት ክሮች ብቻ ተይዞ የነበረው የውቅያኖስ ማዕበል ድካም፣ አሁን ብጥስጥሱ ወጣ። ዓይኖቹን ጨፍኖ ወደ እንቅልፍ አለሙ ሄደ።

ጆን ባፕቲስት፣ በሃይለኛው ህልም ሳቢያ ነቃ። በአትክልቶቹ አጠገብ አንድ እጇ አፏን አፍና፣ አይኖችዋ በፍርሃት ፈጥጠው፣ ፍራንቾይዝ ቆማለች። ማንነቱን ስታውቅ ፊትዋ ተለወጠ።

«ኦ! በመጮሄ አዝናለሁ። ሙሴ ጆን ባፕቲስት፣ ሙሴ ጆን ባፕቲስት፣ በርግጥ አንተ ነህ? እንዴት ማወቅ እችላለሁ? አምላኬ ! እንዴት ተለውጠሃል?»

ተንጠልጣዩ አልጋ አጠገብ ደርሳ፣ የወጣቱን ሰው እጅ ያዘችና ሣመችው።

«እምላኬ ! በጣም ክስተሃል። ያ ጉንጭህን ይሞላው የነበረው ፂምህም ደብልጥ ጉድጉዷል! ፀጉርህ በጣም አድጓል!»

አይኖችዋ እንባ እንዳዘሉ ታየው ጀመር። እርሱ በበኩሉ ስሜቱ በጣም ስለተነካ ቃል መተንፈስ አልቻለም።

«እንዴት ያሉ ውብ ልብሶች ናቸው?» አለች፣ ልዩ ልዩ ጥልፍ የተሰራበትን ወፍራም የቀይ ኮት ጨርቁን እየነካች።

በባህር ላይ ዘራፊዎች ተይዛ የነበረችው መርከብ ከፍተኛ ዋጋ ነበራት ማለት ነው። ጆዳ ውስጥ ስለጉዳዩ እምብዛም አትኩሮት ያልተሰማው ጆን ባፕቲስት፣ እንደጨዋ ሰው መልበሱን አሁን ተገነዘበ።

«ርበሃል?» ስትል ፍራንቾይዝ ጠየቀችው። ራሷን ስትገዛ «ጠምቶሃል?» ቀይ ከቤት የሆነ ነገር አገኛለሁ።

«የለም» አለ ጆን ባፕቲስት «አትቸገሪ፣ ይደርሳል፣ በኋላ፣ በኋላ፣ ብቻ የት እንዳለች ንገሪኝ»

«አ! ሙሴ ጆን ባፕቲስት፣ ስትጠይቃት መስማቴ ለኔ ደስታ ነው። ይህ ማለት ደግሞ አልረሣሃትም ማለት ነው። በጣም ሩቅ አገር በመሄድህ ምክንያት ፍርሃት ነበረብኝ። ለርሷ ግን ሁልጊዜም በተስፋ እንድትጠብቅህ እነግራት ነበር። በህይወት መንገድ ውስጥ ብዙ ነገሮች ሊያጋጥሙና የልብ ስሜትም ሊለወጥ ይችላል»

ጆን ባፕቲስት ተነስቶ፣ እግሮቹን ከአልጋው ልብሶች ውስጥ አውጥቶ ቀጥ ብሎ ተቀመጠ።

«ሊለወጥ ይችላል? የኔ ግን በምንም ምክንያት አይለወጥም። የሆነው ሆኖ እባክሽ የት እንዳለች ንገሪኝ? ለመሆኑ ሃሣቧስ እንዴት ነው?»

«ሃሣቧ ሁሉ አንተኑ የማፍቀር ነገር ነው። ከዚህ ከሄድክበት ዕለት ጀምሮ ካንተ በስተቀር ሌላ አስባ አታውቅም።»



«አ! ፍራንቾይዝ» አለ ጆን ባፕቲስት በክንዶቹ እያቀፋት ወይም እናቱ የሆነች መስሎት በርሷ ክንዶች ውስጥ እየገባ።

ከዚህ በኋላ የፍራንቾይዝን ትልልቅ እጆች በእጆቹ ውስጥ ይዞ ወደ ኋላ ራመድ አለ።

«ወደዚህ ትመጣለች?»

«በየዕለቱ»

«መቼ?»

«እ . . . » አለች ፍራንቾይዝ እየወጣች ያለችውን ፀሐይ በመስኮት በኩል እያየች «በዚሁ ሰዓት አካባቢ»

በጉጉት ስሜት፣ ጆን ባፕቲስት ዘሎ ተነሣ

«መምጣት የለባትም . . . » አለ። «ሂጅና እንዳትመጣ አድርጊያት። መመለሴን ንገሪያት። ነገር ግን በዚህ መልክ ሆኜ ልታየኝ አይገባትም። ለመሆኑ ማኑኤል እስካሁን እዚሁ ነው?»

ማኑኤል በዚህ ግቢ ውስጥ ለረዥም ጊዜ የኖረ ሽማግሌ አገልጋይ ነው። የቀድሞው ጌታው ወደ ፈረንሣይ ከመመለሱ በፊት፣ ጥቂት የጡረታ ገንዘብ ተቆርጦታል። ምንም እንኳ ዲዳ ቢሆንም፣ እስካሁን ድረስ ጠንካራ ሰው ስለሆነ፣ ፖንሴና ሽሪኩ በየጊዜው ሥራ ይሰጡት ነበር።

«እቤት ነው ያለው» አለች ፍራንቾይዝ

«ጥሪው። በገንዳው ውስጥ ውሃ እንዲሞላልኝና ሣሙናም እንዲያመጣልኝ ንገሪው። በተጨማሪም ፀጉሬንና ጢሜን እንዲያስተካክልልኝ እፈልጋለሁ። አንቺም ፍራንቾይዝ፣ ልትንከባከቢኝ ይገባል።»

«ቆስለሃል እንዴ?»

«እግዚአብሔር ይመስገነው ውስጤ ጤናማ ነው። ነገር ግን ውጫዊው አካሌ ብጥስጥስ ብሏል።»

ፍራንቾይዝ ሥራዋን ወዲያውኑ ጀመረች። በዚህ ጊዜ ውስጥ፣ የጆን ባፕቲስት አዕምሮ ግን በሥራ ላይ ነበር።

«ከአጭር ጊዜ በኋላ በቆንስላው ፅህፈት ቤት መገኘት ይኖርብኛል። መመለሴ አንድ ጊዜ ከታወቀ ወደዚህ ለጉብኝት መምጣት አትችልም። ታዲያ እንዴት አድርገን ነው መተያየት የምንችለው?»

«አትጨነቅ፣ አንተ እዚህ ባልነበርክባቸው ጊዜያት ውስጥ ብዙ ነገሮች ተፈፅመዋል። በአሁኑ ጊዜ እኔም፣ ለማዳም ዴ ማይሌ በማገልገል ላይ ነኝ። ወደ ቆንስላው ደስ እንዳለኝ እገባለሁ። እወጣለሁ። ቤቱ ግን እዚሁ ነው። ለማንኛውም አስፈላጊውን ሁሉ እናዘጋጃለን።»

«ፍራንቾይዝ! » አለ ጆን ባፕቲስት እጆችዋን እየሳማቸው።

ሮጣ ለመሄድ የተዘጋጀች መሰለች። የፎቁን መውጫ የመጀመሪያውን ደረጃ እንደደረሰች በተቻላት መጠን በጣም በተለመደ ድምፅ ተናገረች። ምናልባትም ተቀባይነት ያለውን አንድ ጉዳይ ለማንሣት ፈልጋ ይመስላል።

«ሽሪክህ ሜትር ዠረሚ መቼም አብሮህ አይደለም?»

«አይደለም» አለ ጆን ባፕቲስት ከጥያቄው አንዳች ነገር ለማንበብ ሳይችል ቀርቶ። «አሌክሳንደሪያ መሄዱን ታውቂ የለም እንዴ?»

«ጀመርክ እንግዲህ፣ ከእኔ ጋር መቃለዱን ተወው። ዘመቻህን መቀላቀሉን በትክክል አውቃለሁ።»

ካይሮን ለቅቆ ሲወጣ፣ ሜትር ዠረሚ፣ ለፍራንቾይዝ መመሪያ ሰጥቷታል። ምስጢራዊውን እቅዱንም ነግሯታል። ምስኪኗ ሴትም፣ ከተራ ምስጢርነት ባሻገር ነበር የተቀበለችው። ይህንንም ምስጢር ብርቅ ምስጢር አድርጋ፣ ከአሊስ ሣይቀር ደብቃ አቆይታዋለች። በርግጥም ደግሞ ከሰውዬው ጋር የተጋራችው ነገር ቢኖር ይህን ብቻ ነው።

«በይ እንግዲህ ሌሎች ሁሉ የሚያምኑትን አንችም እመኚ። እርሱ የሄደው ወደ አሌክሣንደሪያ ነው። ነገር ግን» ፖንሴ ንግግሩን ቀጠለ «በሚቀጥሉት ሁለት ቀናት ውስጥ እዚህ እንደሚመጣ አንዳች ነገር ሲነግረኝ ይሰማኛል»



# 3

ጆን ባፕቲስት፣ ካይሮ ውስጥ ባልነበረበት ጊዜ ምንም ነገር አልተለወጠም ብሎ ማሰቡ ትክክል አልነበረም። ሆኖም ይህን ያረጋገጠው ቆንሲላው ግቢ ሲገባ ነበር። ጉዳዩን በስፋት ከተመለከተው በኋላ፣ ቆንሲሉ፣ በትልቁ የእንግዳ መቀበያ ውስጥ ያለውን ጠረጴዛውን ከአንድ ጥግ ወደ ሌላው አዟዙሮታል። በዚህም መሠረት ጠረጴዛው እንደ ቀድሞው በመስኮቱ አጠገብ ሳይሆን በቀጥታ በንጉሡ ሥዕል ስር ያለውን ቦታ ይዟል። ቆንሲሉ ከንፁህ አየር ሊያገኘው ያልቻለውን ግርማ ተጎናፅፏል። ጥንቃቄ በተሞላውና በልዩ ሁኔታ፣ ጥቁር፣ ሰው ሰራሽ ፀጉሩን አጥልቋል። ጥብቅ ያለና ሲከፈት የፎሊየር የሐር ሰደሪያውን የሚያሣይ ባለወርቅ ዝምዝማት የቁልፍ ቀዳዳዎች ያሉት ጥቁር ሰማያዊ ልብስ ለብሷል። ከዚህ ቀደሙ ጊዜ ይበልጥ ቢያልበውም፣ በተለመደው ብርታቱ ዋጥ አድርጐ ችሎታል። ከሰዓት በኋላ፣ አስር ሰዐት አካባቢ ፖንሴን ተቀበለው።

ከነሃስ የተሠራ የተንቆጠቆጠ የቀለም ብልቃጥ መደረደሪያ በስተቀር ሌላ ከሌለበት ትልቅ የተስፋ ቆዳ ከለበሠው ጠረጴዛ በስተጀርባ ተቀምጦ፣ ሙሴ ዴ ማይሌ፣ እንግዳው እንዲቀመጥ እንኳ ሳይጋብዘው፣ የሚነግረውን መግለጫ ያዳምጣል። ጆን ባፕቲስት ዊሙን ተላጭቶና ፀድቶ፣ ፀጉሩን ተስተካክሎ ቢታይም፣ አሁንም እንደደከመ ሲሆን፣ ነጭና ጥቁር በሆነው የወለል ምንጣፍ ላይ እንደ ቼዝ ጠጠር ተገትሮ ቀረ። ዲፕሎማቱ፣ ውይይቶችን አጭር ከሚያደርግባቸው አነስተኛ ታክቲኮች አንዱ ይህ ነው። ሌላው፣ አሁን እንደሚያደርገው መጥፎ ቁጣን በግልፅ ማሳየት ነው።

ቆንሲሉ፣ የመድሃኒት ቀማሚው ተልዕኮ ማብቃቱን ግልፅ ለማድረግ ፈልጐ ነበር። ከዚህም በላይ፣ ሰውዬው ገና ሲደርስ ከቀረበለት አጭር የእንኳን ደስ ያለህ መግለጫ ባሻገር፣ ሌላ እንዳይጠብቅ የሚልም ነበር። ፖንሴ፣ ጅዳ ሆኖ የላከው ፖስታ ከአንድ ሣምንት በፊት በመድረሱ፣ ቆንሲሉ ይሠማውና ያስበው የነበረውን ጉዳይ የሚለውጥበት ምክንያት በፖንሴ መምጣት ተከስቶ ይሆናል። በአሁኑ ገዜ እጅግ አሣሣቢው ነገር በተለይም የቆንሰሉ ብቸኛው ጭንቀት፣ የንጉሡን መልዕክተኛ እንኳን ደህና መጣህ የማለቱ ነገር ነው። ይህ መድሃኒት አዋቂ ለጥቂት ጊዜ መልዕክታቸውን በማድረስ ጠቃሚ የነበረ ቢሆንም፣ በአሁኑ ጊዜ ጉዳዩ

እሰምን በሚያተራምሷት ዲፕሎማቶች እጅ ስለሚገባ አንድ ተራ፣ እግረኛና የልምድ መድሃኒት አዋቂ፣ ሣይሣለቁበት እድገት ሊመኝ እንደማይችል ሊረዳው ይገባዋል። ለኢትዮጵያ ኤምባሲ ተገቢውን አቀባበል ለማድረግ፣ ሙሴ ዴ ማይሌ አግባብነት ያላቸው ጥያቄዎችን ጠየቀ። የመልዕክተኛውን ስም፣ የክብር ተከታዮቹን ብዛት፣ የተጓዘበትን አቅጣጫና እዚህ ሊደርስ የሚችልበትን ሰዓት ግምት ጠየቀ። ወጣቱን ሰው፣ በጉዞው ላይ ስለነበረው ጀብዱ ላለማሞገስ፣ ቆንሲሉ ጥሩ ጥንቃቄ አድርጐ አለፈው። ተጓዡም በዚህ ነጥብ ዙሪያ ፍንጭ ሲያሣየው፣ እንዲህ ያሉትን ዝርዝር ጉዳዮች በርሱ ደረጃ ያለ ሃላፊ ሊሰማው እንደማይገባ ግልፅ አደረገ። ስለነዚህ የጉዞ አጋጣሚዎች ሁሉ፣ ቆንሲሉ ጆሮውን ቢሰጥ ሲበዛ ጅልነት ይሆናል። ሰውዬውም፣ እነዚህ ጀብዱዎች ለክብሩ ብቸኛዎቹ መሠረቶች ስለሆኑ ለራሱ ጠቀሜታ ሊያስተካክላቸው እንደሚጥር እርግጠኛ ነበር።

ጆን ባፕቲስት ፍፁም ደክሞታል። ወደ ቆንስላው ግቢ ሲገባም ሞልቶት የነበረው ጥልቅ ስሜትና አሲስን በድንገት የማግኘት ተስፋው ሁሉ፣ ስርዓተ ቢስነቱን በመመገብ ሊጠቅመው የሚችለውን የወኔ ሃይሉን፣ ተስፋ አስቆራጭ ወደሆነ መልክ ለውጦታል። ያጋጠመው የእንኳን ደህና መጣህ አቀባበል፣ ከቆንሲሉ የሚጠብቀው አይነት እንደሆነ አውቋል። ይሁን እንጂ፣ ከምሩ፣ ምናልባትም ይህንኑ ተስፋ አድርጐ ነበር። ሆኖም እጅግ ጥልቅ የቅሬታ ስሜት አደረበት።

«መስናበት እንድችል የቆንሲሉን ፈቃድ ባገኝ?» ሲል ወደ በሩ እየተራመደ ጆን ባፕቲስት ጠየቀ።

«አመሰግናለሁ» አለ። ለመልካም ተግባር የሚገባውን ሽልማት በሚገባ የሚያውቀው ሙሴ ዴ ማይሌ።

«ደህና ሁን ሙሴ ፖንሴ»

ወጣቱ ሰው ወጥቶ ሄደ። በውይይቱ ወቅት በአንድ ጨለማ ጥግ ቆይቶ የነበረው ማቼ፣ ወደ ቆንሲሉ ጠረጴዛ በመቅረብ ወደፊት ጐንበስ በማለት በተጣደፈና ዝቅ ባለ ድምፅ ተናገረ።

«ክቡር ሆይ፣ ኤምባሲውን ለመገናኘት የሚሄደውን የመልዕክተኞች ቡድን ይህ ሰው እንዲያጅብ ቢደረግ ተገቢነት የለውም ማለት አይቻልም»



«እሱን? እና በምን ሚና?» ሲል ሙሴ ዴ ማይሌ ጠየቀ።

«እንደሚመስለኝ . . . የንጉሡ መልዕክተኞችና ይህ መድሃኒት ቀማሚ ርስ በርስ ይተዋወቃሉ። ቢያንስ ቢያንስ፣ ከርሱ ጋር የሚኖረን የመጀመሪያ ግንኙነት ቀላል ይሆናል። አምባሣደሩም፣ የጉዞ ጓደኞቹ የት እንዳሉ ይጠይቅ ይሆናል . . .»

«ልክ ነህ። አሁንም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ወጣ ብለህ በመንገድ ላይ እንዳለ ተመልከተውና፣ መገኘት እንደሚገባው ንገረው» አለው ቆንሲሉ።

ልብስ አጣቢዋ፣ ጥሩ መዓዛ ያለውን ትኩስ ሽቶ በተፈጥሮ በሚያመነጨው ጠረኑ ፋንታ ልብሱ ላይ ስለረጨችበት፣ ሙሴ ማቼ ወደ በሩ ሲንደረደር ሽታው በክፍሉ ውስጥ ቀረ።

አዳራሹን አቋርጦ ደረጃው ላይ ፈጥኖ ደረሰ። በዚያም ሳይታሰብ በመንገዱ ላይ ራቅ ብሎ አገኘዋለሁ ብሎ ከሚያስበው ፖንሴ ጋር ተላተመ። የቀርከሃ ቅርጫት በክንዷ ስር ይዛ የነበረችው ፍራንቾይዝ፣ ከመድሃኒት ቀማሚው ጋር በመወያየት ላይ እንደነበረች አመነ። እርስዋ ግን ፀሐፊውን እንዳየችው አንዳችም ነገር ሳያቋርጣት፣ ከአትክልቱ ሥፍራ በቀጥታ እንደመጣች አስመስላ ወደ ቤት ገባች። ምንም ነገር የማይዘነጋው ሙሴ ማቼ፣ በተለይም አብራርቶ ሊገልፀው የማይችለውን ነገር የማይዘነጋው ሙሴ ማቼ፣ በርቀት ከዝኖ በሚያቆይበት፣ ነገር ግን በሚገባ ለይቶ ሊያውቀው በሚችልበት የአዕምሮው ክፍል ውስጥ፣ «ጠርጥር» የሚለውን ግምታዊ ሃሣቡን መዘገበ። ምንም እንዳላስተዋለ ሆኖ፣ ጆን ባፕቲስትን አናገረው።

«ነገ ጠዋት፣ ለአምባሳደሩ ሰላምታ ለማቅረብ ከሚንቀሣቀሰው የመልዕክተኞች ቡድን ጋር ተቀላቅለህ ለመሄድ ራስህን አዘጋጅ። በሰዓቱ ላይ እስከ አሁን ያልወሰንን ቢሆንም፣ ጊዜው ሲደርስ በተረኛው ወታደር በኩል መልዕክት እንልክብሃለን።»

ሙሴ ማቼ እንደማቅማማት ብሎ፣ ሙሉ በሙሉ የግሉን ምክር እንደሚለግስ ሰው፣ ዝቅ ባለ ድምፅ «እናም ተስማሚ ልብስ ልበስ። እዚህ የምንነጋገረው ወደ ንጉሡ ከሚሄደው ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ጋር ነው።»

ጆን ባፕቲስት በመገረም ተመለከተው። በጭንቅላቱ ውስጥ፣ አንዳች ድምፅ በሰውዬው ላይ ጮክ ብለህ ሣቅበት የሚል ሲሰማ፣ ሌላው ድምፅ ደግሞ ይህን አስቂኝ ሰው ሽቅብ ተቀልብሦ የታሰረውን ክሌታውን በመያዝ አንቀኸው ጭንቅላቱን ከግድግዳው ጋር አጋጨው ይለዋል። ሆኖም እነዚህን ሁሉ አልሰማቸውም። የሃዘንና የፍሬቢስነት ስሜት ስለተሰማው ይህን ሁሉ የሚያስወግድለት እንቅልፍ እንደሚሆን አሰበ። በተረከዙ ላይ እንደመሽከርከር ብሎ ዞሮ፣ ማንንም ሳይገናኝ ወደ ቤቱ ሄደ።

በቆንስላው ጽህፈት ቤት በር ላይ እንዳገኘችው፣ ፍራንቾይዝ ጥቂት ቃላትን ብቻ ልትተነፍስለት ነበር። የቻለችው

«ዛሬ ልታይህ አትችልም»

ጆን ባፕቲስት እነዚህን ቃላት አሰላሰላቸው። እቤት እንደደረሰም በጥልቅ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሰጠመ። ይህ አይነቱ ተስፋ መቁረጥ፣ በአንዳች ድራማዊ ክንዋኔ የተነሣ የተፈጠረ ሳይሆን ይልቁንም በዙሪያህ ያለው ሁሉም ነገር የሚቻል የሚሆነው፣ አንድ ሰው ሲኖርህ፣ ወይም እሰኝ ብለህ ተስፋ ስታደርግ የሚመጣ አሳዛኝ ክንዋኔ ነው። ይሁን እንጅ፣ ይህ አንድ ሰው፣ በሆነ መልኩ ጉድ ቢያደርግህ፣ ከዚያ በኋላ፣ አስደሳች የነበረችው ዓለም ወደ ፍርስራሽነት ትለወጣለች። በውስጧ ያሉት ሰዎች ሁሉ መርዛም፣ ከሃዲዎችና የሚያበሳጭ ይሆናሉ።

ஒ

አሊስ፣ አሁንም በአልጋዋ ውስጥ ብትሆንም መንፈሷ አልተረጋጋም። በትልቅ ተስፋና ሁልጊዜም እየታሰበ የነበረው የጆን ባፕቲስት መመለስ አሁን ከሆነ ነገሮች አንዳንድ ጊዜ እንደሚሆኑት፣ ሳይታሰቡ ልውጥውጥ የሚሉና፣ እርሷንም ማስተዋል ተስኗት የተተበተበች መሰላት። ለዕለቱ የእፅዋት እንክብካቤ ሥራዋ ለመሄድ ስትዘጋጅ ፍራንቾይዝ በመድረስዋ እፎይታ አገኘች። በአይኑ ህሊናዋ በግልፅ የሚታይዋት ችግሮች የፈጠሩባትን ድንገተኛ ድንጋጤ ዋጥ አደረገቻቸው።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጆን ባፕቲስትን ታየዋለች። እንዳችም እቅድ እንዳትነድፍ ሃሣቧ ሁሉ የተመሰቃቀለ ነበር። ፍራንቾይዝ ሁሉንም ነገር በጥንቃቄ ትጠብቃለች። አሊስ፣ ራሷን ዝግጁ



ማድረግ ብቻ ይኖርባታል። አዎን፣ ልክ ነው፣ መዘጋጀት ብቻ ነው ያለብኝ ስትል፣ ወጣቷ ልጃገረድ አሰበች። ፍራንቾይዝ ወጥታ ሄደች። በመጋጌጫ ጠረጴዛዋ አጠገብ ስትቀመጥ አቅሟ ሁሉ ከዳት።

ባለፈው አንድ ዓመት ውስጥ የኮመራውና በራስዋ ውበት የነበራት ኩራት ሁሉ ተጠርጐ ጠፋ። ፊትዋ ያበጠ፣ መልኳም አስቀያሚ፣ የፀጉርዋ ቀለምም አስጠሊታ መሰላት፣ ተፈጥሮአዊውን ፀጋዋን እንድትገነዘበው ያደረጋት የጆን ባፕቲስት የመጀመሪያ እይታ ነበር። አሁን ግን፣ ሙሉ በሙሉ በርሱ ለመፈተሽ ስትዘጋጅ ሁሉም ነገር ጠፋባት። እንዳፈቀረችና በምላሹም እንደተፈቀረች እርግጠኛ በነበረችበት ጣፋጭ ሕልም ውስጥ ኖራለች። በተለመዱ ሁኔታዎች ውስጥ እንዲህ ያሉ የህሊና ትስስሮች ከእውነታው ጋር ድርና ማግ ሆነው በቅርበት የተያያዙ ይሆናሉ። በዚህም መሠረት አንዳቸው ሌላኛውን፣ ማንም እንደሚያውቀው በተፈጥሮ ያጠናክረዋል። ድንኳኑም በእውነታና በዓይነህሊና፣ በተግባርና በፈጠራ፣ በትዝታና በምኞት እኩል ይሠራል። ሆኖም፣ እዚህ ግን፣ በተለመደው መለያየታቸው ምክንያት ፍቅር የሸመነው፣ አስፈላጊ ያልሆነው ለስላሣውንና ውብ ቀለሙን ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ገና ሲነካ እንደሚረግፈው የቢራቢሮ ክንፍ ወድቆ ትቢያ ይሆናል።

ተዘጋጅታ እንደምታገኛት በመተማመን ፍራንቾይዝ ወደ አሊስ ክፍል መጣች።

«ምን ነካሽ፣ ፈጠን በይና ተዘጋጅ እንጅ?» አለቻት

«መዘጋጀት አልፈልግም»

«ቆይ፣ ቆይ፣ ምንድን ነው ነገሩ?»

«እስቲ ተመልከችው ይህንን፣ በአፍንጫዬ ዳር ላይ ያለውን»

ፍራንቾይዝ አይኖቿን እንሸዋርራ ቀረብ አለች።

«የፈጠርከኝ ጌታ፣ ምንም ነገር አይታየኝም»

«በርግጥ ርህሩህ ነሽ፣ ነገር ግን የምትዋሺበት ምክንያት የለም። ትልቅ ቡጉር አለበት። እኔ ይሰማኛል። ደግሞም በግልፅ የሚታይ ነው» ቀጠል አድርጋም በቁርጠኛ ቃላ

«እንዲህ መሰዬ መታየት አልፈልግም»

«ጆን ባፕቲስት በማንኛውም ሰዓት እዚህ ሊደርስ ይችላል። እንደሚመስለኝ ለአፍታ አየት የማድረግ ጉዳይ ነው። የሚመጣውም ላንቺ ሲል ነው። የሚፈልገው ደግሞ አንቺ እስካሁን እዚሁ መኖርሽንና የምትጠብቂው መሆንሽን ለማየት ነው። መዘጋጀት ያለብሽ ራቅ ያለ ቦታ መሄድ ስለሚያስፈልግሽ ጉዳይ አይደለም። ብቻ ይይሽ። አንችም ታይዋለሽ። ሁለታችሁም፣ እንደስሜቶታችሁ ትፅናናላችሁ። ወደፊት ደግሞ ረዘም ያለ ጊዜ አብራችሁ ማሳለፍ ትችላላችሁ።»

«ፍራንቾይዝ፣ አይሆንም! ይህ ቡጉር በጣም አስጠሊታ ነው። እንዲህ ሆኜ እንዲያየኝ አልፈልግም።»

ሰፊ ልምድና ተሞክሮ ያላት ሴት በመሆኑዋ ከዚህ የበለጠ መጉትጉት ጥቅም እንደሌለው ፍራንቾይዝ ተገነዘበች። አሊስ፣ የቡጉሩ ጉዳይ በእውነት ያስጨነቃት ግብዝ አይደለችም። ይህ ሁሉ፣ የፍቅር ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎች ላይ የሚታይና የፈስጉትን እንዳያደርጉ ነፃነታቸውን የሚገድብባቸውና ባህርያቸውን አፍኖ የሚይዝባቸው ምልክት ነው። ፍቅር በህዋ ውስጥ የሚጋልብበት ወይም በህልም ውስጥ በነፃነት የሚከንፍባቸውና እያንዳንዱ ተፈቃሪ እንዲፈላለግ ወይም እንዲሸሻሽ የሚያደርግበት ጊዜያት አሉት። በሌላ በኩል፣ ፍቅር ገና መታወቅ ሲጀምር፣ አንዳች አነስተኛ እንቅስቃሴ፣ ሌላው ቀርቶ ደካማ የእጅ ወይም የክንድ እንቅስቃሴ፣ ሙሉውን ባሪያዎችን ብቻ ከሚጭን መርከብ ላይ ሰንሰለቶችን ለመበጣጠስ ከሚጠይቀው ጥረት የበለጠ ሃይል የሚጠይቅበት ሁኔታ አለ። ይህም ሆኖ ከመጠበቅ በስተቀር ምንም ማድረግ አይቻልም። ፍራንቾይዝ፣ ወጣቱ ሰው ይህን እንዲያውቅ ለማድረግ በአዳራሹ ውስጥ እንደሚተላለፍ ሆና ሄደች። አሊስ፣ በክፍሏ ውስጥ ብቻዋን ሆና ጣቶችዋን ነከሰች።

ካይሮ የሚገኘው የፈረንሣውያን ማህበረሰብ፣ የአውሮፖ አገራት ሕዝቦችን ሁሉ የሚያቅፍ ነው። የፈረንሣይ፣ የጣሊያንና የእንግሊዝ እንዲሁም የሌሎች አገሮች ተወላጆችን የሚያቅፍ ነው። አጠቃላይ ቁጥራቸው በብዙ መቶ ከሚሆኑት ከነዚህ ሕዝቦች መካከል ብዙዎቹ ነጋዴዎች ናቸው። ከአውሮፖውያን አገሮች መካከል ተወካይ ያላቸው ሁለት ብቻ ሲሆኑ፣ እነርሱም እንግሊዝና ፈረንሣይ ናቸው። ይሁን እንጅ፣ በዚህ ወቅት ላይ የእንግሊዝ ልዑካን ቁጥር እንደተለመደው ፍፁም ስለቀነሰ፣ ቆንሲል የለውም። ስለዚህም ላቅ ያለውን ቦታ የያዘው የፈረንሣውያኑ ነው።

የፈረንሣይ ቆንስላ፣ በአስተዳደሩ ጥላ ሥር የሚገኙ ፈረንሣውያን ላይ ቀጥተኛ ባለሙሉ ሥልጣን ሲሆን፣ በሌሎች አገሮች ዜጋዎች ላይ ግን ሥልጣኑ ቀጥተኛ አይደለም። እነዚህ ሰዎች፣ በቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑና ራሣቸውንም መከላከል የማይችሉ እንደ ማሮናይት ክርስቲያኖች ያሉ ስለሆኑ ፈረንሣይ ትጠብቃቸዋለች። በሌላ በኩል፣ ካይሮ ውስጥ ለጋሲዮን ለሌለው አገር ፈረንሣይ ለነዚህ ዜጐች የመንግስትነት ሚና እንዳላት አድርጋ ትገምታለች።

በነዚህ ማህበረሰብ አባላት ውስጥ ያለት ሰዎች፣ የቆንሲሉን ስልጣን፣ ሁሉም እኩል አይቀበሉም። በምስራቅ ሜዲትራኒያን የአውሮፖውያንን ማህበረሰብ ቁጥር ከፍ የሚያደርጉት ነጋዴዎች፣ ለቆንሲሉ ሥልጣን ያላቸው ክብር የማያስደስትና ፈቃደኛነትም የማይታይበት ነው። ይሁንና ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም። በቆንሲሉ ሥልጣን ሥር እንዲሆኑ ያደረጋቸው፣ ቱርኮች፣ በእስላማዊ አገር ውስጥ ለመኖርና ለመነገድ የሚችሉት በዚህ መልክ ሲሆን ብቻ እንደሆነ ስለፈቀዱ ነው። ነጋዴዎቹ፣ ለቆንሲሉ ሥልጣን ተመጣጣኝ የሆነ አቅም እንዲኖራቸውና የነርሱንም አቤቱታ የመቀበል ዕድል ከፍ ለማድረግ ሲሉ የማህበረሰባቸውን ተወካይ እንደራሴ ይመርጣሉ። የቆንስላው ባለስልጣኖችም፣ ፈረንሳውያንን የሚመለከት ማንኛውንም ጉዳይ ለመቀበልና ለመስማት ግዴታ ይኖርባቸዋል። ቀደም ባሉት ጊዜያት፣ ቆንሲሎቹ ሥልጣናቸውን በተወካይ እንደራሴው ላይ ለመጫን ይሞክሩ ነበር። ይህ ድርጊት ግን፣ ውጤቱ መጥፎ ነበር። ሙሴ ማይሌ ሥራውን ለመጀመር ሲመጣ፣ ማህበረሰቡ ያደረገለት አቀባበል ቀዝቃዛ ነበር። ከርሱ በፊት የነበሩት ቆንሲሎች ተመርጠው የወጡት ከራሱ ከማህበረሰቡ ውስጥ ሲሆን የርሱ ሹመት የመጣው ግን ከቬርሣይለስ ነው። ስለዚህ፣ ከመነሻው ሙሴ ዴ ማይሌ፣ የተወካይ እንደራሴውን የግል ድጋፍ ለማግኘት ደፋ ቀና በማለት ጥረት አድርጓል። በዚያን ጊዜ ተወካይ የነበረው ግለሠብ ብሬሎት ይባላል። ይህ ወፍራም ነጋዴ፣ ካይሮ ውስጥ ከሚካሄደው የሃር ንግድ ተካፋይ የነበረና ሥራውን የጀመረውም ሊዮንስ በምትባለዋ የፈረንሣይ የሃር ከተማ ውስጥ ነበር። ሃብታም ቢሆንም፣ የሚያስፈልገውን ነገር በተመለከተ ሲበዛ ቆጣቢ ነው። እንደሚወራው ከሆነ፣ የወለዳቸው ልጆቹ፣ በቤት ውስጥ ለማኝ

እንኳ የሚጠየፋቸውን የተበሳሱና የተቀዳደዱ ልብሶችን ይለብሳሉ። ቅንጦትን በተመለከተ ደግሞ፣ ፍፁም አባካኝ ሰው ነበር። ሊያስከብረውና ከፍ ከፍ ሊያስደርገው ከቻለ፣ የሃብቱን መጠን ማሣወቅ ውድ አይሆንበትም ነበር። በተለይም ከፍ ማለቱንና ክብሩን ሊሠጠው በሚችለው ካይሮ ውስጥ በሚገኘው አንድ እውቅ ሰው ዘንድ ከሆነ ችግር የለበትም። ይህም ሰው ቆንሲሉ ነው።

ስለዚህም፣ ሙሴ ማይሌ፣ በሚቀጥለው ቀን የኢትዮጵያን አምባሳደር ለመቀበል በነበረው ዝግጅት ፊቱን ወደ ብሬሎት መለስ ማድረጉ፣ ሙሉ በሙሉ ተገቢ ነበር። እያደገ የሚታየውን እውቅናውን ከፍ ከፍ ከሚያደርጉለት መገልገያዎች አንዱ፣ ዳሚየታ ከተማ ውስጥ፣ ብሬሎት፣ ከአንድ የባንክ ሰራተኛ የገዛትና ጣሪያዋ ወደ ኋላ ሊታጠፍ የምትችል ውብ የእንግሊዝ መኪና ነች። ምስኪኑ እንግሊዛዊ፣ ኪሣራ ሲገጥመው ወደ ማርሴይ ሊያደርሰው በሚችል መርከብ ላይ ለመሣፈር እንባ በአይኖቹ እንደሞላ መኪናዋን ባልሆነ ዋጋ ሸጣት።

ብሬሎት፣ ለምክክር በሚል ወደ ቆንስላው ጽህፈት ቤት ከሰዓት በኋላ በተደጋጋሚ ተጠርቶ ተመላለሰ። ምሽት ላይ የተቀባዮቹ ስም ዝርዝር ተጠናቀቀ። ከፍተኛ ሰው መምጣቱን የሚያናፍሰው ወሬ በማህበረሰቡ መንደር ውስጥ ተሠራጨ። ጥቂቶቹ ፖንሴ መመለሱን ያወራሉ። ብዙ ነጋዴዎች፣ እልመስለን አለ በሚል አኳኋን በቆንስላው ዙሪያ ማንገርበብ ጀመሩ። ነገር ግን፣ በሚቀጥለው ዕለት አንድ ከፍተኛ ባለስልጣን ለመቀበል ሙሴ ዴ ማይሌ እየተዘጋጀ ስለሆነ፣ ሁላቸውም በየቤቶቻቸው እንዲቆዩ፣ በመንገድም ላይ አንዳችም መንፈስ የሚረብሽ ነገር እንዳይፈፅሙ፣ የተባለውን አምባሣደር ለመቀበል አንድ ጓድ በመኪና እንደሚወጣ፣ በዚህም ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉት በዝርዝር የተመዘገቡት ብቻ እንደሚሆኑ ሙሴ ማቼ ወጥቶ ማሣሰቢያ ሰጠ።

በሚቀጥለው ዕለት ጧት፣ ጆን ባፕቲስት በሚያስደስት ስሜት፣ ሌሊቱን ሙሉ ባገኘው ሰላማዊ ዕንቅልፍ ይበልጥ ተጠናክሮና ብቁ ሆኖ ነቃ። ያለፈውን ዕለት ሁኔታዎች መልሶ መላልሶ ፈተሻቸው። አሊስንም በጥድፊያ አለማየቱ ለበጐ ሣይሆን አይቀርምና ፍራንቾይዝ ያመጣችለት ዜና ድንቅ እንደነበረ ደመደመ። ቆንሲሉ ያደረገለትን አቀባበል በተመለከተም፣ ይጠብቀው የነበረው ነውና እቅዱ ግቡን መትቷል። ከዚህ በኋላ አቀባበል ከሚያደርገው ሠልፈኛ ጋር በትህትና ሄዶ አምባሣደር ሙራድን ይቀበላል። ከዚያም እርመናዊውን፣ አስቀድሞ በነደፈለት መንገድ እየመራ ይወስደዋል። ቆንጆ ቀይ ሙሉ ልብሱን፣ ትናንሽ



ቀዳዳዎች ያሉበት የሚመስል ንድፍ ባረፈበት ለስላሣ ሸሚዝ ላይ ለብሷል። በቁም ሣጥኑ ውስጥ አስቀምጦት የነበረውን ባርኔጣውን እራግፎ አጠለቀ። ጐራዴውን በጐኑ ላይ ታጠቀና ፈረሱን ሊጭን ወጣ።

እርሱ ቆንስላው ግቢ ሲደርስ፣ ተቀባዩ እድምተኛ ተሰብስቦ ቆይቷል። ከበላይ የሚታየው የፈረንሣይ ቆንሲላ ግቢ ሃላፊ የሆነው፣ ሙሴ ፍሌሃው ነበር። ምንም እንኳ ከሙሴ ዴ ማይሌ ጋር ተመሣሣይ የሆነ ዲፕሎማሲያዊ መደብ አባል ቢሆንም፣ በጣም ዝቅ ባለ ደረጃ የሚሠሩ ተራ የሂሣብ ሥራና ደብዳቤዎችን ከመላክ ሌላ ሲሠራ፣ ጆን ባፕቲስት አይቶት አያውቅም። ሰውዬው፣ ጥልፍ ያለበት ሙሉ ልብስ ለብሶና ላባ የተሠካበት ባርኔጣ አድርጓል። በህይወቱ እንዲህ አምሮ አያውቅም። በስተቀኙ፣ የቆንሲሉ ዋና አስተርጓሚ፣ ሙሴ ፍሬሴቲ አለ። አስተርጓሚው፣ሙያውን በከተማው ውስጥ በመለማመድ፣ የንግድ ሥራ ትርጉሞችን እየሠራ የመኖሪያ ገቢውን ያገኛል። አንዳንድ ጊዜ፣ ቆንሲሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሻ የትርጉም ስራ እየሠጠው በርሱና በኦቶማን ባለስልጣኖች መካከል የሚተላለፉ ኦፊሴል ደብዳቤዎችን እንዲተረጉም ሾሞታል። ከሙሴ ፊሌሃው በስተግራ፣ ለንጉሡ ተብሎ ቀሚስ በለበሰ ፈረስ ላይ፣ ብሬሎት ተቀምጧል። ብሬሎትን በፈረሱ ላይ ለማስቀመጥ ብዙ ሰዎች ተሸክመውታል። የብሬሎት ግዝፈት የመጣው፣ የሠውነት መገጣጠሚያዎችን በሚያሣብጥ በሽታ ነው። ይሁን እንጅ፣ በቡኒው ረዥም ሠው ሠራሽ ፀጉሩና በሁብቱ ምክንያት በለበሠው ሙሉ የሃር ልብስ የተነሣ፣ የመጠኑ ልኬት ጥሩ ነው። እርሱን ተከትሎ መኪናዋ አለች። ከመኪናው ውስጥ ከነጅው በስተቀር ሌላ ተሣፋሪ የለበትም። በመልስ ጉዞ ላይ ብሬሎት ከአምባሣደሩ ጐን የመቀመጥ ክብር ይኖረዋል። በመጨረሻም፣ ዝቅተኛ ጥራት ባላቸው ፈረሶች ላይ፣ በሁለት ተርታ የተቀመጡ ነጋዴዎች አሉ። የነዚህ ነጋዴዎች ምርጫ ረዥም ድርድር ተደርጐበታል። ሁለቱ ቬኔሲያውያን በዚህ አጀብ ውስጥ የመሣተፍ እድል ያገኙት እልፍኝ ታዳራሽ የሆነውን ቤታቸውን ለአቢሲኒያው ባለስልጣን ማረፊያነት ስለሠጡ ነው። የፕሮቶኮል ደረጃን በተመለከተ በተደረጉት ውይይቶች፣ አንድ ነጥብ ግን ያለምንም ጭቅጭቅ ተቀባይነት አግኝቷል። ፖንሴ የመጨረሻውን ስፍራ ይይዛል። እርሱም ይህን ቦታ በፈቃደኝነት ተቀብሎታል። ደህ አነስተኛ ቁጥር ያለው ሰራዊት በአራት ሰዓት ላይ ተንቀሣቀሰ። ብዙም ሣይቆይ የመልዕክተኛውን ጓዝ ያገኛሉ። ወዲያውም ተቀባዮቹ አጅበውት፣ በቆንስላው ሠገነት ሥር በማለፍ ወደ ማህበረሰቡ ሰፈር ይመለሣሉ። ሙሴ ዴ ማይሌ መልዕክተኛውን የሚቀበለው እዚያ ነው። ዲፕሎማቱ፣ የሹመት ደብዳቤውን አቅርቦ እስኪያስረክብ ድረስ ምንም ዓይነት የቅርበት ንክኪ ማድረግ

ክልክል ነው። አምባሣደሩም፣ ባሊያኖች በሚኖሩበት የፈረንሣውያን ማህበረሰብ መኖሪያ ውስጥ «የቬኒስ ወረዳ» እያሉ ወደሚጠሩት ቤት ያመራል።

የቁርኮችን አትኩረት ላለመሣብ ሰልፈኛው አሮጌ ካይሮን ትቶ በመከላከያ ምሽጉ ግድግዳ ስቋርጦ ተጓዘ። ምክንያታቸውን ባያውቁም ደማቅ ሰልፎች ሲደረጉ፣ ቱርኮች ሁልጊዜም ይጠራጠራሉ። ሠራዊቱ የድመት በር በሚባለው መውጫ አድርጎ በአቅራቢያው ወዳለው ቀበሌ ሲደርስ፣ በምድረበዳ ውስጥ እየተጓዘ መሆኑን አወቀ። ከከተማው አጥሮች አንድ ማይል ከአሩብ ያህል ርቀት ከተጓዙ በኋላ ቆሙ። ይህ ሥፍራ ፖንሴ ከትናንት በስቲያ በጨረቃ ብርሃን በፈረስ ላይ ሆኖ የተጓዘበት የቤተመቅደስ ቦታ ነው። ቀኑ ሞቃት ነበር። ከምድረበዳው የሚመጣው ነፋስ የአቧራ ደመና ስላስነሣ አይኖቻቸውን ይቆረቁራቸው ጀመር። ብዙም በተንተን ሣይሉ፣ የእድምተኛው አባላት ጥላ በመፈለግ መዝናናት ጀመሩ። የአገሩ እይታ ያልተለመደ ዓይነት ነው። ከወደምድረ በዳው በኩል በነፋስ እየተጠረጉ የተፈጠሩ ታላላቅ የግሪክ ምሰሶዎች ሽቅብ አስግገው ይታያሉ። ከበስተኋላቸው ደግሞ በፈረሶቻቸው ላይ በፀጥታ የተቀመጡና እንቅስቃሴ አልባ የሆኑ ፈረሰኞች፣ በሃብታም ልብሶቻቸውና በረዣዥርም ሰው ሰራሽ ፀጉሮቻቸው ሥር በላብ ተዘፍቀው ይታያሉ። ጥቂቶቹ አድማሱን ባለማቋረጥ ይመለከታሉ። ሌሎች ደግሞ ራሱ ላይ ጥምጣም ያደረገ ሽማግሌ እረኛ ያለ ዓላማ የሚነዳቸው በጐች ያንጠባጠቧቸውን ጥቋቁር በጠጦች በመቁጠር ትኩረታቸውን በዚያ ላይ አድርገዋል።

ጥበቃው በመቀጠሉ፣ ምናልባት አስቸጋሪ ጥያቄዎች ያቀርቡ ይሆናል በሚል፣ ፖንሴ ስለተጨነቀ ከፊት ለፊት ያለውን መንገድ ለመቃኘት እንዲቻል ሃሣብ አቀረበ። ፈረሱን ኮርኩሮ ለአንድ ሰዓት ያህል ጋለበና ምንም ሳያይ ቀስ እያለ እየሰገረ ተመለሰ።

የዕለቱ ከሰዓት በኋላ፣ በሰላም እየተገባደደ ነው። ባለስልጣኖቹ ከፈረሶቻቸው ወርደው የደረቧቸውን ኮቶቻቸውንና ጃኬቶቻቸውን አውልቀው በሸሚዞቻቸው ሆነው፣ በውሃ ጥም ተቃጥለውና ቁጣቸውን ሊሰነዝሩበት ተዘጋጅተው አገኛቸው።

«ሊገባኝ አልቻለም፣አንዳች አስቸጋሪ ነገር አጋጥሞ መሆን አለበት።» አለ።



በዚህ ጊዜ ሌሎች፣ ሌላው ቀርቶ አምባሣደር የተባለው ሰው ከቶውንም ስለመኖሩ መጠራጠር መጀመራቸውን ተረዳ። እነርሱ ሰውዬውን ስለማያውቁት ቢጨነቁም፣ ፖንሴ ግን ስለሚያውቀው በሌላ ምክንያት የሙራድ እጣ ፈንታ አሣሰበው።

«አሁን አሥር ሰዓት ሆነ፣ ወደ ቤት እንድንመለስ ሃሣብ አቀርባለሁ። ምናልባት መልዕክተኛው በምሽት የሚደርስም ከሆነ ጠብቀው እንዲያሣውቁን ሁለት ጠባቂዎችን እንልካለን» አለ ጆን ባፕቲስት።

ባለው ሁኔታ ምላሹ ጥሩ እንደማይሆን ስለተረዳ ላቀረበው ሃሣብ የሚሰጠውን ምላሽ ሳይጠብቅ ፈረሱን ኮርኩሮ ወደ ካይሮ ነጉደ።

# 4

በተለይ በዚያን ዕለት፣ የድመት በር የሚባለውን የሚጠብቁት ሁለቱ ተረኛ ሽማግሌ የአረብ ዘቦች፣ ሰውነታቸው ሁሉ በክብር ምልክቶች ተሞልቶ፣ በጣም ተደስተው ነበር:: የሚሊሺያዎች አዛዥ፣ ለወታደራዊ ጀግንነታቸው ምስጋናውን ለማሳወቅ፣ በዚህ ሰላማዊ ጣቢያ ላይ ሕይወታቸውን ሙሉ እንዲቆዩ ፈቅዶላቸዋል:: በዚህ ጊዜ፣ ካይሮ ከውጭ ከሚያጋጥማት ወረራ ይልቅ የውስጥ የሕዝብ አመፅ ይበልጥ ያስፈራት ነበር:: በየበሩ ያሉት ዘበኞች ዋናው ሃላፊነታቸው፣ በምሽት፣ ጅቦችና ሌሎችም አራዊት ከምድረበዳው ተነስተው ወደ ከተማ እንዳይገቡ በሮችን መዝጋት ነው:: ቀን ሲሆን ግን፣ ሁለቱ ሽማግሌዎች ከመሬት በታች ባለው ጥላ ቦታ ላይ ምንጣፋቸውን ዘርግተው፣ እግሮቻቸውን አመሣቅለው በመቀመጥ ቼዝ ሲጫወቱና በቅርባቸው ካለ ሱቅ አንዲት ባዶ እግሯን የሆነች ትንሽ ልጅ የምታመጣላቸውን ሻይ እየጠጡ ይውላሉ:: ከጧቱ ሦስት ሰዓት ሲሆን በሕዝብ ትርምስ መሃል ሰፊ ቦላሌና እንደ ኩርዶች አለባበስ ሰፋ ያለ የወገብ መታጠቂያ የለበሰ ሰው ወደ ከተማዋ ሲገባ ያያሉ:: ሰውዬው ሥጋው የደለበና በምስኪኗ በቅሎው ላይ ከባድ ጭነት ነበር:: እንስሳይቱ፣ ወደ በሩ ከሚያመራው መውጫና መውረጃ መሃል ስትደርስ ቀጥ ብላ በመቆም አንዲት እጥቅ እንኳ ላለመንቀሳቀስ አሻፈረኝ አለች:: ሰውዬው፣ በፍጥነት ተንቀሣቅሶ ብዙ ቦታ ስብርብር ባለና በቅሎይቱን ሊያስገድዳት በማይችል በደካማ አርፖሜ ይገርፋት ጀመረ:: ማንም ሰው ኑበያዊ ናቸው ሊል የሚችላቸው፣ነገር ግን ቀርፃቸው ለየት ያለ፣ ሦስት ጥቋቁር ሰዎችም የበቅሎይቱን ውዶላ ይዘው ቢገፏትም እንስሳይቱ በቁጣ እነርሱ ላይ ተሽከርክራ ዞረችባቸው:: የመጨረሻው ጥረታቸው ግን እንስሳይቱ እስከነአካቴው እንዳትተኛባቸው መጠበቅ ሆነ:: በዚያው መስመር ፊንጠር ብለው በሰላም አብረው የተቆራኙ ሦስት አህዮች እምቢነገር ተጭኖባቸዋል:: ሌላ አንድ በቅሎም እንደሁ በመንገዱ ዳር ባሉት ድንጋዮች መሃል ብቅ፣ ብቅ ያሉትን ስለታም ሣሮች ትመለከታለች::

በመጨረሻም ሰውዬው ከበቅሎይቱ ላይ ወረደና ወደ በር ጠባቂዎቹ ተራምዶ ፊት ለፊታቸው ሲደርስ ቆመ:: ከበቅሎው ወርዶ አስር እርምጃዎች በመራመዱ ቁና ቁና ይተነፍሣል::



«አ! ውድ ወዳጆች፣ ወንድሞች» አለ እያለከለከ «ይህች በቅሎ እዚህ ድረስ እንድትራመድልኝ ልትረዱኝ ትችላላችሁ:: ዕድሜዋን ሙሉ በከተማ መግቢያ በር አልፋ የማታውቅ እንስሳ ነች:: በጣም ስለፈራች ምንም ዓይነት ምክንያት ማዳመጥ አትፈልግም»

ሰውዬው የሚናገረው አረብኛ የሶርያ ዘዬ ነው

«እንዲያው ለመሆኑ እናንተ ከወዴት ናችሁ? በከተማችሁ መግቢያ፣ በሮች የሏችሁም?» ሲል አንዱ ዘበኛ ጠየቀ::

«እኔ የመጣሁት፣ አናቶሊያ ከሚገኘው ከቫን ከተማ ነው:: በዚያም ብዙ በሮች አሉን:: ነገር ግን እኔና በቅሎዬ ሁለት የተለያየን ነገሮች ነን:: ይህችን በቅሎ የገዛኋት አረቢያ ከሚገኘው ፊሊክስ፣ ከአንድ ባላገር ላይ ነው::»

«አሃ! እንግዲያውስ ማንበብ የማትችለው በቅሎይቱ ነች ማለት ነው!» አለ ሽማግሌው በሣቅ እየተንከተከተ

ሁለተኛው ሽማግሌ፣ የተሰጠው አስተያየት ምን አስቂኝ ነገር እንዳለበት እርግጠኛ ባይሆንም፣ በጓደኛው በሣቅ መንከትከት ተሸንፎ አብሮት መንከትከት ጀመረ:: መንገደኛው፣ ሁለቱም ሰዎች ሲስቁ ተመልክቶ፣ እርሱም አብሯቸው ቢስቅ መልካም እንደሚሆን አሰበ፣ የሣር ጥምጣሙ ከጭንቅላቱ ላይ እስኪወድቅ ድረስ ከልቡ ፍርስ አለ::

«ከዚህች ማንበብ ከማትችል እንስሳ ጋር እንግዲያውስ ወዴት ነው የሚሄዱት?» ሲል የመጀመሪያው ሽማግሌ ጠየቀ:: ሣቁ ጣሪያ የሚደርስ ስለነበረ በአካባቢው የነበሩ ተላላፊዎች ቀልዱን ለመካፈል ተሰበሰቡ::

«ወደ ፈረንሣውያን ቆንሲል» አለ መንገደኛው

«እሃ! ምናልባት በቅሎዎ ላቲንኛ ማንበብ መቻልዋን ለማወቅ ፈልገው ነው!» አለ ሌላኛው ሽማግሌ:: በዚህም ሁለተኛ ዙር ሣቅ ሲቀጥል፣ ባለ በቅሎውም በደስታ የሣቃቸው ተካፋይ ሆነ::

ፀጥታ እስኪሰፍን ድረስ ሁለት ወይም ሶስት የተለያዩ ጉዳዮች በዚህ ዙሪያ ሲያጫውቷቸው ቆዩ:: በር ጠባቂ ዘበኞችም በተጨማደዱ አይኖቻቸው ላይ የተጠራቀሙትን

እምባዎች ጠራረጉ፡፡ አንዳችም የጥቃት እርምጃ ለመሰንዘር ሣይቃጣ፣ ይህን ያህል የመሣቅ ዕድል እንዲያገኙ ላደረጋቸው ለዚህ አስደሳች እንግዳ ሰው ርህራሄ ተሰማቸው፡፡

«ስምዎ ግን ማን ይባላል ወንድም?» አለ ከዘበኞች አንዱ

«ሙራድ ነው፣ ወዳጄ»

«ጥሩ እንግዲያው ሙራድ፡፡ እኛ በቅሉዎን መቼም አንነብልዎትም፡፡ እነዚህን እንሰሳት አውቃቸዋለሁ፡፡ ጥሩ አይደሉም፡፡ ይልቅስ ከዚህ በጣም የተሻለ ልናደርግ እንችላለን፡፡ ምክር ልንሰጥዎ እንፈልጋለን፡፡ ጥሩ ምክር እንሰጥዎታለን፡፡ እሺ?»

«ጆሮዎቼ ያዳምጣሉ» አለ ሙራድ በመበሳጨት ስሜት

«በዚህ መግቢያ በር ካለፉ ከተማዋን በሞላ ማቋረጥ ይኖርብዎታል፡፡ ከዚህ ይልቅ፣ በትናንሽ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች በኩል ባለቅስት መግቢያዎች አሉ፡፡ ማንበብ የማትችለው በቅሉዎ እነዚያ በሮች መግቢያዎች እንደሆኑ ታውቅና ትሄድልዎታለች፡፡ ስለዚህ ጥሩው ነገር በቀጥታ ወደ ቀኝ ታጥፎ ዞሮ መሄድ ነው፡፡ ከዚህ ከመውጣጫው በታች አሾሃማ የፍሬ ዛፍ ይታይዎታል?»

«አዎን አየዋለሁ»

«እዚያ ሲደርሱ ወዲያውኑ ትንሽ እልፍ ብለው ወደ ቀኝ ይታጠፉና፣ በከተማው ዙሪያ የምትዞረውን የእግር መንገድ ይያዙ፡፡ ሌሎች መግቢያዎችን በርቀት ያያሉ፡፡ ስድስት ያህሉን ከቆጠሩ በኋላ ሰባተኛው አጠገብ ሲደርሱ ወደዚያው ያምሩ፡፡ መግቢያው እንደዚህኛው ሳይሆን ትልቅ የብረት ፍርግርግ በር ስለሆነ፣ በቅሉዎን አያስፈራራብዎትም፡፡ በዚያ በኩል ይለፉና አንድ መቶ ያርድ ያህል ከተጓዙ በኋላ፣ በግራ በኩል የፈረንሣውያንን መኖሪያ ያኛሉ»

ሙራድ፣ ለሁለቱ ሽማግሌ ዘበኞች ሞቅ ያለ ምስጋና ካቀረበ በኋላ የሰጡትን አስተያየት ተቀብሎ ባሳዩት አቅጣጫ ጉዞውን ጀመረ፡፡ በዚህ ጊዜ በቅሉይቱም ሙሉ ትብብርዋን አሣየች፡፡

በድመት በሩ ስር ተሰብስቦ የነበረው ሕዝብም ቀስ በቀስ ተበተነ፡፡ የበሩ ጠባቂ ዘበኞች ሁኔታውን እያስተዋሉ በመሣቅ ላይ ሳሉ፣ ከአንድ ሰዓት በኋላ የፈረንሣይ ፈረሰኞች በአስደሣች



የሰምሰማ እርምጃ ሲያልፉ ተመለከቱ፡፡ ፈረሰኞቹ ባለቀለማት ጃኬቶችና ሰው ሰራሽ ፀጉሮችን ለብሰዋል፡፡ ውድ ዕቃዎችን በተጫኑት ፈረሶች መካከል አንፀባራቂ ቀለም የተቀባችና የተወለወለች ጥቁር መኪና አለች፡፡ በግንቡ በኩል ቁልቁል ወጥተው ከከተማዋ ፈጥነው ራቁ፡፡

ለቆንስላው አትክልተኛ፣ ወደ ዋናው ሕንፃ መግባት ፍፁም የተለየ ነገር ነው፡፡ ሽማግሌው ሰውዬ፣ የካይሮ ተወላጅ የሆነ ቅብጣዊ ክርስቲያን ሲሆን ታማኝ አሽከር ነው፡፡ ምሽት ጀምሮ እስከ ለሊት ድረስ፣ በደካማ አቅሙ፣ በዝግታና በፀጥታ በቀጫጭኖቹ ማቋረጫዎች ላይ እየተጓዘ፣ ከነሃስ የተሠራውን የውሃ ማጠጫ ይዞ፣ በደረቁ ቅጠሎች ላይ ውሃ እንደዝናብ ሲያፈስስባቸው ከሚሰማው የማጉረምረም ድምፅ በስተቀር፣ አንዳችም ኮሽታ አይሰማም፡፡ በዚህ ቀን ግን ይህ አትክልተኛ ዕድል አልነበረውም፡፡ የቆንስላው ግቢ ባዶ ነበር፡፡ የሙሴ ዴ ማይሴ ሾፌር፣ የቀንና የሌሊት ጠባቂና ሁለቱ ወንድ አሽከሮች ሁሉ ኤምባሲውን ለመቀበል ከወጣው መልዕክተኛ ጋር ተከትለው ሄደዋል፡፡ ከራሱ ከሽማግሌው አትክልተኛ ከገብርኤል በስተቀር፣ ማንም ሰው በቤቱ ውስጥ አልቀረም፡፡ መልዕክቱን ሲቀበለው የሚችለው ሰው በማጣቱ፣ ከበር በር እየሄደ፣ በመጨረሻም እጁግ እያቅማማ ከቆንሲሉ ጽህፈት ቤት በር ደረሰ፡፡ ሙሴ ዴ ማይሴ፣ ሰው ሰራሽ ፀጉሩንና አንፀባራቂውን የሃር ጃኬቱን በእንጨት መስቀያ ላይ አስቀምጧል፡፡ እርሱ ግን ወንፊት የመሰለ ሸሚዝና የሃር ባላሴ ለብሶ ወደፊትና ወደኋላ እየተንጉራደደ ቅንድቡን በመሃረብ ይጠርጋል፡፡ ሙሴ ማቼ፣ በአንድ ወንበር ላይ ኩርምት ብሎ፣ ትዕዛዝ ወይም የውይይት ርዕስ ሊሆን የሚችል ቃል እንዲተነፈስ ይጠብቃል፡፡ የአትክልተኛውን የፈራ ተባ አገባብ አስቀድሞ ያስተዋለውም እርሱ ነበር፡፡

«እና ይህ ደግሞ ምን ይፈልጋል?» ሲል ቆንሲሉም በተራው እንዳስተዋለ ጠየቀ፡፡

ሙሴ ማቼም፣ አረቢኛ ብቻ የሚያውቀውን ሽማግሌ በቋንቋው ጠየቀው፡፡

«እንደሚለው አንድ ሰው ሊያይዎት ይፈልጋል፡፡ ክቡር ሆይ»

«አንድ ሰው!» አለ ቆንሲሉ በሰበጣ ፈረግታ፡፡ «እንዴት ያለ የሚገርም ነገር ነው፡፡ አንድ ሰው ከማለት ይልቅ ለምን ዱባ ወይም አይነ ትልልቅ ዝንጀሮ አይሆንም? ለዚህ ጅል፣ ከሁሉም በላይ ስለሚያብቡት ተክሎቻችን ብቻ ጥንቃቄ እንዲወስድና ሌላውን እንዲተው ንገረው፡፡

እናም ዳግመኛ እዚህ ሳየው አልሻም። አንድ ሰው እኔን የሚጠይቅ ከሆነም በአጭሩ ስራ ላይ ነው ይበለው።»

የቆንሲሉ መልስ ተተርጉሞለት ከሰማ በኋላ የሽማግሰው ሰው ፊት በንዴት ልውጥውጥ አለ።

«ሄዶ እንደሚነግራቸው፣ ግን የሚሰጣቸው መልስ ሰዎቹን ከርሱ መስኮት ፊቅ እንዲሉ ያደርጋቸው እንደሆነ እንደሚጠራጠር ነው ሚናገረው።

«እንደሚነግራቸው? ለመሆኑ ስንት ናቸው?» አለ ቆንሲሉ።

«አራት ናቸው። ጭነት ያለባቸው አህዮችና በቅሎዎች አሉ» አለ ሽማግሌው ሰው።

«ለመሆኑ ምን ይመስላሉ? ቅፍለት ይሆን?» ሲል ሙሴ ዴ ማይሌ ጠየቀ።

«አዎን፣ ከፊሰን ቅፍለት ነው። ይሁን እንጂ በዚህ አካባቢ እንዲህ ያለ ነገር አይቼ አላውቅም»

«ለመሆኑ፣ ወደ ማህበረሰቡ ሰፈር በሚያስገባው በር ላይ የሚገኘው ዘብ ለምንድን ነው እንዲገቡ የፈቀደው?»

«ምናልባት ሰውዬው ለኔ የነገሩትን ለዘቡም ነግረውት ይሆን ይሆናል»

«ምን ነበር የተናገረው?»

«የአቢሲኒያውያን ንጉሥ አምባሣደር መሆናቸውን ነው» አለ አትክልተኛው በአክብሮት ፈገግታ

ሙሴ ማቼ አመዱ ቡን አለና የሽማግሌውን ቃሎች ተረጐማቸው።

«ቸሩ ጌታዬ!» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ

ለአፍታ ያህል ዲፕሎማቶቹ መናገር ተስኗቸው ቆዩ። ከፍተኛ ጥንቃቄ በማድረግ ወደ መስኮቱ ተራመዱ። ተራ በተራ ወደውጭ ተመለከቱና በቅፅበት ምልስ አሉ።

«ሊሆን የሚችል ነው እንዴ?» አሉ ሁለቱም በጋራ

በድጋሚ በመስኮቱ በኩል ተመለከተ። በታች በኩል በሚገኘው ማዕከላዊ መንገድ ዳር፣ በመደዳ በተተከሉት ዛፎች ሥር መከረኞቹ የክብር ዘበኞች ቆመዋል። ሰውነታቸው የተንግጠበና የተመሳለጡ፣ ጫንቃቸው የቆሳሰለ ስለሆነ ትናንሽ ወፎች የሚያነቁሩት፣



እንዲሁም ካይሮ ውስጥ ዝቅተኛው ውሃ አመላላሽ የማይፈልጋቸው በቅሎዎች ይታያሉ። እነዚህ ምስኪን እንስሳት መጠናቸው ትልልቅ የሆኑ ጭነቶችን ተሸክመዋል። ጭነቶቹ በጀርባቸው ላይ በቃጫ ገመድ ጥፍር ተደርገው ሲጫኑ፣ በጣም በቆሰለው አካላቸው ላይ እራፊ ጨርቅ ተደርጎባቸታል። ከጥጥ የተሰራው የሰበሱት ሸሚዝ የበረሃውን አፈር የመሰለ ሦስት ጥቋቁር ወንዶች መናገር ተስኗቸው ይጠብቃሉ። አንድ ዛፍ ተደግፎ መሬት ላይ የተቀመጠው ሙራድ ጫማውን አውልቆ የእግሩን መዳፍ በሃይል ያከካል።

«ማቼ» አለ፣ ሌሎችን ለማዘዝ የተፈጠረውና ሳይታሰብ ድንገት ቢጠራ የማይበሣጨው ቆንሲል። «ውረድና የቆንሲሉን አክብሮት ግለፅለት። ከዚያም ሁኔታውን አስረድተኸው ወደተዘጋጀለት የቬነስ ወረዳ ውሰደው።»

ፀሐፊው ወዲያውኑ ወጣ። አትክልተኛው እየመራው ሄዶ ሹልክ ብሎ ጠፋ። ሙሴ ዴ ማይሌ፣ ብቻውን ቀረ። ቀና ብሎ የንጉሱን ሥዕል በዓይኖቹ ቀረፀና፣ ወዲያውኑ፣ የሁሉም የበላይ ለሆኑት ንጉሠ ነገስትና ለዋናው ሚኒስትር ለፖንቻርትሬይን ብልህነት ያለው ታላቅ አክብሮት መንፈሱን ሞላው። ዋናው ሚኒስትር በቅርቡ የላኩለትን ደብዳቤ በምስጋና እምባ አስታወሰ።

በዚህ መሃል፣ ማቼ፣ እስከዚህ ጊዜ ድረስ እግሩን ያክክ ወደነበረው ወደ ሙራድ ዘንድ ደረሰ። አትኩረቱን ለመሣብ ሲል እንደማሳል አደረገ።

«ኦ ጓደኛ አገኘን ማለት ነው» አለ፣ አርመናዊው ጫማውን መልሶ እያጠለቀና ተነስቶ እየቆመ

ሙሴ ማቼን ለመጨበጥ የእርግ ጣቶቹን ሲያክክበት የነበረውን እጁን ዘረጋ

«ሙራድ እባላለሁ። ከኢትዮጵያ የመጣሁ አምባሳደር ነኝ»

«እጅግ ሞገስ ያለዎ እንኳን ደህና መጡ።» አለ፣ ፀሐፊው የእጅ መጨባበጡን ለመከላከል ከወገቡ በመጠኑ ዝቅ ብሎ።

«እሺ፣ እሺ፣ ተነሱ» አለ ሙራድ በመጨነቅ። «እራሣችሁን እየጐዳችሁ ነው። ተነሱ ተነሱ፤ እሺ እባክዎን ይንገሩኝ፣ እርስዎ በርግጥ ቆንሲሉ ነዎት?»

«አይደለሁም፤ የተከበሩ፤ ክቡር ቆንሱሉ ክቡርነትዎን እንኳን ደህና መጡ እንድልዎትና አክብሮታቸውንም እንድገልፅልዎ ልከውኝ ነው። ኦፊሴላዊ የሆነ የሚቀበልዎ የመልዕክተኛ ቡድን ልክንልዎ ነበር። ነገር ግን ሳያገኝዎት ቀርቶ ነው»

«በዚህች ደደብ በቅሎ ምክንያት ነው» አለ ሙራድ፣ ፍንክች የማትለዋን እንስሳ እየረገጣት። «ምንም ነገር የምትሰማ አይደለችም። በዚህም የተነሣ በግንቡ ዙሪያ መንገዱና በብረት በሩ በኩል ዞሬ ማለፍ ነበረብኝ። ምን ይደረግ! መድረሱን እንኳ ደርሰናል፣ መንገዱም ደግሞ አታምነኝም በጣም ረዥም ነው። ለመሆኑ ፖንሴ የት ነው?»

«እርሱም ከተቀባይ አድምተኞች ጋር ነው»

«ከአድምተኞች! ታዲያ እንዴት ሳደርግ ነው? ይህን ከተማ በጭራሽ አላውቀውም። ማንም ሰው ቢሆን ማረፊያ ሊሰጠኝ አይችልም»

«ማረፊያ አይሰጠኝም? ይህማ ለክቡርነትዎ ተዘጋጅቷል። እኔን ብቻ ይከተሉኝ»

«እውነት ነው? በል፣ ይህ ጥሩ ዜና ነው። እና የምመገበውም ትሰጠኛለህ?»

«የሚበላ፣ የሚጠጣ፣ ክቡርነትዎ የሚሻውን» አለ ሙሴ ማቼ ይበልጥ እየተደነቀ-

«እግዚአብሔር ታላቅ ነው። በል እሺ እከተልሃለሁ። እናንተ ሦስታችሁ። ወዲህ ኑ። እነርሱ አቢሲኒያውያን ናቸው። በተፈጥሯቸው ጠንካራ ህዝቦች ናቸው። ነገር ግን ለኔ የተሰጡኝ ሶሶት ሰነፎች ይመስሉኛል። ኑ ተከተሉን፣ ተከተሉን»

በቅሎዎችንና አህዮችን እንቀሣቅሰው፣ የማህበረሰቡን ሰፈር በሙሉ አቋረጡ። ቆንሲሉ፣ በዚያን ዕለት በመንገድ ላይ የሕዝብ እንቅስቃሴን በመከልከላቸው፣ ማቼ፣ ራሱን በራሱ እንኳን ደስ ያለኝ ይላል። ምንም እንኳ በነበሩት ጥቂት ምስክሮች ይህን ያህል ባይሰጋም፣ ከርሱ በፊት የነበረው ሰው ግን ከዕለታት አንድ ቀን «ኦ አዎን፣ ማቼ፣ የኢትዮጵያን አምባሣደር ሁለት አህዮችን ሲነዳ ያየሁት መሆኔን አታውሣለሁ» ብሎ ታሪኩን ያበላሸበት ይሆናል።

በመንገዱ ዳር ከተተከሉት በአንደኛው ዛፍ አጠገብ አረፍ ለማለት ሙራድ ቆመ። ይሁን እንጂ፣ በጉረሮው ውስጥ እርሱ ራሱ የፈጠረው ድምፅ ይህ ዕፎይታው የሚሰጠውን ደስታ ያበላሽበታል።

በመጨረሻም ወደ ቬኑሲያውያኑ ቤት ደረሱ። የምድር ቤቱ የተወሰነው ለኤምባሲው ነበር። ቤቱ የእንጨት ቢሆንም፣ ሁለተኛው ፎቅ ግን ውብና ማራኪ በሆኑ ባለሦስት ማዕዘን



ወጋግራዎች ድጋፍ ቆሟል። በቤቱና በጉዳናው መሃከል በደንብ የተጠበቀች ትንሽ የአትክልት ቦታ አለች። አንድ አነስተኛ የጣውላ አጥር፣ የቬነስ ሪፐብሊክ ግዛት የት ድረስ እንደሆነ ለማመልከት ተስተካክሎ ታጥሯል። በዚህም ውስጥ አረንጓዴ በአረንጓዴ ላይ የሆነ፣ በመስኩ መሃል ላይ የተዘጋጀ፣ የቤተሰቡ መሰያ ቢጋሻ ላይ ተነድፎ ተቀምጧል። እንስሳቱ ሁሉ ሣሦንታቸው ከተራገፈላቸው በኋላ ወደ መስኩ እንዲገቡና እንዳሻቸው በነፃነት እንዲንቀሣቀሱ፣ ሙራድ ሙጭጭ ብሎ ለአቢሲኒያውያኑ መመሪያ ሰጠ።

አርመናዊው ወደቤት ሲገባ፣ ጫማዎቹን አወለቀና በመጀመሪያው ሶፋ ላይ ሄዶ እንዘጭ በማለት ዳግመኛ ላለመነሣት ይምል ጀመር።

ሙሴ ማቼ ሃላፊነቱን ለመወጣት ቀዝቃዛ መጠጦች እንዲመጡ መልዕክት መላኩን ገልፆ ተሰናበተ

«እና የሚበላ ነገርም ጭምር!» ሲል ሙራድ ሙከ በማለት ማቼ ከእይታ ሳይሰወር በፊት ተናገረ።

ፀሐፊው ከተመለሰ በኋላ ስለአምባሳደሩ ያልተለመደ ባህርይ ለቆንሲሉ ማብራሪያ ሰጠ። ሙሴ ዴ ማይሌም፣ አንድ በባዕድ አገር ውስጥ ሆኖ ራሱን በአድናቆት ስሜት ውስጥ እንዲገባ የሚያደርግ ዲፕሎማት፣ በጦርነት መሃል የራስ ቁሩን እንደሚያነሣ ተዋጊ ነው ሲል ነገረው።

«ከሁሉም በላይ ጥቂት ቸርነትን ልናሣየው ይገባናል። ከየት እንደመጣም አስተውል»

የእንኳን ደህና መጡ አቀባበል ከሚያደርጉ መልዕክተኞች ጋር ስማቸው ያልተጠቀሱትን ነጋዴዎች በሙሉ ለሴላ የክብር ሥራ፣ በተለይም ለአምባሣደሩ ቀለል ያሉ ምግቦችና ለስላሣ መጠጦችን እንዲያቀርቡ በሚል ለሁለተኛ ጊዜ ዝርዝር ተዘጋጀ።

«ምንም እንኳ . . . ልገልፀው» ሲል ሙሴ ማቼ ጠየቀ

«በደንብ ነዋ» አለ ቆንሲሉ። «ከነዚህ ከተከበሩ ሰዎች ለመጀመሪያው ቢሮውን እንዲያሰናዳ ንገረው»

ከሰዓት በኋላ ያለውን ጊዜ በሙሉ፣ ክብር ያላቸው ሃብታም ነጋዴዎች፣ ባልተቋረጠ መልክ በሰልፍ የገዙት አሽከሮቻቸው የፍራፍሬ ቅርጫቶችን፣ የበሰሉት ሣህኖችንና ጣፋጭ ምግቦችን ተሸክመው፣ የቬኒሲያውያኑን ቤት ሞሉት። የኢትዮጵያውን አምባሳደር በክብር ለመቀበል የከፈሉት ዋጋ ይህ ነው። በኋላ ላይ ሁሉም ነጋዴዎች ወደ ሙሴ ዴ ማይሌ

በመምጣት እንዲህ ያለ ነገር ዳግመኛ እንዲያከናውኑ እንዳይገደዱ ሲነግሩት ተጣደፉ። የተቀበሉቸውና ያስተናገዳቸው እንዲህ ያለ ቀርፋፋና ባለጌ የንጉሡ ባለሥልጣን መሆኑ ሲያምኑት ከሚችሉት በላይ ነው። ቆንሲሉ ላይ አንዳችም የመከነን ነገር ሣያሣርፉ፣ ፖንሴን የማጭበርበር ስራ ሰርቷል በሚል ከሰሱት። ይህን አይነት አስደንጋጭ ትዕይንት እየተከናወነ ሣለ፣ የብሬሎት ተወካዮች ተመለሱና ሁሉም በፖንሴ ላይ ቁጣቸውን አወረዱበት። ምን እንዳጋጠመ ከተረዱ በኋላ የሴለን መልዕክተኛ እንዲጠብቁ ያደረጋቸውን መድሃኒት ቀማሚውን መክሰሳቸውን አቁመው፣ ቅሬታቸውን የሚያስተካክልላቸውን መዝናኛ ተቀሳቀሱ። በወቅቱ ሰፍኖ የነበረውን ትርምስ በመጠቀም ጆን ባፕቲስት ከቆንስላው ሾልኮ ወጣ።

«ክቡራን፣ ፀጥታ» አለ፣ ቆንሲሉ፣ ከፍ ባለ ድምፅ። «ከዚህ በኋላ ከድካማችሁ አረፍ እንድትሉ እጠይቃለሁ። በተጨማሪም ለድጋፋችሁ አመሰግናችኋለሁ»

ሌላ የተቃውሞ ጫጫታ ተቀሰቀሰ። ቆንሲሉ በአካላዊ እንቅስቃሴው አበረዳቸው።

«ይህ ሰው የአንድ ታላቅ ንጉስ መልዕክተኛ ነው። በርግጥ ንጉሡ ለብዙ ዘመናት ከስልጣኑ ተቆራርጦ ኖሯል። ቸርነታችንንም ማሣየት ያለብንም ለዚሁ ነው። ከሁሉም ነገር በላይ የዚህ መልዕክተኛ እዚህ መድረስ በራሱ ትልቅ በዓል ነው። መልዕክተኛው በማንኛውም መልኩ ከያዘው መልዕክት በታች የሚገመት ነው። የአቢሲኒያው ንጉሥ ምን እንደሚነግሩን ነገ እንሰማለን። »

ቆንስላውን ከለቀቀ በኋላ፣ ፖንሴ፣ በቀጥታ ወደ ቬነስ ወረዳ ሙራድን ለማየት ሄደ። የቬነስያውያን የእንግዳ መቀበያ ክፍል መቀመጫዎች በሙሉ በግድግዳው የውጭ አካል በኩል በሙራድ ትዕዛዝ እንዲከመሩ ተደርጓል። በነጋዴው የእንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ የቀሩት፣ ምንጣፎችና ከባለመደገፊያው ወንበር ላይ ወርደው ወለሉ ላይ የተበታተኑት ትራሶች ናቸው። ሙራድ፣ እግሮቹን አጣምሮ፣ በመስተዋት ጨሌ በተጌጠው በትልቁ መብራት ሥር፣ ብዛት ባላቸው የብር ትሪዎች፣ አብረቅራቂ ጉድጓዳ ሣህኖች፣ ከፍተኛ ዋጋ ባላቸው ማንቆርቆሪያዎች ተከብቦ ተቀምጧል።

ጆን ባፕቲስት፣ የበቅሎዋን ባህርይና ባልታሰበ መንገድ የመጣበትን ታሪክ እንዲያወጋው ጠየቀው። የፈረንሳውያን ማህበረሰብ እንዴት እንደተቀበለው የሙራድን ሃተታ ሰማ። ሁሉም ነጋዴዎች አስነዋሪ ብልግና ያሣዩት መሆኑን አርመናዊው ይገምታል። ከእንግዲህ በኋላ እቤቱ ዱለ አድርጉ እንዲገምትና ስጦታዎችንም ካበረከተለት በኋላ ሁለቱም ያንን ማንጓጠጥና



ብልግና ሊያረግቡና ይህን ንብረት እንዴት እንደሚጠቀምበት ተወያዩ። ምንም ነገር እንደሚፈልጉት አልነበረም። በአትክልቱ ሥፍራ ያሉት በቅሎዎች ወይም ከክፍሉ የተነሣው የቤት ውስጥ ቁሳቁስ፣ ወይም በአቢሲኒያውያን ስልት ፊት ለፊት ባለው መድረክ ላይ በሚገባ በተቀጣጠለው እሣት ላይ የፈላው ቡና እንደሚፈልጉት አልነበረም።

የሙራድን ቁጣ ባባባሰው በዚህ ታሪክ ከልብ ከሣቀ በኋላ፣ በፀባዩ ላይ አንዳችም ነገር እንዳይለውጥ ጆን ባፕቲስት ነገረው። በሚቀጥለው ቀን ከቆንስላው የሚመጣ ሰው አግኝቶት ስለሹመት ደብዳቤው ቢጠይቀው፣ ምን ማለትና ማድረግ እንደሚገባው በጣም ግልፅና ትክክለኛ የሆነ መመሪያ ሰጠው።

ከዚህ በኋላ፣ ጆን ባፕቲስት ወደ ቤቱ ፈጥኖ ሄደ። ከአሊስ፣ በአንድ ወይም በሌላ መልክ መልዕክቷን ይጠብቅ ነበር። ከትናንት በስቲያ ጀምሮ ስላላያት፣ የሚያስበውም ይህን ብቻ ስለነበረ በጣም ጓጉቷል።

ፎቁን በጨለማው ውስጥ ወጣውና ሻማውን አበራው። እንደገመተውና እንደጠበቀውም አራት ቦታ የታጠፈ መልዕክት በሻማው ሥር አገኘ። መልዕክቱ ከፍራንቾይዝ የተላከ ማስታወሻ አልነበረም። ማስታወሻው የቤተክርስቲያኑ ደወል ሁለት ጊዜ እንደተደወለ በማህበረሰቡ ዋና መንገድ መጨረሻ ላይ ባለው የአትክልት ሥፍራ እንዲያገኛቸው የሚያዝዝ ነበር።

# 5

አሊስ፣ በጨለማው ክፍሏ ውስጥ ቆማ የቀጠሮውን ሰዓት ትጠብቃለች። በዚያ ምሽት፣ ብርማዋ ጨረቃ ፣አልፎ አልፎ በከባድ ደመና እየተጋረደች አለች። እንዲህ ባለ ድቅድቅ ጨለማ ሌሊት እስከመናፈሻው ድረስ በመንገዶች ላይ መጓዝ እንደማያስፈልግ ፍራንቾይዝ አስባች። በዚህም፣ ከቆንስላውና ከሰላዮቹ ቢያንስ ትንሽ ራቅ ይላሉ። ገና አመሻሽ ሲጀምር፣ ውጣቷ ልጃገረድ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማድረግ ከበቂ በላይ ጊዜ ስለነበራት፣ ወደዚያ ወደተባለው መገናኛ መሄድ የጅል አስተሣሰብ እንደሆነና ክብሯንም ዝቅ እንደሚያደርግባት ለራሷ ስትነግር ቆየች። ሰዓታት እያለፉ ሲሄዱ ግን እርሷም ይህን ሃሣቧን ልክ እንደ ሌባ ሲያጠቃህ ሲመጣ ገፍትረህ ግርግዳ ላይ እንደምትወረውረው ሁሉ አሽቀንጥራ ጣለችው። ለራሷም እንዲህ አለች። ለመሆኑ በሙሉ ልቤ አላፈቅረውም?

ከዚህ ውሳኔዋ በኋላ፣ ቀጠሮውን አፈርሣለሁ ከሚለው ሃሳቧ ይልቅ፣ አከብረዋለሁ፤ በሚለው ውሣኔዋ ርግጠኛ ነበረች። በአሁኑ ጊዜ በአዕምሮዋ ውስጥ የሚመላለስባት የክርክር ነጥብ፣ የጥንቱ የዕድገትዋ ጉዳይ ሣይሆን፤ ባለፈው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ራሷ ያገኘችው የአሁኑ አዲሱ ዕኑ እምነትዋ ነበር። ከፍራንቾይዝ ጋር በተጫዋወተችባቸው ረጅም ወራት ውስጥ፣ በጥቅም ሣይሆን በጥልቅ የስሜት ፍቅር የሚመራውን የእውነተኛ ፍቅርን ክብር ተገንዝባዋለች። ክብርን በተመለከተ ከሆነ፣ በሚገባ ልትጠብቀው የቻለችው እናትዋ ጥሩ ምሣሌ ናት። እርሷ ግን፤ እንደራሱ የግል ንብረት ሳደረጋት ሰው ባሪያው ካልሆነች ምን ልትሆን ነው? ልብሷን እየለበሰች ይህን የመሰሉ አደገኛ ሃሣቦች፣ በአሊስ አዕምሮ ውስጥ አለፉ። ይህ ሁሉ ግን በፍራንቾይዝ የማነሣሣት ተፅዕኖ የመጣባት ሃሣብ ነው ብሎ ማሰቡ ትክክል አይሆንም። ሁለቱ፣ በማድቤቱ መግቢያ በኩል ተሾልከው ከወጡና በመንገዱ ላይ ካለው ጭለማ ጋር የራሣቸውን ጥላ ካመሣሰሉ በኋላ፣ አሊስ የደስታ እንቅጥቃጤ ተሰማት። ይህ መንቀጥቀጥ የተፈጠረባት እያደረገችው ባለው ነገር ሃሣብ አልነበረም። ይልቁንም በጉዳዩ ላይ ያለው ጥልቁ የተግባር ዕውቀት፣ አሁን እያከናወነችው ያለው ተግባር፣ አደጋ፣ ምናልባትም የመስዋዕትነት መልክ ያለው አደጋ፣ ፍፁም እውነተኛ የሆነና በሥልጣኔ ቅንጣት ታህል ያልተሸፈነ፣ በአጭሩ፣ የርስዋ እውነተኛ ባህሪ የፈጠረባት ነው።



መገናኛውን እየጠበቀ፣ ጆን ባፕቲስት በትውስታ ወደ ኋላ ተመለሰ። ሁልጊዜም ቀላልና ብልጭ ብሎ የሚያልፍ የፍቅር ግንኙነቶች እንደነበሩት ትዝ አለው። ከነዚህ ውስጥ የመጀመሪያ ግንኙነቱ እንደሚታወቀው ሁልጊዜም የመጨረሻ ይሆናል። የውድድር ዓይነት ትርዕ ነበረው። የውድድሩ ተሣታፊዎች እያንዳንዳቸው ግልፅ የሆነ ለማሸነፍ ወይም ለመቋቋም ያለመፈለግ ቅዝቃዜ ይታይባቸው ነበር። በመሆኑም ጨዋታው የተቻለውን ያህል ለረዥም ጊዜ ከመደባበቅ ባለፈ እውነተኛው ሃሣብ ሣይገለጥበት ቀረ። ይህ ከሆነ በኋላ እያንዳንዱ በጥልቀት ያለውንና ሌላኛው ሰው ምን እንደሚሰማው ማወቅ ቻሉ። የማሸነፍ ወይም የመተው ጥያቄ አልነበረም። መደረግ የነበረበት በውስጣቸው ተፀንሶ የነበረውንና ለረዥም ጊዜ አውግዘውት የነበረውን ፍቅር፣ ለዓለም ግልፅ ማድረግ ነበር። መደረግ የነበረበት፣ቃላትና የሰውነት እንቅስቃሴዎች የሚያስተጋቡትን ፍቅር ፍንትው አድርገው በአየር ውስጥ በግልፅ ማሣየት ነበር። ይህን የማድረጉ ሃላፊነት ገልጃጃ እንዳደረገው ተሰማው።

ሰዓቱ በጭለማው ውስጥ ሁለት ጊዜ እንደደወለ፣ ሁለቱም ፍቅረኛሞች ወደመገናኛው አቀኑ። አሊስና ፍራንቾይዝ፣ ከመግቢያው በስተግራ በኩል ሲደርሱ፣ በአትክልት ስፍራው በስተጀርባ ተሸሽጉ የነበረው ጆን ባፕቲስት፣ ከውስጥ በኩል ብቅ አለ። ሁለቱም እንክት በሚልና ሊጠገን በማይችል ውድ ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ መስሎ ተሰማቸው። ይህ ደግሞ የተገነባውን ቃል ኪዳን በማመልከቱ አይደለም። ምክንያቱም፣ ቃልኪዳኑ ከረዥም ጊዜ በፊት የተፈፀመ ነው። ነገር ግን ዳግመኛ አይፈፀምም የሚል ስጋት ስላላቸው ነው። እያንዳንዳቸው በየበኩላቸው፣ ይህ ጊዜ በተቻለ መጠን ረዥም እንዲሆን ለማድረግ፣ ልክ ዳግመኛ ሊታዩት የማትችሉትን ሰው መልክ በህሊናችሁ ቀርፃችሁ ለማኖር እንደምትሞክሩ፣ እነርሱም በትዝታ ኅዳቸው ውስጥ መስርተው ሊያኖሩት ቁርጠኞች ነበሩ። በአጭሩ፣ ግንኙታቸውን በመጣደፍ ሊያሣጥሩት አልፈለጉም። ይሁን እንጂ አካላዊ ጥላዎቻቸው እርስ በእርስ መቀራረባቸውን ሲመለከቱ፣ ሁለቱም ብቻቸውን በነበሩበት ጊዜ ውሣኔአቸው ትታቸው ጠፋ። ተለያይተው የቆዩበት ጊዜ ረዥም ነበር። ጭለማውና ሰው በሌለበት ቦታ ያደረጉት ግንኙነት ጉጉታቸውን ጨመረው። ፍላጐት አጠጋጋቸው። ወዲያውኑ ተቃቀፉ። እርስ በርሣቸውም በመሣሣም ተሸፋፈኑ።

«ምን ያህል ደስ እንዳለኝ» አሉ፣ ተራ በተራ።

የያንዳንዳቸውን ክንፈሮች አጣጣመ። ትዕግስት በሌለው ሁኔታ፣ በርግጥ እንደኛው አብሮት መኖሩን ለማረጋገጥ በሰቀቀን ሥጋቸውን አካከ። በዚህም ደስታን ሸመቱበት።

ሁሉም ነገር ጠፍቶ፣ በፍቅር መድረክ ላይ ሁለቱ ብቻ ነበሩ። ስለዚህም ጥቂት ቃላት አስፈለጓቸው። መቀራረባቸው በራሱ በቂ ነበር። ነገር ግን በፍርግርጉ የብረት በር በኩል ጥበቃ ስታደርግላቸው የነበረችው ፍራንቾይዝ መጥታ፣ ብዙ ጊዜ እንደሌላቸው ነገረቻቸው። ንግግሩ፣ በመንገዳቸው ላይ ጥንቃቄ ስለሚያስፈልገው መሰናክልና ወደ እውኑ ዓለም መለሣቸው።

«አባቴን እንዴት ልታግባባው ትችላለህ?» አለች አሊስ፣ ቀጭኑን ጥላውን ብቻ የምታየውን ፍቅረኛዋን እየተመለከተች «ደግሞና ደጋግሞ እንደሚድረኝ ነው የሚያወራው»

«ለጊዜው ምንም አንነግራቸውም። እርሣቸውም፣ አንዳችም ነገር እንዲጠረጥሩ አናደርግም። ከዚህ በኋላ ግን መተያየታችን ይቀጥላል። አንቺን በክንዶቼ ውስጥ ካልያዝኩሽ በስተቀር መኖር አልችልም። ይኸው አሁን በመጨረሻ ላይ አብረን ሆነናል። እኔ እቅዴን ወደ ተግባር እስክለውጥ ድረስ አንድም ሰው እንዳያውቅ ይሁን። ሆኖም ግን አስቀድሞ ወደ ቬርሣይለስ እሄዳለሁ»

«ምን?» አለች አሊስ፣ በፍርሃት ወደርሱ ሹጉጥ በማለት። «እዚህ የደረስከው እኮ በብዙ ውጣ ውረድ ነው። ይህ እያለ አሁንም ለመሄድ ትፈልጋለህ?»

«ረጋ ብለሽ ብታስቢው፣ ያለው ብቸኛ መፍትሔ ይኸው እንደሆነ ታያለሽ። ንጉሱ፣ ኤምባሲ ይፈልጋሉ። ታዲያ፣ እኔ አንድ አመጣሁላቸው። የምፈልገውን ውለታ ሊከፍሉኝ የሚችሉት እርሣቸው ብቻ ናቸው። ስመለስ ክብር ያለው ሰው ሆኜ እመለሣለሁ። ያን ጊዜ አባትሽ የሚከለክሉኝ ነገር አይኖራቸውም»

የምታፈቅረው ሰው የሚነግራትን ማንኛንም ነገር ለመቀበል፣ አሊስ ዝግጁ ነበረች። ነገር ግን እቅዱ እንደገና እንዲለያዩ የሚያደርጋቸው ስለሆነ አልተደሰተችበትም። በሌላ በኩል ግን ይህ እቅድ የተሻለው ዘዴ እንደሆነና እርስዋም ጃን ባፕቲስትን፣ በርስዋ አቅምና ችሎታ ሥር ባለ ነገር ሁሉ እንደምትረዳው ማለች።

«ልትረጂኝ የምትችይው አንዱ መንገድ እኔን አለመርሣትሽ ነው።»



በኩርፊያ ቁጣ፣ ተቃውሞዋን ስትሰነዝር፣ በረዥም መሣም ታፈነ።

በመጨረሻም ፍራንቾይዝ ተመልሣ በመምጣት፣ የዕለቱ ተረኛ ተዘዋዋሪ ዘበኞች የሚመጡበት ሰዓት ስለሆነ እንዲላቀቁ ለመነቻቸው። ተላቀቁና መልሰው በፈጣን እርምጃ ለአንድ ጊዜ ተቃቀፉ። በመጨረሻም ሁለቱም በሞቃቱ ምሽት በተለያየ አቅጣጫ ተጓዙ። ከበላያቸው፣ የዘንባባ ዛፎች በነፋሱ እየተወዛወዙ ይንሳጠጣሉ።

መራድ፣ በጆን ባፕቲስት ላይ ሙሉ እምነት አለው። ንጉሡ ራሣቸው፣ ለዚህ እንግዳ፣ የተለየ ፍቅር አሣይተውት አልነበረም? በዚህ ምክንያት፣ ሐኪሙ የሚጠይቀውን ማንኛውንም ነገር ለመፈፀም ፈቃደኛ ሆነ። ይህን ሁሉ እንዲህ ቀላል ያደረገው ሌሎች የፈረንሣውያን ማህበረሰብ ነዋሪዎች ሊማርኩት ስላልቻሉ ነው። እነዚህ ሲበዛ ሃብታምና ሲበዛ ፍልቅልቅ የሆኑ ነጋዴዎች፣ አሌፖ ውስጥ የነበረውን የጥንቱን ጌታውን አስታወሱት። ያ የጥንት ጌታው፣ ሁልጊዜም በመልካም ቃላት እየሸረደደ በከፍተኛ ግብዝነት የሚሠራ ነው። ብዙ ጊዜ በጥንቃቄ የተሠራውን ምግብ በቀጣሪው ሰው ፊት ላይ ለመወርወር ይቃጣም እንደነበር አስታወሰ። አሁን ቢሆን ሊያደርገው ይችላል። በተቀባይ ጫፍ ያሉት ምንም ካላደረጉት ሲበዛ መጥፎ ነው።

«ምን ማለትህ ነው፣ የሹመት ደብዳቤዬን ስትል?» አለው መራድ በኩራት፣ ሙሴ ማቹ ስለደብዳቤው ሊጠይቀው በመጣ ጊዜ። «ማን የሆንኩ ነው የመሰለህ? እኔ እኮ የንጉሡ መልዕክተኛ ነኝ። የነገስታት ንጉስ፣ ከዚህ የበለጠ ምን አለ?»

እንደሕፃን ልጅ የፋፉትን እጆቹን፣ በነሃስ ቀለበት የተጌጠውን ትንሽ ጣቱን ተመለከተና ቀጠለ።

«ግርማዊነታቸው በጥብቅ ያሣሰቡኝ፣ ደብዳቤአቸውን ለማንም ሰው ሳይሆን፣ ለፈረንሣይ ንጉሥ በእጃቸው እንድሰጣቸው ነው። ደብዳቤዎቹን ለመስጠት ወደ ቬርሣይለስ መሄድ ይኖርብኛል።»

ሙሴ ማቼ ሙጭጭ አለ። አርመናዊውም ከአቋሙ ፍንክች አልል አለ። በመጨረሻም ግን ፈረንሣዊውን አዋርዶ አባረረው። ፀሐፊው፣ ወደ ቆንስላው በፍርሃት ተሞልቶ ተመለሰና የነበረውን ውይይት በቅሬታ አንላለፅ ለሙሴ ዴ ማይሌ ተረከለት።

«እህ! እንዲህ ነው እንዴ!» አለ ዲፕሎማቱ።

«ደብዳቤውን ማሣየት አይፈልግም! ግን ምን የይለፍ ይሏል። መሬት ላይ ተቀምጦ መላውን ማህበረሰብ እንዲበድብ እንፈቅዳለን? ነገር ግን እጅግ ቢያንስ በሕጉ መሠረት ራሱን ማሣወቅ ይገባዋል።»

«ምናልባትም ለርስዎ . . . » ሲል ሙሴ ማቼ ሃሳብ ሰነዘረ

ቆንሲሉ ባለበት ረጋና፣ ምስኪን ፀሐፊውን ጥላቻ በተሞላው እይታ አተኮረበት

«እኔ የፈረንሣይን ንጉሥ የምወክል፣ የሹመት ደብዳቤውን የማያሣየውን ሰው ማነጋገር እንደምችል መገመትህ የሚያጠራጥር አይደለም»

«አይደለም፣ በእውነት» አለ ሙሴ ማቼ በመስማመጥ

«መልካም። ሊያግባባው የሚችል ሌላ መልዕክተኛ እንልክበታለን»

«ወደዚያ ተመልሶ ለመሄድ አንድም ነጋዴ ፈቃደኛ አይሆንም»

«እንግዲያው ራስህ ትሄዳለህ።» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ «እናም የሹመት ደብዳቤውን ከነገ በፊት ባያቀርብ ከማህበረሰቡ ሰፈር እንደሚባረር ትነግረዋለህ። ከዚያም በአርጌው ካይሮ ሠፈሮች ውስጥ የሚስማማውን መስፈሪያ ሊፈልግ ይችላል»

ማቼ፣ መልዕክቱን ለማድረስ ሄዶ፣ ጆሮ ግንዱ ላይ አምባረቀበት። ሙራድ፣ የብልግናውን ደረጃ ከፍ በማድረግ ዘይት የጠገበውን የባቅላቫ ቁራጭ አስቀድሞ ትንሽ ከገመጠ በኋላ፣ ማቼ ጭንቅላት ላይ ወረወረ።

«ይህ አነስተኛ ቀልድ እዚህ ላይ ያከትማል» አለ ሙሴ ዴ ማይሌ፣ በርጋታና በቆራጥነት። «የዚህን የደብዳቤ ሥረ መሠረት እንዴት ማግኘት እንደምችል አውቃለሁ። እናም አመነኝ፣ አንድም ደብዳቤ አለመያዙ ከተረጋገጠ ይህን ሽካራ ፀባዩን እንደያዘ፣ እርሱን፣ ከብቶቹን፣ ባሮቹንና ቁርጥራጭ ጨርቆቹን መንገድ ላይ ለመወርወር ጥሩ ምክንያት ይኖረኛል።»

ይህን ከተናገረ በኋላ፣ ቆንሲሉ፣ ጋሪው እንዲዘጋጅለትና፣ ፓሻው ዘንድ፣ ሊቀር የማይችል ጉብኝት እንደሚኖረው አስቀድሞ እንዲያሣውቁለት ተናገረ።

ከስብሰባው ሲመለስ ስለራሱ በጣም ተደስቶ ስለነበረ፣ ያን ሌሊት በጥሩ ሁኔታ ተኝቶ አደረ። በማግስቱ ወደ ቢሮው ሲገባ ግን አባ ፕላንቴይን መምጣታቸው ተገለፀለት።

ጀስዊቱ፣ ካይሮ የደረሱት፣ አባ ብሬቬደንት ወደ ኢትዮጵያ ከሄዱ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነበር። አባ ጋበሪን የአልጋ ቁራኛ ያደረጋቸው ሕመም፣ እኒህን አዲስ መጪ ካህን በይፋ እንዲታዩ አደረጋቸው። በጥቂት ሣምንታት ውስጥም አባ ፕላንቴይን በዚህ ጣቢያ ላለው የምስራቅ ሜዲቴራኒያን ሕጋዊ ተወካይ ሆኑ።

ዕድሜአቸው አርባ ዓመት ያህል ይሆናል። ሰውነታቸው በሚገባ የተገነባ ነው። ይህ ደግሞ፣ እንደእውነቱ ከሆነ ቤተሰባቸው በቀንድ ከብቶች ኢንዱስትሪ ፈረንሣይ ውስጥ፣ በቻሮሌ አካባቢ ለዘመናት መስራቱ ነው። ረዣዥም አለንጋ የመሰሉ ጣቶች ሲኖሯቸው፣ ቀስ እያሉ እጃቸውን ይጨብጧቸዋል፤ ይዘረጓቸዋል። እጆቻቸውን በፍቅር ሲመለከቷቸው፣ የቀንድ ከብቶች እረኛነት መሠረት እንዳላቸው ብቻ የሚያጋልጡባቸው አይደሉም። ጭንቅላታቸው፣ ክብ አለት ከመሰለው ከትልቁ ግራጫ የራስ ቅላቸው በታች፣ ጠፍጣፋ ሆኖ በአይኖቻቸው ላይ ወደፊት አብጦ የወጣ ነው። ግንባራቸው ትልቅ ነው። ቀደም ባለው ጊዜ ይህ የብልህነት መለያ የነበረ ቢሆንም፣ አሁን ግን ልክ ክብደቱ በመላው ፊታቸውና መላ አካላቸው ላይ ቁልቁል የተጫነው ይመስል፣ አንዳች የዘገምተኛነት ስሜት ሰጥቶታል። የተፈጥሮ ቅርፃቸውን ብቻ ብንወስደው፣ በቀላሉ ድንጋይ ጠራቢ ወይም ሙዚቀኛ ሊሆኑ ይችሉ ነበር። ለመማር ጥሩ ጭንቅላት ቢኖራቸውም፣ አሁንም በመማር ላይ ያሉ ግን ምንም ልምድ የሌላቸው ናቸው። ካይሮ ከደረሱበት ጊዜ ጀምሮ፣ ለቆንሲሉ ብዙ ወዳጃዊ ጥርጣሬአቸውንና በሴራ ተግባር ለመሰማራት ማቀዳቸውን ነግረውታል። በመጀመሪያ ላይ፣ ቄሱ ቀላልና ፊት ለፊት ናቸው ሲል፣ ሙሴ ዴ ማይሌ አሰበ። ውሎ አድሮ፣ የአታላይነት ባህሪይ ሲያይባቸው ስህተቱን ተገነዘበ። ከዚያ ወዲህ፣ ለጀስዊቱ የአታላይነት ባህርይ ዕድል ነፈገው።

«እርስዎን ማየት ደስታ ነው አባቴ!» አሉ ቆንሲሉ፣ ጥቁር ካባ የለበሱት ሰው በቤቱ በር ደርሰው ሲያያቸው። ይህ ሁሉ ሲሆን፣ ዲፕሎማቱ፣ አንድ ሰው መርዘኛ እንስሳን በትንሽ የጭራሮ ጫፍ ለማንሣት ሲል የሚያደርገውን ጥንቃቄ ያህል ራሱን ጠንቀቅ አድርጐ ነበር።

አባ ፕላንቴን፣ ቢያንስ ለማገልገል ፈቃደኛ አልነበሩም። አጭበርባሪነታቸው በማስመሰል በጀግንነት የተሸፋፈነ ነበር። ሰላምታቸውን ጮክ በማለት «ክቡርነትዎ!» በማለት ትዕዛዝ ለመቀበል እንደተዘጋጀ ሰው በተጠንቀቅ ቆሙ።

«ማስታወሻዎን ተቀብያለሁ፣ ክቡር ሆይ አመሰግንዎታለሁ። እጅግ ድንቅ ዜና ነው። ምስኪኑ አባ ዱ ብሬቬደንት ጉዞውን በሕይወት አለማጠናቀቃቸውን ከሣምንት በፊት አውቀን ነበር። ከዚህ መጥፎ እድል በስተቀር ሁሉም መልካም ነበር። አምባሣደራችንም መጥቷል» አሉ ጀስዊቱ

ወደ አቢሲኒያ ተልኮ የነበረው የመልዕክተኞች ጓድ መመለሱን፣ ቆንሲሉ፣ ለእየሱስ ማህበረሰብ[6] ተወካዮች አስታውቋቸው ነበር። ወደ ኋላ መለስ ብለው ሲያዩት፣ ይህ ከርህራሄ የመነጨ ሊመስል ቢችልም፣ ቅፍለቱን ለመቀበል ከተንቀሣቀሰው ጓድ ጋር እንዲቀላቀሉ ካህኑን አልጋበዛቸውም።

«እንደሚመስለኝ» አሉ ቄሱ። «እርስዎ ያረጋግጡልኛል እንጂ፣ የተመለሱት ከሦስት አቢሲኒያውያን ተወላጆች ጋር ነው»

«እኔም እንደዚያ ነው የሰማሁት»

«እርስዎም አላየኋቸውም ነው የሚሉኝ?»

«በጨረፍታ ብቻ ነው»

የሹመት ደብዳቤውን ጉዳይ በማንሣት ከነሀ ችግር ፈጣሪ ጋር ለመወያየት፣ ሙሲ ዱ ማይሌ ፍላጐት አልነበረውም።

«ገና መድረሣቸው መሆኑንማ አይዘንጉ እንጂ» አሳቸው ሙሴ ዱ ማይሌ በየዋህነት



ጥቁር የለበሱት ሰው፣ የተሸከሙት ክብደት፣ አካላዊ እንቅስቃሴአቸውን ያሰቃየው መሆኑን በሚመሰክር መልኩ ጭንቅላታቸውን ደጋግመው አነቃነቁ።

«ስምሥራቅ ተማሪዎች በተያዙ መቀመጫዎች ላይ ሦስት አቢሲኒያውያን በታላቁ የሉዊስ ትምህርት ቤት ሊገቡ ነው።» አሉ ጀስዊቱ አይኖቻቸውን እያቁለጨለጩ። «ይህ ደግሞ ታላቅ ዱላ ይሆንብናል። ክቡር ሆይ! ለመሆኑ እርስዎ ይህ እንደሚሆን አውቀው ነበር» ሲሉ ቄሱ ወደፊት ዘንበል ብለው ንግራራቸውን ቀጠሉ። «ማለቴ በቅርቡ በኢትዮጵያና በሲናር ንጉስ መካከል በተደረገው ጦርነት ላይ፣ ካፑቺኖች ሰባቱን እንደያዟቸው ያውቁ ነበር? እስቲ ያስቡ። እነዚህ ሰዎች በቀጥታ ወደ ሮም ሊያመሩ ነው . . . »

ወደ ቆንሲሉ ይበልጥ ጐንበስ ብለውና ድምፃቸውንም በጣም ዝቅ አድርገው

« . . . ለዚያውም ቱርኮች እንዲሣፈሩ የሚፈቅዱላቸው ከሆነ።»

እነዚህን ቃላት በፈገግታ አጅበው የተናገሩት ቄስ፣ በሁኔታዎች ሂደት ውስጥ ጣልቃ ለመግባት ማሰባቸው አያጠራጥርም

«እኛም ተመሣሣዩ ችግር ይኖርብናል።» ሲል ቆንሲሉ ጀመረ። ወዲያውኑ ግን ተፀፅቶ «በተለይ ከአገራቸው ወጥተው ወደኛ ዘንድ የመጡትን አቢሲኒያውያን በመላካችን ችግር ይኖርብናል»

«እ! ክቡር ሆይ» አሉ ጀስዊቱ፣ ራሣቸውን በግርማ ሞገስ ቀና እያደረጉ። «የፈረንሣይ ንጉሥ የሚሹት ጉዳይ፣ እዚህም ቢሆን ክብደቱ ተመሣሣይ ነው። ቱርኮች እኛ የምንላቸውን እንደሚሰሙን አምናለሁ። በርግጥ ፋታ ሳልሰጥዎና ተራ ሳልጠብቅ እያወራሁ ነው። እርስዎ ዲፕሎማት ስለሆኑ እነዚህን ጉዳዮች ከኔ በተሻለ ያውቋቸዋል።»

ሙሴ ዱ ማይሌ ፣እንደ እሮጊት ልብስ አጣቢ፣ እንዳች የጥላቻ መግለጫቸውን ፍንጭ የሰጡትን እኒህን እንደ አለት የጠነከሩ የሚመስሉ ሰው ሽፍጥ አደነቀ።

«አባ፣ እርስዎ እንደገለፁት የዲፕሎማቲክ ሥራዎች በጣም ውስብስብ ናቸው። እንደመጣልኝ ልናገረውና የዲፕሎማቲክ ሥራዎች ምናልባትም እርስዎ ከሚገምቱትም በላይ ነው። ዋናው ሃላፊነትም፣ ሁሉም ነገር ተራ በሆነና በተለመደው መልክ መከናወን የሚገባው

መሆኑ ነው። እርስዎ የክርስትናን እምነት እያገለገሉ ነዎት። እንቅስቃሴ በማደንዘዣ ስለመተላለፉና የመንፈስ ቅዱስ ብርሃን በሰው ልጅ ነፍስ ላይ ስለመውረዱ ልምድ አለዎት። እኛ ደግሞ በሌላው ወገን የምንሠራው በዚህ ዓለም ገፅ ላይ ነው። ፖለቲካ የሚከናወነው በሰዎች እንቅስቃሴ ላይ ነው። ለዚህም መጣደፍ የለበትም»

የዚህን አነስተኛ ንግግር ምንነት ጀስዊቱ በጭራሽ አልተረዱም። ከአመታት በፊት፣ አባታቸው አታላይ ነው ብለው የሚያስቡትን አንድ ውብና የደለበ እንስሳ እንደሚመለከቱት አይነት፣ ቁሱም ቆንሲሉን በጥልቀት በተሸበሸቡት አይኖቻቸው ቂጥ ተመለከቱት። ቆንሲሉ፣ አንዳች ከፍተኛ ጉዳይ እየደበቃቸው እንደሆነ አምነዋል። ጭውውቱ ለተጨማሪ አስር ደቂቃዎች ቢቀጥልም ቁሱ ምንም ያወቁት ነገር አልነበራቸውም።

ጀስዊቱ ወጥተው በመሄድ በመንገዱ ላይ እያመነቱ ሲጓዙ ቆይተው፣ ወደ ፖንሴ ቤት አቀኑ። እንደደረሱ በሩን ቢያንኳኩም ጆን ባፕቲስት በቤቱ ውስጥ አልነበረም። ከዚያ በኋላ ወደ ቬኒስያዊው ቤት ሄዱ። ከአትክልቱ መግቢያ በር ላይ ዝርግት ብሎ የነበረው አንድ ሽማግሌ ቱርካዊ፣ የተከበሩት የኢትየጵያ አምባሣደር ማንንም እንደማይቀበሉ ለአባ ፕላንቴይን ነገሩቸው።

ጀስዊቱ፣ ግራ ተጋብተው ወደ ቤታቸው ሄዱ።

ሜትር ዠረሚ፣ ጥንቃቄ በተሞላው ሁኔታ በቆንስላው ግቢ በምሽት፣ በየጭለማው ጥላ ውስጥ እያደባ ወደ ማህበረሰቡ ሰፈር ተመለሰ። እቤት ሲደርስም፣ ከፖንሴ ጋር ለመጨረሻ ገዜ የተያዩት ከሁለት ወራት በፊት እንደነበረ ሁሉ ፖንሴ እርሱን በማየቱ ሲደሰት አገኘው።

ባለፈው ቀን የነበረውን ሁኔታ ጆን ባፕትስት ነግሮት ካበቃ በኋላ፣ ፕሮቴስታንቱ በመቀጠል፣ «መቼም እዚህ ስትደርስ የጀግና አቀባበል እንዳደረጉልህ፣ አንተም ጀብዱህን በአድናቆት ለሚያወሩ ወይዛዝርት ስትናገር እንደቆየህ እገምታለሁ።» አለው



«ይህ የሚያመለክተው የማህበረሰቡን ሠፈር ምን ያህል እንደምታውቀው ነው። ፈሪዎች ስለሆኑ እርስ በርሣቸው ይሰላለላሉ። እኔ እንደሆንኩ በየሄድኩበት ቦታ እንኳን ደህና መጣህ አልባልም። ሊያዩኝ የሚፈልጉኝ ሰዎች ደግሞ እኔ ልርቃቸው የምፈልጋቸው፣ ለምሳሌ ዛሬ ከሰዓት በኋላ እንደመጡት ጀስዊት ያሉ ሊያነጋግሩኝ እንደሚፈልጉኝና ጉረቤቱ ሁሉ ይህን እንዲያውቅላቸው የሚሹ ናቸው። ጉዞው ገና አለመገባደዱን አመነኝ። ባለፉት ሁለት ቀኖች ምድረበዳውን ስናቋርጥ ከነበርኩበት ሁኔታ ይልቅ ብቸኝነት ተሰምቶኛል።

«ሙራድስ?»

«በርግጥ እርሱን አገኘዋለሁ። የመሣፍንት መኖሪያ ቢሰጡትም፣ ቆንሲሉ እስካሁን ሊያገኘው አልተስማማም። ቆንሲሉ የሹመት ደብዳቤውን ሊያደብት ይፈልጋል። እኔ ደግሞ፣ ሙራድ ደብዳቤውን እንዳይሰጠው ቃል አስገብቼዋለሁ። እንዲያውም፣ ተልዕኮው እስከ ቬርሣይለስ እንደሚቀጥል ከመግለፅ ሌላ ትንፍሽ አላለም።»

«እና ፍቅረኛህስ?»

«ዳግመኛ መቼ እንደማያት አላውቅም። ትናንት ምሽት ላይ . . . ለመሆኑ ምግብ ቀምሰሃል?»

«እስካሁን ገና ነኝ»

«እንግዲያውስ ከሃሰን መስጊድ ባሻገር ወዳለው፣ ወደ ዩሱፍ ቤት እንሂድ። እዚያ በሰላም መጫወት እንችላለን»

ሁለቱም ደስ ብሏቸው ወደ አሮጌው ካይሮ ተያይዘው በእግራቸው ተጓዙ።

ፖንሴና ሽሪኩ እኩለ ለሊት ላይ ወደ ቤት ተመለሱ። ልክ በራቸው ሲደርሱ ከጨለማው ውስጥ አንድ ጥላ ወደነርሱ ዘልሎ ወጣ። ሜትር ዠረሚ ጐራዴውን መዘዘ።

«ይትርታ!» አለ፣ ጥላው። «እኔ ነኝ»

«ሙራድ! በዚህ ውድቀት ሌሊት እዚህ ምን ታደርጋለህ?»

ወደ ቤቱ ውስጥ ገፍተው አስገቡት። ፖንሴ ጧፍ አበራ። አርመናዊው በላብ ተዘፍቆ ቁና ቁና ይተነፍሣል።

«ተኝቼ እያለሁ ከጥቂት ጊዜ በፊት አንድ ሃያ የሚሆኑ ሰዎች ገቡ» አለ ሙራድ እያለከለከ

«ሃያ ሰዎች? እነማን ናቸው? ወታደሮች ናቸው ወይንስ ነጋዴዎች?»

«ወታደሮች ናቸው። ቱርኮች ናቸው። ሙሉ በሙሉ ያበዱ ሰዎች ነበሩ። ዘልለው ያዙኝና ትልቅ ጉራዴአቸውን መዝዘው አንገቴ ስር በመወደር እንድማረክላቸው አፈጠጡብኝ፣ እዩት»

አገጮ ስር የተንጠለጠለውን ወፍራም ቆዳውን አሣያቸው።

«እና ከዚያስ?»

«ከዚያማ ሁሉንም ነገር ፈተሹ፣ ሁለንም ነገር እየገለባበጡ አመሰቃቀሉ፣ ሁሉንም ነገር ከፋፈቱ። ቤቱን በሙሉ፣ የላዩን ወደታች የታቹን ወደ ላይ ካደረጉት በኋላ፣ ነገ ጧት ፓሻው ዘንድ እንደምቀርብ ብቻ ነገሩኝ።

«ምንድን ነበር የፈለጉት?» ሲል ፖንሴ ጠየቀ

«ምንስ ወሰዱ?» ሲል ሜትር ዠረሚ አከለ

«ምንም»

«እንዴት፣ ምንም?»

«ምንም፣ ወርቅ አልወሰዱም፣ ገፀ በረከቶችን አልወሰዱም፣ ልብሶችንም አልወሰዱም»

«ምንም ነገር አልወሰዱም?»

«የንጉሡን ደብዳቤ ብቻ» አለ ሙራድ አይኖቹን ሰብሮ



# 6

ፖንሴ ባልነበረባቸው ረዥም ጊዜያት ውስጥ ታማኝ ታካሚው የነበረው የካይሮ ፓሻ ሁሳይኒ፣ ከፈረስ ላይ ክፉኛ ወድቆ እግሩን ተሰብሮ ነበር። የሕክምናው ዕውቀትና ችሎታ የሌላቸው አታላዮች እንዲያክሙት ይጠሩሱ። እነዚህ አጭበርባሪዎች በሕክምናቸው የፓሻውን የእግር ቆዳ በመጥፎ ሁኔታ በማሸት ስብራቱን በድጋሚ ያናጉታል። የሕዝብ አመፅም ይሁን፣ ወይም መርዝም ይሁን፣ ወይም ደግሞ ብልግና የተሞላበት ህክምናም ይሁን፣ ያከናወኑት ጉዳይ ብቻ በአንድ የወሰን ምልክት ድንጋይ ማደናቀፍ ላይ ተሳብቦ ቀረ። ሁሳይን ክፉኛ ተሰቃይቶ ሞተ።

ሁሳይኒን እንዲተካው በከፍተኛው ባለሥልጣን ተሹሞ የተላከው ሰው ደግሞ፣ ፍፁም የተለየ ነበር። ስሙ መሃመት ቤይ፣ ሲሰኝ፣ ፍፁም ጦረኛ ነበር። በሃንጋሪ ውስጥ የቱርክ ወራሪ ሃይል ፊታውራሪ በመሆን ሲያገለግል፣ ለክርስትና ፍፁም ጥላቻ ያለው ሆኖ ተገንጥሎ ወጣ። ይሁን እንጂ፣ ይህ ሰው፣ አንዱን ሕዝብ ከሌላው መለየት ስለሚችል ፈረንሣውያንን በሚገባ ለይቶ ያውቃቸዋል። እንዲህ ያለውን አስቸጋሪ ሥራ የሚያከናውኑት ጥቂት ቱርካውያን ናቸው። ከፈረንሣውያን ጋር በቀጥታ አልተዋጋም። ይሁን እንጂ፣ ፈረንሣውያኑ በሃፕስበርጎች ላይ ከከፍተኛው ባለሥልጣን ጋር ብዙ ልዩ ልዩ ምስጢራዊ ንብረቶችንና ስምምነቶችን ማድረጋቸውን ያውቃል። ዕድሜ እያሸነፈው ሲመጣ፣ መሃመት ቤይ፣ በኢማሞችና በሙፍቲዎች እጅ ወደቀ። እነዚህ ቅዱሣን ሰዎች በጥበብና በዘዴ፣ ራሣቸውን የፓሻው መንፈሳዊ መሪዎች አደረጉ። ይህም፣ ይህ ጠንቃቃ፣ ነገር ግን ማይም የሆነ ሰው ከቀደሙት መሪዎች ይልቅ በእስልምና ጠላቶች ላይ ያለው መረጋጋት ቀዝቀዝ ያለ መሆኑን ተስፋ በማድረጋቸው ነው።

ሙራድ፣ ከፓሻው ፊት ተከስሶ በቀረበ ጊዜ፣ መሃመት ቤይ በመጀመሪያ የብስጭት ቁጣውን ለቀቀው። አርመናዊው የሚቀርብለትን ቃለመጠይቅ በማሰብ በጣም ከመፍራቱ የተነሣ፣ እስከ ከተማው ጠባቂ ድረስ ራሱን አረጋግቶ በበቅሎው ላይ ሆኖ ደረሰ። እንደ እድል ሆኖ የከተማውን የጥበቃ በር በበቅሎ ላይ ሆኖ የመግባት መብት በአገሮችና ቁስጥንጢንያ በሚገኘው ከፍተኛው ባለሥልጣን መካከል በተደረሰ ስምምነት መሠረት ለክርስቲያን

አምባሣደሮች የተወሰነ ነበር። ጠባቂዎቹ፣ ሙራድን በሚዘገንን ሁኔታ ከበቅሎው ላይ እንዲወርድ አድርገው በፓሻው ፊት ጉተቱት።

«ለመሆኑ ማን የሆንክ ይመስልሃል?» ሲል ወርቅማ ጥብጣብ የሚከበበውን የራስ ጥምጣሙን አጥልቆ፣ የቱርኮችን ቀይ ዩኒፎርም ለብሶ፣ በእብሪት ተወጥሮ የቆመው መሃመት ቤይ ጠየቀ። «ሆኖም ግን አስቀድመህ ዝቅ ብለህ ስገድ! ሡልጣኑን ሳለማክበር ሃሣቡ አለህ?»

«እኔ . . . እኔማ አከብራቸዋለሁም። የሚገባቸውንም ክብር አቀርባለሁ» አለ ሙራድ ተንበርክኮና የድንጋይ ንጣፍ ወለል ላይ አፍንጫው ተጣብቆ እየተንቀጠቀጠ።

«ከዚህም በላይ» አለ መሃመት ቤይ፣ ከፊቱ ሰግዶ ባለው ሰው ዙሪያ እየተራመደ፣ «አንተ ቱርካዊ አይደለህም።የአክብሮት ነገር በጣም ከማጣትህ በስተቀር ቋንቋችንን ትናገራለህ፣ ባህላችንንም ትጋራለህ። መቼም ሃይማኖትህን የካድክ አትሆንም፣ ከደህ ይሆን?»

«በጭራሽ፣ በጭራሽ፣» አለ፣ አሁን ድረስ አፍንጫው መሬት ላይ ተጣብቆ ያለው ሙራድ። ቆሞ ቢሆን ኖሮ የክህደት እርምጃ ለመፈፀም ቃጥቶ የነበረው ሙራድ እውነቱን እየተናገረ። «እኔ አርመናዊ ነኝ። ሃይማኖቴም ከአባቴና ከታላቁ ሰው፣ ከቱርካዊው ሱልጣን በርህራሄና ጥበብ ከተሞላው የወረስኩት ሲሆን ሃይማኖቴን ጠብቄ እንድቆይ ያደርገኛል»

« እኛ የፈረንሣይ ውሾችን ስንዋጋ፣ እናንተ ከጀርባ ሆናችሁ ስትወጉን ሱልጣኑ፣ ለክርስቲያኖች እጅግ ታላቅ ርህራሄ ያሣያችኋል። መቼም የዚህች ዓለም ጉዳይ እንዲህ አይደል? . . . »

ተነስ! እስቲ ይህን ከሃዲውን ፊትህን አሣየኝ»

ሙራድ ቀና ቢልም፣ በእንብርክኩ ላይ ቆየ። ወፍራሙ ፊቱ፣ ለረዥም ሰዓታት ተዘቅዝቆ በመቆየቱ ቀልቶና አብጦ ይታያል። ፓሻው አንዱን ጠባቂውን ሲጠቅሰው፣ የብር ትሪውን ይዞለት ቀረበ። ከዚያም ላይ ፓሻው የንጉሡን ደብዳቤ አነሣ።

«የነብዩን ትዕዛዞች ሣትቀበል፣ በመሬታቸው ላይ መኖርህ ብቻ ሣይሆን፣ እኔ እስከሚታየኝ ድረስ አንተ እስልምናን በፅናት ከሚከላከሉና እንዲያውም ከሚወጉት ጋር የተባበርክ ነህ»



ሙራድ አቅሉ ከተመለሰለትና ከተበረታታ በኋላ፣ ወኔውን ሞልቶ ምን ማለት እንደሚገባው ፖንሴ የመከረውን ለማስታወስ ሞከረ።

«ክቡር ሆይ፣ እኔ ነጋዴ ነኝ» ሲል በደካማ ድምፅ አሳዘነ። «መኖሪያዬን የማገኘው የምችለውን ሁሉ አድርጌ ነው። ወደቀይ ባህር የወሰደኝ ዕድል ፈንታ ነው። ለአጭር ጊዜ ያህል ለምፅዋው ናኢብ አገልግዬ ነበር። እርሣቸው ጥሩ ሙስሊም ናቸው። አንድም ጊዜ በኔ ላይ ቅሬታ አልነበራቸውም። ይህን ሊጠይቋቸው ይችላሉ። ከዕለታት አንድ ቀን ለኢትዮጵያውያን ንጉስ የማደርሰው መልዕክት ሰጡኝ»

«ለዚያ ቀበሮ ደብዳቤ የሚልክለት ለምንድን ነው?»

«ክቡር ሆይ፣ በቀድሞው ጊዜ አቢሲኒያውያን ውሃውንና እህሉን ሁሉ አቋርጠውባቸው ነበር። ናኢቡ፣ መሬታቸው ከርሣቸው በላይ በተራራው ላይ ከሚገኙት ከጐረቤታቸው ጋር ከመስማማት በስተቀር ሌላ ዕድል አልነበራቸውም።»

መሃመት ቤይ፣ የሙራድ ንግግር አእምሮውን ዘልቆ የገባው መሆኑን በሚያመላክት ሁኔታ አይኖቹን በትንሹ አንሸዋረራቸው። ከጠጣሩ ጭንቅላቱ ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ምናልባትም እርሱን በሚመለከት ከሆነ፣ ከስንት አንድ ጊዜ ቢባል የተሻለ ይሆናል፣ እውነታ አብረቅርቆ፣ ሃሣብ የሚባለውን የሚያበሳጭ ነገር ሰርስሮ ይገባዋል።

«እንዲህ ከሆነ ንጉሡ በርግጥ ውሃ ወደ አገራችን እንዳይፈስ መከልከል ይችላል ብለህ ታስባለህ? ይህ ከሆነ ደግሞ ይህን ያህል ከልቡ የሚጠላን ከሆነ ለምን እስከዛሬ አላደረገውም ነበር?»

«ይህንን በባህረ ገብ ምፅዋ ላይ ፈፅሟል። ሳሳነሰ ጊዜ ምፅዋን ሁሉንም ነገር ነፍገዋት ነበር»

«ይሁንና እኛን በተመለከተ፣ እዚህ ግብፅ ውስጥ በአባይ ወንዝ ላይ ሕይወታችን የተመሠረተውን?»

«ክቡር ሆይ፣ እኔ ከማውቀው ከሁሉም በበለጠ፣ ንጉሡ አንድም የመከልከያ ዘዴው የላቸውም ወይም ለሙስሊሞች የሕይወታቸው መሠረት የሆነውን ውሃ የመንፈግ ምክንያት

የላቸውም፡፡ ነገር ግን ሊታሰብ የሚገባው ንጉሡ የአባይን የላይኛውን ፍሰት፣ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ የሚፈስሰውን እንዘልና ወደ ምስራቅ አቅጣጫ ቢለውጡት፣ የግብፅን ፍፁም መውደም ብቻ የሚያመለክት ሣይሆን፣ ነገር ግን. . . »

«ነገር ግን ምን?»

« . . . ነገር ግን በተመሣሣይ መልኩ እንደርስዎ ሙስሊም ስሆኑት ለሶማሊያውያን ብልፅግናን ያስገኙላቸዋል»

ፓሻው እነዚህን ቃላት መዘገባቸው፡፡ ቃላቱ በአዕምሮው ጥልቅ ጭለማ ጓዳ ውስጥ ተጉዘው፣ በመጨረሻ ላይ እርሱ ራሱን በሣቅ አፈነዱት፡፡ ሣቁ ደግሞ፣ በታላቁ አዳራሽ ዙሪያ በጥበቃ ላይ ባሉ ዘበኞች ተቀባይነት በቀላሉ የገደል ማሚቶ ፈጠረ፡፡

«እግዚአብሔር ወደ ምድር የሚልከው ውሃ» አለ ፓሻው «አስቀድሞ በርሱ ለሚያምኑትና የርሱንም ኸብይ ለሚከተሉት የታደላቸው ነው፡፡ ጌታህ፣ ዝናቡ በመጀመሪያ ከርሱ ጠቃሚነት በሌላቸው ተራሮቹ ላይ በመዝነቡ፣ ሃይል ያለው መስሎት ካሰበ ተሳስቷል፡፡ እና ይህንን መልዕክት እንድታደርስልኝ ነው እንዴ፣ ወደ እኔ የላከህ?»

«አይደለም፣ክቡር ሆይ»

«እኔም፣ አንተንም ለዚህ ብለህ መጥተሃል ብዬ አላስብም፡፡ ይሁን እንጂ፣ እዚህ ከደረስክበት ጊዜ ጀምሮ የሱልጣኑ ዜጋ እስከሆንክ ድረስ አክብሮትህን ልትገልፅላቸው ወይም ለኔ ልትገልፅልኝ እንደሚገባህ አላሰብክበትም»

«ክቡር ሆይ፣ ሙሉ በሙሉ አቅጄ ነበር፡፡ ነገር ግን ጊዜ . . . »

«አትቅጠፍ፣ እውነቱ የሚታወቅ ነው፡፡ ንጉሡ ከፈረንሣውያን ጋር ወዳጅነት እንድትመሠርትና ይህም የሕብረት ወዳጅነት በርግጥም በኛ ላይ እንዲሆን ታስቦ ነው የላከህ፡፡ ይህ ደግሞ እንግዳ ተቀባይነታችንን ባለማቋረጥ የሚሣደቡት የነዚያ የካቶሊክ ቀሣውስት ክፉ የእጅ ሥራ እንደሆነ እገምታለሁ»



ጥቁር ቀሚስና ነጭ ጥምጣም በመልበሣቸው ተለይተው የሚታወቁት ሙፍቲዎች፣ በስብሰባው አዳራሽ አንድ ጠርዝ ላይ እጅብ ብለው ተቀምጠዋል፡፡ ፓሻው ከተናገረ በኋላ የማዳነቅና የመስማማት ዓይነት መንሾካሾክ ጀመሩ፡፡ በፓሻው ፅናትም ተደሰቱ፡፡

«ክቡር ሆይ፣ ንጉሡ የላኩኝ የተወሰኑ ነገሮችን እንድ ነገ ነው»

«ምን?» አለ መሃመት ቤይ፣ ነጉድጓድ በሆነ ድመፅ፡፡ «ተጨማሪ ውሸት! ብትጠነቀቅ ይሻልሃል፡፡ ከዚህ አታላይ ባህርይህ ሊያድንህ የሚችለውን ግርፋት አልሰጥህም፡፡ አንተንና አንተን በመሰሉት ላይ ከረዥም ጊዜ በፊት ማከናወን ይገባኝ የነበረውን ነው የምፈፅመው»

ሙራድ እንደመጀመሪያው ጊዜ አንገቱን ደፋ፡፡

«ክቡር ሆይ፣ ርህራሄዎን ያሣዩ?»

«የማውቀውን ሁሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ልግለፅላችሁ፡፡ በግልፅና በተደጋጋሚ ወደ ንጉሥ ሉዊስ 14ኛ የተላከው የንጉሡ መልዕክተኛ መሆንህን ራስህ ተናግረሃል፡፡ በወታደሮች ፍተሻ ከሻንጣህ ውስጥ የተገኘው ደብዳቤ የሚገልፀው የአቢሲኒያውያን ንጉሥ በአንድ ተልዕኮ ላይ የሾመህ መሆኑን ነው፡፡ ያ ተልዕኮ ምንድን ነው?»

«የአቢሲኒያዊ ንጉስ ወደ ፈረንሣይ እንድሄድ መፈለጋቸው እውነት ነው»

«እኛ በአውሮፖ ላይ ጦርነት ስናካሄድ ከጀርባችን ልትወጉን፡፡ ከዚያ መንግስት ጋር ሽፍጠኛ ስምምነት ላይ ለመድረስ እንደሆነ አያጠራጥርም »

«አይደለም፣ ክቡር ሆይ» አለ ሙራድ ቀና ብሎ በመታነቅ አይነት ድምፅ

«እንግዲያው ለምን?»

«በእጭሩ ግርማዊ የፈረንሣይ ንጉስ፣ ነፍሳቸውን ስለታደጓት ለማመስገን ነው»

«ነፍሱን ስለታደጋት?»

«አዎን፣ ክቡር ሆይ! ጉዳዩ ቀላል ነው። ንጉሡ እጅግ ክፉኛ ይታመማሉ። በአገራቸውም ውስጥ አንዳችም መፍትሔ ያጣሉ። ስለዚህም ከፈረንሣይ ዕርዳታ ይጠይቃሉ። የፈረንሣይ ቆንሲል፣ የንጉሣዊውን የቤተመንግስት ቆንሲል፣ ስለሁኔታው ካስረዳው በኋላ፣ ለንጉሡ አንድ ፈረንሣዊ ሃኪም ላኩላቸውና ይኸው ሃኪም አዳናቸው። ከምሥጋናው ጋር እግረ መንገዱንም ለንጉሥ ሉዊስ ጥቂት ገፀበረከቶችን በማቅረብ ውለታቸውን እንድገልፅላቸው ነው።»

«ይህ ፈረንሣዊ ሃኪም የት ነው ያለው? ለመሆኑ አቢሲኒያ ሄዶ በዚያው ቀርቷል?»

«አይደለም፣ ክቡር ሆይ፣ ከኔው ጋር ወደዚሁ ተመልሷል። በዚህ በአሁኑ ሰዓት እዚሁ ካይሮ ውስጥ ነው»

መሃመት ቤይ ስለዚህ ጉዳይ የሚያውቀው አንዳችም ነገር የለውም። ይሁን እንጂ ስለዚህ ሐኪም፣ ከርሱ በፊት የነበረው ባለስልጣን አጃቢዎች ሲያወሩ ሰምቷል። ከአካላዊ ጤንነት ጉዳይ ጋር በተዛመዱ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ እምነት ስላላቸው፣ ከዚህ መረጃ በኋላ፣ ፓሻው በእስልምና ዶክተሮች ላይ ላለው ጭፍን እምነት ወሰን አበጀለት። በጦር ሜዳዎችም ቢሆን፣ ክርስቲያኖች በሙሮች ላይ መድሃኒትን በተመለከተ የበላይነት እንዳላቸው ብዙ ጊዜ አስተውሏል። ከዚህም በላይ የመድሃኒትን ጥበብ የሚያከናውኑት ብዙዎቹ ሙሉ በሙሉ ሃይማኖተ ቢሶች ናቸው። እነዚህን ሰዎች ደግሞ ሙያቸውን በስኬት ከማከናወን የሚያግዳቸው ነገር እንደሌለም ያውቃል። በዚህም የተነሣ፣ የተነሣው ርዕሰ ጉዳይ ሃይማኖታዊ ስላልሆነ በዚህ ረገድ ያለውን አቋሙን ማስዘብ እንደሚሻለው ወሰነ። ባለፉት ዓመቶች ጉልበቶቹንና የመገጣጠሚያ አካላቱን እያሣበጠ በሚያሳምመው በሽታ፣ ጠንከር ባለ ሁኔታ ይሰቃይ ስለነበረ፣ በተጠቀሰው ፈረንሣዊ ሃኪም ላይ ይበልጥ ስሜቱ ጠነከረ። አርመናዊው በቀጥታ የንጉሡን ሕመምና ፖንሴ የተጠቀማቸውን ዘዴዎች ለመግለፅ ፈቃደኛ ባይሆንም፣ ፓሻው ብዙ ጥያቄዎችን ጠየቀው። ከሙራድ ጋር ከረር ባለ ሁኔታ ለመቀጠል ፈልጐ የነበረው ፓሻ፣ ሙራድ ስለጉዞው በሰጠው ምክንያት ስሜቱ በረድ ያለ መሰለ። በመጨረሻም አሰናበተው።

«የመንግስት መልዕክተኛ፣ እዚህ ያለኸው እኔ ወድጄ በሰጠሁት ፈቃድ እንዳልሆነ እንዳትዘነጋ። በማንኛውም ሰዓት ግን፣ እዚህ ቀርበህ ትዕዛዜን ልሰጥህ ስለምችል ትመጣለህ። የያዝከው መልዕክት የተለየ መብት አያሰጥህም። ለብልግናህም ማስረጃ ሊሆንህ አይችልም።



አሁን በቀጥታ ወደ ፈረንሣዮች ዘንድ ሂድ። ነገር ግን፣ ከነርሱ ካህናት ጋር እያሴርክ መሆንህን እንዳውቅ አታድርገኝ። ሰምተኸኛል?»

«ክቡር ሆይ» አለ ሙራድ ከመጨረሻው እምብርክክ በኋላ። «ሁሉንም ነገር አረዳለሁ። ከኔ የበለጠ ታማኝ አገልጋይ ፈፅሞ ሊኖርዎ አይችልም»

«እንዲሆን እግዚአብሔርን እለምነዋለሁ» አለ ፓሻው

አርመናዊው ሰላምታ አቅርቦ፣ ከአዳራሹ ሲወጣ ጉንበስ ብሎ፣ ወደ ኋላው ተራመደ። ወዲያውኑ ግን ቆመና

«ክቡር ሆይ! ደብዳቤዬስ!»

«አንተም ዲፕሎማት ነኝ ብለህ ማስመሰል በመቻልህና ንጉሡም ለፈረንሣይ መልዕክት ይዘህ እንድትቀርብ ስለሾመህ ደብዳቤህን ፈረንሣይ ቆንሲል ውስጥ ታገኘዋለህ»

ይህ የተሰጠው መልስ፣ ወደፊት ሁኔታዎችን እንደሚያወሣስብ ታየው። ነገር ግን ስንብቱ በጣም ስላስደሰተው፣ ጭንቅላቱን ትከሻው ላይ ዘለስ እንዳደረገ፣ በቅሎውንም ረስቶ የሩጫ ያህል ወጥቶ ሄደ።

ሙሴ ዴ ማይሌም መልዕክተኛውን ለማየት የተዘጋጀ መሆኑን የሚገልፅ መልዕክት ላከ። የዚያኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ፣ የንጉሡ ነገስቱ መልዕክተኛ ፈረንሣይ ቆንሲል ውስጥ ተገኘ።

ሙራድ፣ ከፓሻው ጋር የነበረውን ውይይት አጠናቅቆ ሲወጣ በጣም ደንግጦ ነበር። ካይሮ ሲደርስ ይሰማው የነበረው ደንታ ቢስነትም ጨርሶ ጠፍቶበታል። በአቋሙ ጸኑ ሆኖ እንዲቆይ ፖንሴ የሰጠው ምክር ቢኖርም፣ አርመናዊው፣ ከፈረንሣውያኑ ጋር የነበረው በቀላሉ የመዛመድና የመቀላቀል ስሜቱን ፈፅሞ ተወው። ቆንሲሉን የሚያስደንቁት ነገሮች ማብቂያም የላቸውም። ሙራድ ወደ ቢሮው ሲገባ፣ ፓሻው ዘንድ እንዳደረገው በጉልበቱ ተንበረከከ። ሙሴ ማቹ እንዲቆም አደረገው። ቆንሲሉ ግን፣ አንዲት ባሏ የሞተባትን የመስፍን ሚስት፣ ነፋስ

በድንገት ቀሚሷን ቢገልብባት የሚያሣየውን ትህትና ዓይነት በማቅረብ ምንም እንዳላስተዋለ አስመሰለ፡፡

«ውድ ጌታዬ» አለ ቆንሲሉ፣ ሁሉም ተደላድለው ከተቀመጡ በኋላ፡፡ «የቱርካውያኑ ፓሻ፣ አንተ እዚህ ከደረስክበት ጊዜ ጀምሮ ሲናፈስ በነበረው ወሬ በጣም ስለተደናገጠ፣ ስለማንነትህ እርግጠኛ መሆን እንዳለበት አሰበ፡፡ እንዲህ ካለ የወዳጅነት ጥሰት ባህርይ ጋር ግንኙነት እንደሌለኝ ስነግርህ እመነኝ፡፡ እኔ፣ ሁሉንም አይነት የሃይል ሁከት እጠላለሁ፡፡ ነገር ግን ቱርካውያን ለራሣቸው የተወሰኑ መብቶችን ስለሰጡ፣ በባዕድ አገር ያለው የኛ ኑሮ ዕጣ ፈንታው ይኸው ነው፡፡ የዚህ ሁሉ ሥራ አንዱ ፍፃሜ የሆነው ከቤትህ ተበርብሮ የተወሰደውን ደብዳቤ ፣ ፓሻው፣ በእኔ እጅ እንዲደርስ ማድረጉ ነው፡፡ እዚህ አገር ከገባህበት ጊዜ ጀምሮ እንድታሣየኝ በከንቱ ስታደክመኝ የነበረው ደብዳቤ ይኸው አሁን በኔ ቁጥጥር ሥር ሆነ፡፡ በርግጥ እጅግ መጥፎ ይሆንብህ የነበረውን ሁኔታ ሁሉ ያስቀረልህ አንድ የዕድል ውጤት አለ፡፡ ይኸውም፣ አንተ ከጥርጣሬ ባሻገር፣ የንጉሡን እውቅና ያገኘህ መልዕክተኞቸው መሆንህንና ይህ ሠነድም እውነተኛውን የንጉሠ ነገስቱን ማህተም የያዘ መሆኑን ማወቅ ችያለሁ፡፡ ስለዚህም አክብሮቴን ልገልፅልህና የአቢሲኒያው ንጉሠ ነገስት መልዕክተኛ አድርጌ ስቀበልህ ክብር የሰማኛል»

ሙራድ በአክብሮት ጭንቅላቱን ጉንበስ አደረገ፡፡ ወዲያውኑ ገልመጥ ብሎ፣ ከዚህ ከሚሰማው መልካም ዜና ጋር ተጐዳኝቶ ያልተጠበቀ ውርደት ይገጥመኝ ይሆናል በሚል ዙሪያውን ቃኘ፡፡

«የሹመት ደብዳቤው» ሲል ሙሴ ዴ ማይሌ ቀጠለ፡፡ «በማያወላዳ ሁኔታ ሕጋዊነትን ሲያረጋግጥ፣ ንጉሡ የቬርሣይለስ ቤተመንግስትን እንድትጐበኝ መመኘታቸውን የሚጠቅስ ነገር የለውም፡፡ ፈቃደኛ ከሆንክ በሚከተሉት ላይ እንስማማ፡፡ በካይሮ ቆይታህ ወቅት ለቤተሰብህ ጭምር፣ እንደሚመስለኝ ሦስት ናቸው፣ ያወጣኻቸውን ወጭዎች እንተካልሃለን»

ሙራድ ጭንቅላቱን ነቀነቀ

«በፈለግኸው ጊዜ ልትጠቀምበት የምትችለው፣ ከቆንስላው ሂሣብ ላይ የሚከፈል አምስት አቡኪል በየወሩ እናስቀምጥልሃለን፡፡ ተልዕኮህ ግቡን መምታቱን እርግጠኛ በምትሆንበት ጊዜና ወደ አቢሲኒያ ስትመለስ፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ እናደርግልሃለን፡፡»



«ነገር ግን» አለ ሙራድ እየፈራ፣ የፖንሴን ምክር አስታውሶ፣ «ከሹመት ደብዳቤዩ በተጨማሪ ለንጉስዎ የማደርሰውን የግል መልዕክትም ይዣለሁ»

«ነገርኩህ እኮ» አለ ቆንሲሉ፣ የተዘጋጀለትን ሸርባ ለመመገብ ከማይችል ሕመምተኛ ጋር የሚያወራ ይመስል ረጋ ባለ አነጋገር፣ «ደብዳቤው እኮ መልዕክቱን አንተው ማድረስ አለብህ አይልም፡፡»

«ይህም ሆኖ . . . » አለ ሙራድ ድክም ብሎ

«ውድ ጌታዬ» አለ ቆንሲሉ መረር ባለ መልክ፡፡ «ጉዳዩ እኮ ሙሉ በሙሉ ቀላል ነው፡፡ በዚህ ላይ ምንም ውስብስብ ነገር ባንጨምርበት፡፡ ለንጉሡ መልዕክት አለህ፡፡ መልካም፡፡ እንግዲያው ለኔ አስረክበኝ፡፡ የተፃፈ ከሆነ እኔ እልከዋለሁ፡፡ ነገር ግን ፓሻው ባደረገው ፍተሻ፣ እኔ እስከማውቀው ድረስ እንዲህ ያለ ነገር አላገኘም፡፡ በቃል የተላከ ከሆነም፣ ይፋዊ በሆነ መልዕክት እኔው በታማኝነት አስተላልፈዋለሁ፡፡ ምናልባት መልዕክቱ ከስጦታ ጋር አብሮ መቅረብ ያለበት ከሆነም በራሣችን መርከብ እንልከውና ወደታቀደለት ቦታ በሰላም እንዲደርስ እናደርጋለን፡፡»

«ነገር ግን ! ንጉሡ፣ ራሴ ሄጄ ለማድረስ ርግጠኛ እንድሆን ነግረውኛል»

«ስማ» አለው ቆንሲሉ «ፈጥነህ መልስ ለመስጠት አትጣደፍ፡፡ ዝግ ብለህ አስብበት፡፡ ከዚህ ከተማ ባህል ጋር ራስህን እስክታለማምድና እዚህ ያለህን ተልዕኮ እስክትረዳ ጊዜ እንደምትፈልግ ይገባኛል»

ከሁሉም ነገር በላይ፣ ሙራድ፣ በጊዜ ርዝመት ውስጥ የርሱ ሁኔታ የማያስተማምን መሆኑን እንደሚረዳና የተሻለው ምርጫ ምን ሊሆን እንደሚችል እንደሚገነዘብ፣ ሙሴ ዴ ማይሌ ያምናል፡፡ ከዚህ በኋላ፣ ከቆንሲሉ ጋር ሰፊ ክርክር ተደረገ፡፡

«መልዕክቱን አንተው በግንባር ባለማቅረብህ ንጉሡ እንደጥፋት አይቆጥሩብህም፡፡ እውነቱ ደግሞ ጉዳዩ ቀላል መሆኑ ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ አንተ በአፊሴል ወደ አውሮፖ መሄድህን ይቃወማሉ፡፡ በመካከላችን ላለው መልካም ግንኙነት ምስጋና ይግባውና እዚህ ሊጋሲዮኑ ውስጥ መገኘትህን ይቀበላሉ፡፡ ነገር ግን ወደፈረንሣይ በመጓዝ በመርከብ ላይ እንድትሣፈር በምንም አይነት አይፈቅዱልህም፡፡ ለመሆኑ ራሴን ግልፅ አድርጌአለሁ?»

ሙራድም ከዚህ የተለየ ነገር እንደማይኖር ስላወቀ ተስማማ። በሰማው ዜናም ሰራሱ እየተደነቀ እፎይታ አገኘ። በልቡ፣ ከነፋሱና ከሞገዱ ጋር እየተላተመ፣ ንጉሥ ሉዊስ 14ኛን ለመጉብኘት ምኞቱም የለውም። የንጉሡ ሥዕል ከላይ ወደ ታች በቆንሲሉ ላይ እንዲታይ በመደረጉ፣ ቆንሲሉን፣ ከፓሻው ይልቅ አስፈሪ አድርጎታል። ከሙሴ ዱ ማይሌ ጋር ያደረገውን ውይይት በደስታ አጠናቅቆ፣ በዘጠኝ ሰዓቷ ፀሐይ ኃይል እያላበው፣ አስደናቂውን ዜና ለፖንሴ ሪፖርት ለማድረግ ተመለሰ።

❧

በአየር ጠባዩ ላይ በተፈጠረ ያልተለመደ ምክንያት፣ ግብፅ ውስጥ ያደጉ የዝዮች ላባ፣ ዋጋ ቢሶች ናቸው። አውሮፖ ውስጥ እንደሚገኙት የዝዮች ላባ፣ ወረቀት ላይ ሲያርፉ ጠንካራና ቀጥ ያሉ በመሆን ፈንታ ሲበዛ ደካማና እጥፍጥፍ የሚሉ፣ ቀለም ውስጥ ሲነከሩ የበሰበ የሚለሰልሱ ይሆናል። ስለዚህም ለሙሴ ማይሌ እነዚህ ላባዎች የተላኩለት ከፈረንሣይ ነው። የቆንስላው ተቀጣሪዎች መፃፍ የሚገደዱት በአገር ውስጥ ውጤቶች ሲሆን፤ ጥሩዎቹን ላባዎች ከስንት አንድ ጊዜ በራሱ የእጅ ጽሁፍ ለሚያዘጋጃቸው ደብዳቤዎች መፃፊያ ያስቀምጣቸዋል። በዚያን ዕለት ምሽት፣ ለሙሴ ዱ ፖንቻርትሬይን፣ በራሱ እጅ ለመፃፍ ቆረጠ። በሰዓት ማሰሪያው ላይ ተደጋግሞ በመመላለስ የሚሰማው ህመም ቢሰማውም፣ሥቃዩን ፈርቶ ሃሣቡን ለሚኒስትሩ በራሱ እጅ ከማስፈር አያግደውም። ረዥምና ጋደድ የሚለው የብዕር አጣጣሉ በፋኖሱ ብርሃን ስር ያበራል።

*ለንጉሡ መልዕክተኛ፣ ቱርኮች የርሱን ወደ ፈረንሣይ መጓዝ እንደሚቃወሙ አመለክቼዋለሁ። የምር ከተናገርኩ እውነቱ በትክክል ይህ አይደለም። በካይሮ የሚገኘው ፓሻ እኛ አስተያየት ከፃፍን እንደህ ዓይነቱን ተልዕኮ ለመከልከል ሥልጣን የለውም። ይሁንና የአቢሲኒያውያን ኤምባሲ፣ ለረዥም ጊዜ ባለን ጥሩ ግንኙነት ላይ መጥፎ ስሜት ማሣደሩና ከፍተኛውን ባለሥልጣን ማስከፋቱ እንደማይቀር እውነት ነው። ይህ አባባል በተዘዋዋሪ መንገድ እውነት ሲሆን፣ ቱርኮችም እንዲህ ዓይነቱን ጉዞ በርግጥ ሊያደናቅፉ አይችሉም። በዚህ ጉዳይ ላይ ጠበቅ አድርጌ ልገልፀው የምሻውና ይህንንም እንዲያምን የሚያደርገኝ ነጥብ አለ። ይኸውም የነገስታትን ንጉሥ ወክሎ እዚህ የሚገኘው ሰው ለዚህ ሃሣብ ተቃውሞ እንደማያስነሣ ነው።*

*የሃሣቤን አመክንዮ ሠፋ አድርጌ እንዳብራራ ይፍቀዱልኝ። አቢሲኒያውያን በመልካም ሁኔታ የጀመሩት ሃሣብ የኛን ፍላጐት ወደፊት ሊያራምደው የሚችል ምልክት ሆኖ ሊያድግ ካልቻለ ትልቅ ሃፍረት ይሆናል ብዬ እፈራለሁ። በዚህም ባቢያ፣ ሥራውን ከጀሰዊቶች እጅ በመውሰድ፣ በኛ እይታ መሠረት እኛው እንድናከናውነው ሃሣብ አቀርባለሁ። ለመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ የጀሰዊቶች ፍላጐት ምን ነበር? የአገሪቱን ሃይማኖት ለመለወጥ ነው? ይህን እንዲያደርጉት፣ በአባ ብሬቬደንት ያለጊዜአቸው መሞት ተስናክሉባቸዋል። ይሁን እንጂ፣ ይህን ሁሉ ርቀት ከመንግስት መልዕክተኛው ከሙራድ ጋር ተጉዘው ከመጡት ሦስቱ አቢሲኒያውያን ጋር ወደ ፈረንሣይ መጓዝ ቢችሉ፣ ጉዞው የተሣካ ነበር ብለው ያስባሉ። እነዚህ ሰዎች፣ በጥሩ የአባቶች ትምህርት ቤት በሚገባ በትምህርት ታንፀው ወደ ሃገራቸው እንዲመለሱ ቢደረጉ የአገራቸውን ሕዝብ ከባዕድ ሰው ይልቅ ለማሳመን ትልቅ ዕድል ይኖራቸዋል። የኢየሱሳውያንን ማህበረሰብ የሚያሳስባቸውም ይኸው ነው። በኔ አስተሣሰብ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ሙሉ በሙሉ መደሰት ይገባቸዋል። በስሌታቸው ተደፋፍረውና፣ አዲሶቹን አቢሲኒያውያን ተረጂዎቻቸውን በማዘጋጀት ሥራ ላይ ተመስጠው፣ ይህም የወደፊቱን የመንግስት መልዕክተኛ ይጨምራል፣ የጀሰዊት አባቶች ቢያንስ ለጊዜውም ቢሆን እንኳ፣ ወደ ንጉሡ ኤምባሲ በመላኩ ጉዳይ ላይ ከእንግዲህ በኋላ ፍላጐት አይኖራቸውም። በተቃራኒው፣ እኛ በነፃነት ለብቻችን ብንንቀሣቀስ እነርሱን ከማርካታችንም በላይ ሰፊ ጊዜ እንዲኖረን እናደርጋለን። በዚህ ላይ፣ ይህን ዕድል በመጠቀም በተቻለ ፍጥነት ከመንግስት መልዕክተኛው ከሙራድ ጋር ሊጓዝ የሚችል የራሣችንን ኤምባሲ ወደ ንጉሡ እንድንልክ ሃሣብ አቀርባለሁ። ከሙራድም ጋር ቢሆን፣ ራሣችንን በማራቅ በመጨረሻ ስሙን የራሣችን እናደርጋለን።*

*ለሽልማት የሚያበቃው የጉዞው መሪ መልዕክተኛችን፣ የፖንሴ ተግባር፣ ጉዞው የሚቻል እንደሆነ ከማሣየቱም በላይ አደገኛነቱም ማንም ከሚያስበው በታች መሆኑን ነው። እውነተኛ ኤምባሲ በመላክም፣ ዳግመኛ ድንገቴ በሆነ በመድሃኒት ቀማሚ ፍላጐትና ለምሮት ላይ እምነት አንጥልም። ከዚህም ጋር አጠቃላዩ ተልዕኳችን አነሰም በዛም፣ ፍላጐታቸው በጥልቁ ውስጣቸው ውስጥ በስልት ተሸፍኖ ካሉ ድብቅ ቀሣውስት ጋር*

ይደራደራል ብለን አንፈራም። እንዲህ ያለው ኤምባሲም በእውነተኛ ዲፕሎማ ከተመራ፣ ከኢትዮጵያ ንጉሥ ጋር በጠንካራ መሠረት ላይ የሚገነባ የፖለቲካ ግንኙነ ለመመስረት ይችል ይሆናል። ከዚሁ ጋር በተጓዳኝ በፈረንሣይ የምሥራቅ ሕንድ ኩባን ስም ከፍተኛ ተስፋ ያለውን የንግድ ሸርክናም ያዳብራል። በዚህች አገር ውስጥ ወር በብዛት እንዳለ እናውቃለን። የተፈጥሮ ሃብቷም ቢሆን ገና ያልተነካ ነው። አገሪ በአሁኑ ጊዜ ከተከከር ሙሉ በሙሉ ነፃ ሆና ያለችና ወደ ሩቅ ምስራቅ ለመድረስ መነ መሆን የምትችል ናት።

ይህን የመሰለውን ተልዕኮ ማን ሊመራው ይችላል ብለው ይጠይቁ ይሆናል ምንም እንኳ ጠልቄ ባላውቀውም፣ በቅርቡ በላኩልኝ ደብዳቤ ላይ መምጣቱን የገለፁልኝ በኔ ሥር በሚገኘው፣ ዳሚየታ ውስጥ የምክትል ቆንሲልነትን ሃላፊነት ማሟላ የሚችለውና ለዚህ አይነቱ ሥራ አስፈላጊው ብቃት ሁሉ ያለው፣ ምስጉኑ የንጉሠ ነገስ ባለሟል ፈረሰኛ፣ ሌ ኖይር ዱ ሮውሌ ነው።

ሙሴ ሌ ኖይር ዱ ሮውሌን ለመምረጥ ዕድሉን እንዳገኝ ላደረጉኝ ቤተሰቢ ያለኝ የፍቅር አክብሮት እገልፃለሁ። በዚህ ባቀረብኩት ሃሣብ የራሴን ፍላጐት ከንጉሡ በላ አድርጌ እንደማላስቀምጥ እንደማረጋግጥ ተስፋ አለኝ። በድፍረት ተስፋ የማደርገዉ ሁለቱም እንደሚገጣጠሙና ሙሴ ሌ ኖይሬ ዱ ሮውሌም፣ ላቀርባለት በምችለው ክብር ሃብት እንደሚያንፀባርቅ፣ከሁሉም በላይ ከሴት ልጄ ጋር ተጋብቶ ቤተሰቤን በማኩራነ ትክክለኛው አቻ እንደሚሆን በማሰብ ነው።



# 7

ጆን ባፕቲስት፣ የሙራድን ዜና ከሰማ በኋላ፣ ጨዋታው ማብቃቱንና ከዚህ በኋላ የሰኬት ነገር እንደማይቻል ተገነዘበ። በቆንሲሉና በፓሻው መካከል ተራ የሆነ የፍላጐት መገጣጠም ይሁን ወይም ቅን ስምምነት የፈጠረው ህብረት፣ ከኤምባሲው ጋር እስከ ቬርሣይለስ የመጓዙን ዕድል አጠፋው። ሙራድ፣ መልዕክቱን ለቆንሲሉ ለመስጠት ቢስማማ፣ ዲፕሎማቱ ለንጉሡ ከማድረሱ በፊት ለራሱ ዓላማ በሚያመች መልክ ይቀይሰዋል። በዚህም የተነሣ እየናቀው እንዳለው፣ የፖንሴን ፍላጐት ለማሣካት የሚያስችለው ቅንጣት ታህል ዕድል አይኖረውም።

ያ ሁሉ ጥረት፣ ማብቂያ ያልነበራቸው የሚመስሉት የጉዞ ቀናት፣ መከራውና ችግሩ ሁሉ መና ቀረ። ሁለት መልካም ዜናዎች በተከታታይ ሣይደርሱት ቀደም ብሎ፣ ጆን ባፕቲስት በተስፋ መቁረጥ ውስጥ የሚሰጥምበት ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። እነዚህ ሁለት መልካም ዜናዎች የወደፊቱን አተያዩን በምንም መልኩ ሳይለውጡ ተስፋ ያሰበትን ቅፅበታዊ ደስታ አላበሱት።

በቀዝቃዛው ጥላማ በረንዳ ላይ ከሜትር ዠረሚ ጋር በመሆን እየተወያዩና ርዕሰ ጉዳዩን በሁሉም አቅጣጫ ሲመለከቱት ወደ ቬርሣይለስ የሚደረገው ጉዞ በፍፁም ድርድር እንደተደረገበት እርግጠኛ በሆኑበት ጊዜ፣ አንድ ዘበኛ ከቆንስላው ጽህፈት ቤት ሙሴ ዱ ማይሌ የላከለትን ማስታወሻ ሊሰጠው መጣ። ቆንሲሉ፣ «ሙሴ ፖንሴ» በሚቀጥለው ቀን «በግርማዊ የአቢሲኒያ ንጉሥ ክቡር ተወካይ» እዚህ መድረስ ክብር ሲባል በሚደረገው የዕራት ግብዣ ላይ እንዲገኝ ይጋብዘዋል። ጆን ባፕቲስትን ያስደሰተው ግን በዝርዝሩ ውስጥ «ክቡር የፈረንሣይ ቆንሲል፣ ማዳም ዱ ማይሌ እና ሴት ልጃቸው» የሚለው ብቻ ነበር።

ከዚህ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ፍራንቾይዝ በቤትዋ መስኮት በኩል ብቅ አለችና ዘልላ በረንዳው ላይ በመውጣት፣ ከእራት ግብዣው በዓል በኋላ፣ እሲስን ለብቻዋ ሊያገኛትና ሊያያት ከፈለገ ሊከተለው የሚገባውን እያንዳንዱን ዝርዝር እቅድ አብራራችለት። መልዕክቱን ካጠናቀቀች በኋላ በመድሃኒት ቀማሚው ቤት ውስጥ ሽርጉድ በማለት ምንም እንዳልጠፋባቸው

ለማየት በማሰት እንደሆነ ተናገረች። የምታደርገውን ፍተሻ ሜትር ዠረሚ መድሃኒት የማቀሳቀሱን ዝግጅት ለማድረግ ወደሄደበት እስከ ምድር ቤቱ ድረስ አዘለቀችው። እርሱም በማጉረምረም ስለተቀበላት ምስኪኗ ሴት በመጣደፍ ወደ ፎቁ ወጥታ በመመለስ፣ በስሜት ውስጥ የነበረውን ፖንሴን በማለፍ ቀደም ሲል በገባችበት በኩል ሾልካ ተሰወረች።

በሚቀጥለው ዕለት ከዕራት በፊት ያሉት ሰዓቶች እንዲገባደዱለት በማለት፣ ፖንስ በቤቱ ውስጥ ተደብቆ ቆየ። ቀትር ላይ ግን ሙራድን ለማየት ሾልኮ ወጣ። በዚህ ዕለት ማታ፣ በቆንስላው ውስጥ የመንግስት መልዕክተኛው ሊያሣየው የሚገባውን ፀባይ በዝርዝር ገለፀለት። የሙራድ የመጀመሪያው የማህበራዊ አቀራረብ መልኩ፤ ወደ ፈረንሣይ ቤተመንግስት እዳይሄድ፣ ቆንሲሉ እንዲከለክሰው ምክንያት ሊሆነው ይችላል የሚል ሥጋት ፖንሴ ነበረው። ከዚያ በኋላም ወደ ቤት ተመለሰና እዚያም ማንኛውንም ጉብኚ ሰላም እንኳ ላለማለት ከመቸውም ጊዜ ይልቅ ዠረሚን አኩርፎ አገኘው። በነጋዴዎች አካባቢ እያንዳንዱ ሰው የፖንሴን የጉዞ ታሪክ ከሌላው ቀድሞ ለማወቅ ጠንከር ያለ ጉጉት አድሮበት ነበር። መድሃኒት ቀማሚው እስከ አሁን ድረስ ታሪኩን ለማንም ሰው ስላልተናገረ፣ የተሰጠው ግምትም ዕለት ተዕለት እየጨመረ ነበር። አባ ፐላንቴይንም ሶስት ጊዜ ያክል መጥተው ነበር። ይሁን እንጂ ሜትር ዠረሚ በሩን እንዳያልፉ ስለተጋረዱባቸው፣ ጀስዊቱ፣ በፕሮቴስታንቱ ትከሻ ላይ አሻግረው በቤቱ ውስጥ ምን የተደበቀ ምስጢር እንዳለ ለማየት ወዲያና ወዲህ ተሟሟሩ። ሙራድም እንዲሁ ማንንም ስለማይቀበል አባ ፐላንቴይን ከፋኛ ቅሬታ ያሰማሉ። እርሣቸው፣ የአባ ብሬቬደንትን የአሟሟት ታሪክ እንዲሁ ለመስማት ይፈልጋሉ። ሜትር ዠረሚ፣ እነሀን ጀስዊት ወደ መንገዱ ላይ ገፍትሮ ከመወርወር ራሱን ገትቶ፣ የምሬት ቅሬታቸውን በትዕግስት ቢያዳምጥም፣ ከቆመበት ሥፍራ ግን አንዲት ጋት እንኳ ፈቀቅ አላለላቸውም።

በመጨረሻ የእራት ሰዓት ደረሰ። ጆን ባፕቲስትም በጥንቃቄ ልብሱን ለበሰ። ከባህር ላይ ወንበዴዎች የገዛቸው ልብሶች፣ በሰላማዊ ጉዳዮች ላይ ከአስፈላጊው በላይ የሚያሸበርቁ ቢሆኑም፣ ለዛሬ ምሽት ሁኔታ ግን ፍፁም ተስማሚ ነበሩ። እፁብ ድንቅ መሆኑን ጓደኛው ሜትር ዠረሚ አረጋገጠ። ፖንሴ በበኩሉ በጓደኛው ዐይኖች ውስጥ የቅሬታ ሁኔታዎችን አነበበ። ይህ ቅሬታ ብዙም ጉጉት ባላሳደረበት ከዛሬው ምሽት በዓል ውጭ በመሆኑ ሳይሆን፣ ሁሉም ሥራ፣ አደጋውና የወራት ጉዞ ድሳቸው፣ የማይቀበሉትና የጥፋት እውነቶች ሆነው፣



እርሱ የዋህ እምነቱን በታማኝነት ደዞ እንዲቆየው እንዲደበቁና በምስጢር ደረጃ ገቶ በማለታቸው ነው።

ወደ ቆንስላው እየተጓዘ ሣለ፣ መልካም ስሙን ለመጠበቅ፣ ከፍተኛው አስተዋፅኦ የሜትር ዠረሚ ስለሆነ፣ ውለታውን ለመመለስ፣ ከፈረንሣይ ሆኖ በተሻለ ብቃት መስራት እንደሚችል ማሰላሰል ጀመረ። ይህም ወደ ቬርሣይለስ ኤምባሲውን መርቶ ለመሄድ አንድ ተጨማሪ ምክንያት ይሆነዋል። ሆኖም የዚህ ዓላማ የስኬት ዕድል ይበልጥ እየራቀ ነው።

እራት በታላቅ ሥርዓት እንዲቀርብ ሙሴ ዱ ማይሌ አዘዘ። የንጉሡን መልዕክተኛ እንኳን ደህና መጣህ ሊለውና ባጋጣሚውም ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ላይ ሊክሠው ፈለገ። ዘበኞቹ፣ በድል አድራጊ ወታደር ባህል ዓይነት በዋናው የመግቢያ ደረጃ ላይ አሽሟጣጭ ጉራዴአቸውን በግራና በቀኝ ከፍ አድርገው በማገናኘት፣ ለሚመጣው እንግዳ ማለፊያ ቅስት ሠርተው በተጠንቀቅ ቆመዋል። በተትረፈረፈ መጠን የተዘጋጁ መብራቶች በባለጌጥ አቃፊዎች ላይ ተቀምጠው የአዳራሹን መግቢያና ታላቁን የእንግዳ መቀበያ ክፍል ፍፁም እንዲያሸበርቁ አድርገዋል። ከዚህም በላይ በወርቃማ የስዕል ፍሬሞች፣ በተወለወለው የወለል ጣውላና ሌላው ቀርቶ በአስናጋጆች ልብሶች ላይ ባሉት የነሃስ ቁልፎች ላይ ብሩህ አንፀባራቂ ብርሃን ፈንጥቀውባቸዋል። ይህ ከፍተኛ ብርሃን ፊቶቻቸውን በአብረቅራቂው ሃይሉ አጥለቅልቆትና ከመጠን በላይ አጋንኖባቸው ስለነበረ፣ ሴቶቹ በዚህ ሰው ሠራሽ ብርሃን በደስታ ተሞሉ። በፈረንሣውያን ማህበረሰብ መንደር ውስጥ የሚኖሩት ሴቶች፣ ምንም እንኳ በአብዛኛው ጉናቸው ክብር የሚገባቸው የነጋዴዎች ሚስቶች ቢሆኑም፣ አሁን ባለው ሕይወታቸው ውስጥ ረግተው ከመኖራቸው በፊት፣ እጅግ ምስቅልቅልነት የበዛበት ሕይወት ነበራቸው። የመጀመሪያውና በአጠቃላይ ለረዥም ጊዜ የነበረው ሕይወታቸው የንግድ ሱቅ ላይ ያተኮረና ወይም እንዲያውም በጉዞ መዝናኛዎች ላይ መሥራት ነበረ። ጆብደኛ የትዳር ጓደኞቻቸው በመጨረሻ ላይ ካይሮ ውስጥ ሃብት ሲያገኙ፣ እነዚህም ሴቶች ገደብ የለሹን ፍላጐታቸውን ለማርካት ስለቻሉ ወደመከበሩ ደረሱ። የአልማዝ ጌጦቻቸውን በሕገወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ ከሚገቡ የአይሁድ ነጋዴዎች በመግዛት፣ የእጅ ዋጋዋን ሲከፍሏት ሳልቻሏት የአሥራ ሁለት ዓመት ልምድ ላላት የአረብ ልብስ ሰፊ ሴት በመስጠት፣ በወቅቱ በፖሪስ ውስጥ ያለውን ፋሽን ኮፒ እንድታደርግላቸው ያደርጋሉ። እነዚህ አርቲፊሻል ጌጣጌጦችንና መዋቢያዎች፣ ቁመናቸውን ለማስዋብ የበቁት፣ ሥራና ወሲባዊ ፍላጐታቸው፣ የአበባ ጊዜያቸውን በእጅጉ

ከሸረሸሩት በኋላ ዘግይተው ነው፡፡ ቢሆንም ግን፣ እነዚህ የቅንጦት ባህርያት ናቸው፡፡ የማስፈለጋቸው ምክንያት ደግሞ የተገዙት ጌጣጌጦች ጥራት፣ ስለባለቤቱ ማንነቱን የሚገልፁ ናቸው፡፡ የስውነቱ መነጣጠሚያዎች ያባበጡበትና፣ በከተማ ውስጥ በዘመነኛ ባለ አንድ ፈረስ ሠረገላው ሲዞር የሚውል ሰው፣ ለፈረሶቹ ደህንነት በእጅጉ ሲጠነቀቅ፣በምሽት ስአት ወጣትነትዋ የሸሻት ሴት አዲስ፣ ደማቅና የለበሰችውን ለስላሣ ጨርቅ ያለሃፍረት በወንዶች እግር ላይ ስታሻሸው ሲመለከት ለአይን አስደሳች ትሆንበታለች፡፡

በመጨረሻ ከደረሱት ሁለት ተጋባዦች አንዱ የሆነው ጆን ባፕቲስት፣ ለቆንሲሉ ያለውን አክብሮት ገለፀ፡፡ በዚያን ጊዜ ቆንሲሉ በአዳራሹ መግቢያ ላይ ለእንግዶቹ ሰላምታ በመስጠት ይቀበላቸው ነበር፡፡ በኋላም፣ ቆንሲሉ፣ ሃር በለበሱ፣ በሉልና በሚያንፀባርቁ የከበሩ ድንጋዮች ባጌጡ፣ ሴቶች መካከል በርሱ ዓይን ለሽልማት የምትብቃዋን ለማግኘት በሰዎች ውስጥ ሰጠመ፡፡ በዚህ ታላቅ በዓል ጊዜ የምድር ቤቱ ክፍሎች በሙሉ ተከፍተዋል፡፡ የእንግዳ መቀበያው ክፍል አሁንም የፀሃዩ ንጉሥ ሥዕል ሲታይበት፣ የቆንሲሉ ወንበር ግን ተነስቷል፡፡ ከበስተጀርባ የሚገኘው ሌላው በኢኮኖሚ ምክንያት በአዘቦቱ ጊዜ ተዘግቶ የሚኖር ክፍል ለዛሬው ምሽት የእራት ግብዣ ሲባል ጠረጴዛዎች ገብተውበታል፡፡ በዚህ ቦታ አሊስ አልነበረችም፡፡ በመጨረሻም፣ ጆን ባፕቲስተ ባልጠበቀው ክፍል ውስጥ አገኛት፡፡ ክፍሉ፣ ሴቶች በምሽት ሲደክማቸው የሚያርፉበት የሙዚቃ ክፍል ነው፡፡ በንር በኩል ወዳለው መስኮት አጠገብ፣ በቀላል ውበት የተጌጠ አረንጓዴ ፒያኖ ግድግዳውን ተደግፎ ቆሟል፡፡ አሊስ፣ በእሣት ማንደጃው ምድጃ ላይ ከተቀመጠው ትልቅና ረዥም መስተዋት አጠገብ ቆማለች፡፡ ጆን ባፕቲስት ወደዚህ ክፍል በድንገት ሲገባና ከኋላ በኩል ሲያያት ደነገጠ፡፡ ክፍሏ ትንሽ ነች፡፡ ድንገት ፊት ለፊት መነጣጠማቸው ሁለቱንም በመጠኑ አደነጋገራቸው፡፡ ይሁንና በዙሪያቸው ያለው ትዕይንት ሲበዛ የተሟሟቀ፣ በሣቅና ሁካታ የተሞላ፣ ማጋነን የሚሰማበትና ጮክ ያለ የሰላምታ ልውውጥ የነበረበት ስለነበረ፣ እንዲህ ያለውን ዝርዝር ሁኔታ ማንም ልብ ብሎ አይመለከተውም፡፡

ምንም እንኳ በአለባበስዋና በደረበቻቸው ማላበሻዎቿ ከፍተኛ ጥንቃቄ ብታደርግም፣ ልብ ያለ ተመልካች ሊለያት ይችል ነበር፡፡ በእንፃሩ፣ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ማራኪነትዋን አልተጠቀመችበትም ነበር፡፡ አሁን ግን፣ እንዲህ ተነቃቅታ ስትታይ ማንፀባረቅ ጀምራለች፡፡ ውበቷ፣ ልክ እንድ የነፋስ ማራገበያ ተዘርግቶ ሲታይ ወይም የጣዎስ ወፍ የጭራ ላባዎችዋን ዘርግታ ወይም ቢራቢሮ ክንፎችዋን ዘርግታ ስትታይ ያለውን ማራኪ ውበት ይመስላል፡፡



ትጠብቀው የነበረው ለስላሣ የነፋስ ሽውታ ሲደርስና ወደዚያው ክፍታ ስትወጣ፣ ቁንጅናዋ እንደ ጀልባ አንሣፍፎ ወሰደው፡፡ ጆን ባፕቲስት፣ ሣንባው ጉረሮው ላይ ተወትፎበት፣ ለአፍታ ያህል ፀጥ ብሎ ቆመ፡፡ ከዚያ በኋላ ሁለት ርምጃ ወደፊት ተንቀሣቀሰ፡፡ ወዲያውኑም ሁሉም ጥይት በርሱ ላይ ያነጣጠረበት መሆኑን እንደተገነዘበ ወታደር፣ በአምስት ወይም ስድስት ሴቶች ተከበበ፡፡ ሴቶቹ፣ ስለዚህ ወጣት የጀብዱ ሥራ ሰምተው ስለነበረ፣ ወደ ቤታቸው ሊጋብዙት እንዲችሉ ባሎቻቸውን በየዕለቱ ይለምኗቸው ነበር፡፡ ብርማ ጉንጉን ያለበትን ቀይ ሰደሪያውን ለብሶ፣ አምሮና ተውቦ፣ ፀጉሩ በነፃነት ተዘናፍሎ፣ከራቫት ሣያስርና፣ከተፈጥሮአዊ ቁመናው ጋር ሲያዩት፣ የራሣቸውን ውስጣዊ ፍላጐት በርሱ ታሪክ ውስጥ እያደባለቁ ይስቡታል፡፡ አንዳንዴ በውስጣቸው የሚዳብረው ስሜት፣ በተንቆጠቆጠው ልብሣቸው ውስጥ አሁንም ሊቋቋሙት የማይችሉትን ምስጢራዊ የቁም ቅዥት ያጐላብቸዋል፡፡

በድንገተኛው ጥቃት ውስጥ ሲሰምጥ ጥቂት ሲቀረው፣ ከዚያች አነስተኛ የሙዚቃ ክፍል ውስጥ የአምባሣደሩ መምጣት ሲነገር ተጣድፎ ሲወጣ፣ በተፈጠረው አጋጣሚ እንቅስቃሴ ተረፈ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን የውሸት ጥንቃቄ ነበር፡፡ ቆንሲሉ፣ ሠረገላውን ለሙራድ ቢልክለትም፣ አርመናዊው አልተዘጋጀም ነበርና ምናልባት ቆንሲሉ ሠረገላውን ይፈልገው ይሆናል በሚል ግራ በተጋባ ስሜት ይመልሳል፡፡ በዚህም የተነሣ ሦስቱን ባሮቹን ከተጓዡ ጋር ቀድመው እንዲሄዱና እርሱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በእግር ተጉዞ እንደሚደርስ እንዲናገሩ አዝዞ ይልካቸዋል፡፡ ሠረገላው እየተሽከረከረ በቆንስላው ግቢ ደርሶ ሲቆም፣ ቆንሲሉ ራሱ በሩን ለመክፈት ተሽቀዳድሞ ነበር፡፡ ነገር ግን በአድምተኞቹ ኮስተር ያለ እይታ ተገርሞ ሲመለከት፣ ሠረገላው ሦስት በባዶ እግራቸው ያሉ፣ ሰውነታቸው በእራፊ የጥጥ ጨርቅ የተሸፈነና በፍርሃት አይኖቻቸው ቁልጭልጭ የሚሉባቸው የአገሬውን ተወላጆች አየ፡፡ ከአንድ አሥር ደቂቃዎች በኋላ፣ ሙራድ ቁና ቁና እየተነፈሰ፣ በሩ ዘንድ ደረሰ፡፡ መጀመሪያ ላይ፣ በጨለማው ውስጥ ሊለየው ባለመቻሉ ዘበኛው በአስነዋሪ ሁኔታ እንዳይገባ ከልክሎት ነበር፡፡

በዚህ የአጋጣሚ መጥፎ መዘግየት የተነሣ፣ የእራት ግብዣውም ዘግይቶ በመጀመሩ የእንግዶቹን ደስታ አቀዘቀዘው፡፡ ብዙዎቹ ተጋባዦች እንዲህ ላለ ኦፊሴላዊ በአል በአክብሮት ተጋብዘው አያውቁም፡፡ በመጨረሻ ላይ እንግዶቹ በሁለት ረዣዥም ጠረጴዛዎች ዙሪያ መቀመጫዎቻቸውን ያዙ፡፡ አምባሳደር ሙራድ፣ በመጀመሪያው ጠረጴዛ አጠገብ ከቆንሲሉ አንፃር ተቀመጡ፡፡ ሁለተኛው ጠረጴዛ በበላይነት የሚመራው፣ በቅኝ ግዛት ተወካይ በሰር

ብሬሱት ነበር። ስር ብሬሱት፣ ሙራድን ለመቀበል ወጥቶ የነበረውንና ነገር ግን ሳያገኘው የተመለሰውን የመልዕክተኞች ጓድ መርቶ የነበረ ሲሆን፣ ሙሴ ዴ ማይሌ በአሁኑ አቀራረቡ ሊያባብሰው የፈለገ ይመስላል። ክርሱ ትይዩ ያለው ቦታ በቆንስላው ውስጥ ቀዳሚ አስተርጓሚ ለሆነው ለፍሪሴቲ ተሰጠ። ፖንሴ፣ አሣዛኝ መሆናቸውን ወዲያውኑ በተገነዘቡላቸው ሁለት ሴቶች መካከል በሁለተኛው ጠረጴዛ ዙሪያ ሲቀመጥ፣ በስተቀኙ በኩል በቅርብ የተቀመጠው ወንድ፣ ፀሐፊው ማቼ ነበር።

አሊስ የተቀመጠችበትን ቦታ ለማየት ሲል፣ ጆን ባፕቲስት ክፍሉን ቃኘው። በመጀመሪያ ላይ ሊያያት ባለመቻሉ አንዳች የብስጭት ውጋት ተሰምቶት ነበር። እርስዋም ተገቢ ወዳልነበረ ቦታ ሄዳ ስለነበረ፣ በመጨረሻ ላይ ከፍሪሴቲ በስተቀኝ ተቀመጠች። ይህ ደግሞ በቀጥታ ከፍቅረኛዋ ፊት ለፊት ካለው ቦታ ባሻገር አድርጓታል። ቀደም ሲል ከተገናኙ በኋላ እንዲህ በሕዝብ ፊት ሲቀራረቡ ይህ የመጀመሪያ ጊዜያቸው ነበር። በደማቁ ብርሃን ውስጥ ሁለቱም የቤቱ አባወራና እማወራ የሆኑ ያህል የቁም ቅዥት ተሰማቸው።

ጆን ባፕቲስት ስሜቱ ጠንካራ ስለሆነ፣ ይህንኑ ሰዎች ከፊቱ ላይ እንዳያነብቡበት በመስጋት ወደ አሊስ አቅጣጫ አብዝቶ መመልከቱን ተወ። እንግዶቹ በሙሉ በየመቀመጫቸው ላይ ከሆኑ በኋላ አጠቃላይ ጫጫታው ሰከነ። ስርዓት ባለው ሁኔታ እራት አንድ ጊዜ በአንድ በኩል፣ በሌላ ጊዜ በሌላ በኩል ሲቀርብ ጨዋታው ደራ።

«ውድ ሙሴ ፖንሴ፣ እንግዲህ አሁን ወደ አቢሲኒያ ያደረግሽውን ጀብዱአዊ ጉዞ በርግጥ ትነግረናለህ?»

ጥያቄው የቀረበው ከሙሴ ማቼ ቢሆንም፣ በጠረጴዛው ዙሪያ ያሉትን ሰዎች ፍላጎትም የሚያንፀባርቅ ነበር።

«እንዲህ ከሆነ ጥያቄዎችን ልትጠይቀኝ ይገባሃል።» አለው ጆን ባፕቲስት። «አቢሲኒያ የምትገኘው በእጅግ ርቀት ቦታ ላይ ነው። በእያንዳንዱ ዕለት ያጋጠመኝ ሁኔታ ደግሞ በራሱ መጠን አንድ የመፅሃፍ ምዕራፍ የሚወጣው ነው»

«ከጉዞው ከራሱ ጀምር። እዚያ አገር ለመድረስ በርግጥ አደገኛ ነበር?» አለ ማቼ



የፀሐፊው ጥያቄ በአቀራረቡ ሁሉ ከእውነት የመነጨ ፈጣን አቀራረብ ቢሆንም፣ እውነቱ ግን እንደሁልጊዜውም ትዕዛዝ የሚከተል ነው። ቆንሲሉ፣ ከዚህ በኋላ አንድ ኦፊሴል ኤምባሲ ለመላክ ወስኖ በትጋት እያቀደ ባለበት ጊዜ ሊያጋጥም የሚችለውን አደጋም ለማወቅ ይፈልጋል። በዚህ ረገድ መረጃ ለመስጠት፣ የሙራድ እርዳታ አነስተኛ ነው። ስለዚህ የተሻለው ዘዴ ፖንሴ የራሱን የጉዞ ታሪክ እንዲናገር ማድረግ ነው። በዚህ ላይ ቆንሲሉ ራሱ በቀጥታ ሊጠይቀው ፈቃደኛ አይደለም፣ ወይም ደግሞ መድሃኒት ቀማሚው በርሱ ላይ ዝንባሌ እንዳለው ተረድቶ ክብር እንዲሰማው አልፈለገም።

የእራት ግብዣው ሲታቀድ፣ ሙሴ ዴ ማይሌ ፣ ፖንሴን የማጋነንና የማምካሸት ሃሣብ ነበረው። ስለዚህ የተለየ አትኩረት እንዳላደረገበት በማስመሰል፣ በሕዝብ ፊት እንዲናዘዝ ሂደቱን ጀመረው። በተቻለ መጠን፣ ፖንሴ ብዙ እንዲናገር እንዲያደርገው፣ ሙሴ ማቼ መመሪያ ተቀብሏል። የትረካውን አቅጣጫም ብልህነት በተሞላው ጥያቄ በመምራት፣ ፖንሴ የሚላትንም ሁሏንም ነገር በአስገራሚዋ የማስታወስ ችሎታው ውስጥ ይከትባታል። የአሊስ አይኖች በርሱ ላይ ማተኮራቸው ሲሰማው ጆን ባፕቲስት ሽሽት ጀመረ። በጠረጴዛው ዙሪያ ለተቀመጡት ቂላቂል ከበርቴዎች፣ የገለባ ያህል አልተጨነቀላቸውም። ይልቁንስ የጉዞውን ውኔ የተሞላበት መግለጫ፣ አደጋ፣ መከራና ያጋጠመውንም ደስታ የሚተርከው ለሚያፈቅራት ሴት ብቻ ሲል እንደሚሰጥና እርሷም እነዚህን ሁሉ እውነታዎች ከሰማች በኋላ ስሜቱን የምትጋራው ይሆናል በሚል ተናገረ።

የተንገፍን ትረካ ወደ ተግባራዊ ጉዳዮች በማስተላለፍ ረገድ፣ ማቼ ትልቅ ችግር ነበረበት። ፖንሴም፣ ባለማቋረጥ ከርዕሱ ወጣ እያለ ዝርዝር ውስጥ ስለሚገባ፣ ይህ ደግሞ ፀሃፊውን ከመጠን ባለፈ ስሜቱን ይይዘዋል። ለምሣሌ ፖንሴ ማለቂያ ወደሌለው የአቢሲኒያውያን የቡና ሥነስርዐት ይሸጋገራል። ማቼ፣ ወደ ሲናር ንጉስ ወይም እስከ ጣና ሐይቅ ድረስ ስላለው ጉዞ ለማወቅ ተራኪውን ወደ ኋላ ሊመልሰው ሲሞክር፣ ወይዛዝርቱ ግን ግልፅ የሆነ ስሜታቸውን በነዚህ ጉዳዮች ላይ በማሣየት፣ የሙሴ ማቼን ጥረት ያከሽፉበታል። ከዚህ በኋላ፣ ተስፋ በመቁረጥ፣ ፖንሴ ምንም እርባና የሌላቸውን ጥያቄዎች መመለስ እንዲችል ተወው።

ከእራት በኋላ፣ ጣፋጭ ምግብ ሊቀርብ ሲል፣ በመጠጥ ሞቅ ያላት የአንድ ነጋዴ ሚስት የሆነች ባለትልቅ ዳሌ ሴት ውይይቱን ለመካፈል ተደፋፈረች። በዚህም የተነሣ ለአሣ ሻጭነት ስትለማመድ የኖረች መሆንዋን በሚያጋልጥ ድምፅ፣ ጆን ባፕቲስትን አነጋገረችው።

«ጌታው፣ ሰዎች አቢሲኒያውያን ሴቶች ሲበዛ ቆንጆዎች ናቸው ይላሉ። ለመሆኑ አንዲት ሴት ይዘህ አልተመለስክም?»

ሁሉም ሰው ፖንሴን ተመለከተው

«ሴት?» አለ አይኖቹን ሰበር አድርጎ።

አጠቃላይ የሆነ የአፍታ ዝምታ ነገሠ። ጆን ባፕቲስት አይኖቹን ቀና አድርጐ ለአጭር ጊዜ ወደ አሊስ ተመለከተ። በዚህ እይታም ውስጥ የፍቅራቸው ሃይል ሁሉ በመካከላቸው ተላለፈ።

«እውነቱ፣ እመቤቴ» አለ ጥያቄውን ወዳቀረበችው ሴት አንዳችም ትኩረት ሣያደርግ «ጉዞውን የተቀበልኩትም አንዲት ሴት ለማግኘት ስል ነበረ። እናም እንዳገኘኋት አምናለሁ።»

ከአንደበቱ የወጡት ቃላት፣ ክስተር ብለው በመነገራቸው፣ ረዘም ላሉ ሴኮንዶች የቆየ ግራ የሚያጋባ ዝምታ ተከተለ።

«እያጃጃለን ነው!» አለ የወንድ ሰው ድምፅ በመጨረሻ ላይ። ውጥረቱ ፈጥኖ በመላላቱ ብዙ ሰዎች ሳቁ።

«እየቀለድክ ነው፣ አይደል?» አለው፣ ከአጠገቡ የተቀመጠው ሰው ወደርሱ ዘንበል ብሎ።

«የተጋነነ ነገር የለበትም»

ለአፍታ ያህል ሁሉም በመደነቅ «እምም» የሚል ድምፅ ካሰማ በኋላ፣ ጭውውቱ እንደቀድሞው ተሟሟቀ። ሙሴ ማቼ፣ የማዳሞዜል ዱ ማይሌን ውበት ሣያደንቅ በቀጥታ እንዳይመለከታት ራሱን ቢቆጣጠርም፣ እርሷ ከጆን ባፕቲስት ጋር የተለዋወጧቸውን የጨረፍታ እይታዎች በማስተዋል ትክክለኛ ትርጉሜውን ተረድቷል። ከዚህ በኋላ፣ ሁሉቱንም



በሚገባ በመከታተል እያስተዋላቸውና ለበኋለኛ ጊዜው እንዲጠቅመው፣ ማስታወሻውን በአዕምሮው ውስጥ መመዝገብ ቀጠለ።

እራት አበቃ። ተጋባዦቹም፣ በእንግዳ መቀበያው ክፍል ውስጥ በሚገኘው በንጉስ ሉዊስ አሥራ አራተኛ ሥዕል ስር ሆነው ቡና ለመጠጣት ከየተቀመጡበት ተነሱ። ፖንሴ በነበረበት ጠረጴዛ ዙሪያ የተመገቡት ሁሉ በጣም ተደስተውና በትረካው ተደንቀው ነበር። በመጀመሪያው፣ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው የተመገቡት ደግሞ ፊታቸው የከፋውና ያኮረፈ ነበር። በግልፅ ስሜት፣ የአቢሲኒያውን ንጉሥ ነገስት ባለሙሉ ሥልጣን አምባሣደርን አሣፋሪ ባህሪ በሃሜት ሲበጭቁት ነበር። የአምባሣደሩ አበላል በእጆቹ በመሆኑ፣ እንግዳና ያልተለመደ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ በአጠገቡ ያሉ ሰዎች ከአንድ ምግብ አብሣይ ጋር እራት እየተጋሩ እንደሆነ እስኪመስላቸው ድረስ፣ በአንዲት የዶሮ ብልት ላይ፣ ይህን ለማዘጋጀት ስለተጠቀሙት ዘዴ፣ ወጡ ውስጥ ስለተጨመረው የቅቤ መጠን ጥያቄዎችን ያቀርብ ነበር። በወይን ጠጅ ሞቅታ ሣቢያ አጠገቡ በተቀመጠች ሴት ቀሚስ ላይ ጣቶቹን ለመጥረግ ደርሶ ነበር። የባህሪው መጥፎነት ያለጥርጥር የታየው አንድ ብርጭቆ ጣፋጭ መጠጥ ከተጐነጨ በኋላ፣ ከጐኑ በተቀመጠችውና በፈረንሣይ ማህበረሰብ ውስጥ ሃብታሙ ባለባንክ የሆነውን ሰው ሚስት አንገቷ ሥር ሊስማት ማስመሰሉ ነበር። በፈረንሳይ ማህበረሰቡ ውስጥ የመጨረሻው ወሳኝ ዳኛ የሆነውና እያንዳንዱ አባልም ባህርይውን ለርሱ በሚስማማ መልክ እንዲያርቅ የሚያደርገው ሙሴ ዱ ማይሌ፣ ጉረሮውን የታነቀ በማስመሰል የሰዎችን ስሜት ለመቀየር ባይችል ኖሮ፣ ሁኔታው መጥፎ መልክ ይይዝ ነበር።

በክፍሉ ውስጥ እንዲህ የመሰሉ ታሪኮች ሲከናወኑና በአንዱ ጠረጴዛ ዙሪያ የሚረብሹ ትዕይንቶች በመኖራቸው እንግዶቹ ቅሬታዎቻቸውን ሲለዋወጡና በሌላው ጠረጴዛ አካባቢ በሚነገረው ትረካ ሲበሳጐ፣ አሊስ ክፉ የራስ ምታት እንደጀመራት ለመንገር ወደ እናቷ ሄደች። አስቀድሞ እምቢ ብላ የነበረ ቢሆንም፣ ይህን የእራት ግብዣ ለማዘጋጀት ልጅዋ ያደረገችውን ጥረት ማዳም ዱ ማይሌ ታውቃለች። ግንባሯ ላይ ከሣመቻት በኋላ፣ መልካም ሊሊት ብላ አሰናበተቻት። ጆን ባፕቲስት ግን ወጥቶ ለመሄድ እጅግ ተቸገረ። ሃያ ሴቶች ባለማቋረጥ ጨቀጨቁት። የምርጫው ሁኔታ ደከም ያለ ቢሆንም፣ ለእራት ግብዣቸው እንደሚመጣ ለአሥራ ዘጠኙ ቃል በመግባቱ እጅግ አስደሰታቸው። ሃያኛዋ ግን ምንም ለመጠየቅ ብልህነት እንደሆነ ብትገምትም፣ ወዲያውኑ፣ በሌሎች ላይ ቅናት አደረባት።

ጆን ባፕቲስት ለቆንሲሉ ምስጋናውንና አክብሮቱን ለመግለፅ ቀረበ። ቆንሲሉም፣ ስለአንደበተ ርቱዕነቱና ስለደስተኛ ስሜቱ እንኳን ደስ ያለህ አለው። በጠረጴዛው ዙሪያ የሚገኙ ተጋባዦችም ተጨማሪ ምስጋናቸውን አከሉ። ከዚህ በማስከተል ይህ አቢሲኒያዊ መልዕክተኛ፣ ቀደም ብሎ የመውጣት ልማድ ስላለው፣ አጅቦት ወደ ቤቱ ሊሄድ ይችል እንደሆነ መድሃኒት ቀማሚው ጠየቀ። ቆንሲሉ፣ ከዚህ ባለማቋረጥ ከሚያሣፍር ሰው ለመላቀቅ ሲል ሃሣቡን ወዲያውኑ ተቀበለ። ሠረገላውን እንዲጠቀሙበት ቢፈቅድም፣ አላስገደዳቸውም። በእንግዳ መቀበያው ክፍል፣ ሰው በለቀቀው አንድ ጥግ በኩል፣ አርመናዊው ባለመደገፊያ ወንበር ላይ እጥፍጥፍ ብሏል። የለበሰው ሸኬት በጥብስ ቅባት ተበክሏል። ምግብ በጣቶቹ ስለሚያነሣ እጆቹ በቅባት ወርዝተዋል። በዚህ ሁሉ የተነሣ አዲሱና ሃር መሣይ ሰማያዊ የመደገፊያ ትራስ ሊነገር ከሚችለው በላይ ተበላሽቷል። ፖንሴ፣ በእግር መጓዙ የተሻለ እንደሚሆን ገልፆ፣ አምባሣደሩን ጉትቶ ሲያነሣው፣ ሰውዬው በሁሉም አቅጣጫ እየተጥመለመለበት ያልተያያዘ ማጉመትመት አሰማ። በማዕድ ቤት ውስጥ እራታቸውን የበሉትን ሦስቱን አቢሲኒያውያን በመግቢያው በር ደረጃ ላይ አገኟቸው።

«ለተከበሩ አምባሣደር ባትሪ አምጡላቸው» ሲል፣ ሙሴ ዴ ማይሴ አዘዘ።

«በዚህ ትዕይንት ውስጥ ከሚያስፈልገው በላይ መብራት አለማብራት የተሻለ ይሆናል» ሲል፣ ጆን ባፕቲስት ሃሣብ አቀረበ።

ቆንሲሉም፣ የዚህን አስተያየት ትክክለኛነት በመገንዘብ በሽሽት ላይ እንደሚገኝ አንድ አነስተኛ ጉሣ በጭለማ እንዲሄዱ ፈቀደላቸው።

መንገድ ውስጥ ከገቡ በኋላ ለአንድ ሁለት መቶ ሜትሮች ያህል አብረው ተጓዙ። ከዚያ በኋላ ፖንሴ፣ የሙራድን ክንድ፣ ጠንካራ ለሆነውና አረቢኛ ለሚናገረው አቢሲኒያዊ ካስያዘው በኋላ ወደ ቬነሲያውያን ቤት ይዞት እንዲሄድ አዘዘው። ጆን ባፕቲስት በበኩሉ ወደ ግራ ታጥፎ በሰፊው የቆንስላው መሬት ዙሪያ ተጉዞ፣ በሁለቱም ጐናቸው መስኮት በሌላቸው ቤቶች መሃል በሚገኝ አነስተኛ መንገድ ውስጥ ገባ። ከነዚህ ቤቶች አንዱ የሌጋሲዮኑን የማዕድ ቤት ግቢ የሚለይና ለቁሣቁስ አቅራቢዎች መግቢያ በር ያለው ነው። በዚያ ቦታ ፍራንቾይዝ ስትጠብቀው አገኛት።



# 8

ፖንሴ፣ እምክ እምክ በሚሸትት ቀጭን የጎሮ ደረጃ፣ ፍራንቾይዝን ተከትሏት ወጣ። ከዚያ በኋላ ብቻውን ወደ አንድ ጨለማ የመልበሻ ክፍል አመራ። ቀጥሎም መስኮቱ የሌሊቱን ከዋክብት በብዛት እንዲያሣይ ተብሎ በስፋት ወደተከፈተ የመኝታ ክፍል ገባ። ቀሰል ያለ የሰሜን ነፋስ ከከተማው ዝቅ ብሎ ከሚገኘው የደለል ሥፍራ የአፈር ሽታ ተሸክሞ ያመጣል። ከምድር ቤቱ በኩል፣ ግራ የተጋቡት የእራት ግብዣው እንግዶች ውካታና ጫጫታ ይሰማል። ብዙዎቹ እስከዚህ ሰዓት ድረስ በሣቅ እያውካኩ ቆይተዋል። ጭል፣ ጭል የሚለው ሻማ፣ ከመቅረዙ ላይ ሆኖ፣ ቢጫ ብርሃኑን ፍቅረኛዋን በምትጠብቀው አሊስ ላይ ይረጫል። ጆን ባፕቲስት፣ በዝግታ ወደርስዋ ተራምዶ፣ በእቅፎቹ ውስጥ አስገባት። ልብሶችዋን አልቀየረቻቸውም ነበርና፣ ጆን ባፕቲስት ያንን እንግዳ ፀጉር፣ ጌጣጌጥና በተለይም ያንን በቅርቡ በአዕምሮው ውስጥ አትሞ ያቆየውን ውበት፣ ቀለሙንና የውበቱን ውህደት አጣምሮ የያዘውን አንፀባራቂ መልክ፣ በታላቁ የእንግዳ መቀበያ አዳራሽ ግዙፍ የመብራት ብርሃን ስር ተመለከተ። በአጭሩ፣ ሁለቱ ፍቅረኛሞች አንዳቸው ለሌላኛው በሕይወት ቆይተው ፣ይጓጉለት ለነበረው ጊዜ መድረሳቸውን በደስታ ለመገንዘብ ችለው ነበር። እዚህ ደረጃ ለመድረስ ብዙ መሰናክሎች ተደንቅረውባቸው ስለነበረ፣ በአሁኑ ጊዜ ያገኙትን ደስታ ለአመል ያህል እንኳ የሚያደናቅፍባቸው ነገር ቢኖር የማይቀበሉት ነው። ሁለቱም በስሜት ተውጠው በረዥም መሣሣም ውስጥ ቀለጡ። በጨለማ ውስጥ በቆየው የኦፔራ አዳራሽ፣ ትዕይንቱ ሊያልቅ ሲል፣ ውብ ጥንዶች በመድረክ ላይ ዳግመኛ ሲገናኙ የሚሰማውን የድጋፍ እልልታ ዓይነት ድምፅ ከምድር ቤቱ በኩል ይሰማል።

ከአጠገባቸው አንድ አልጋ አለ። ብቸኝነታቸው፣ ከማንኛውም ዓይነት ሁከት ነፃ የሆነው፣ ምስጢራቸውም ፍፁም የግላቸውና የተሟላ ነበር። ይሁን እንጂ በዚህ የፍቅር ደረጃ ላይ እርስ በርሣቸው የመፈላለጋቸው ነገር፣ እጅ እንዲሰጡና እንዲሣሣቁ አድርጓቸዋል ብሎ ማመን እነርሱን አለመረዳት ነው። እስከዚህ ጊዜ ድረስ፣ አንድ ቀን ርስበርስ የመፋቀራቸውን የነፃነት ተስፋ በማጣፈጥ ያሣድጉታል። በዚህ የደስታ ተስፋቸው ላይ የተጋረጡትን ገደቦች ሁሉ ለማስወገድ ጊዜውን ይጠብቃሉ።